# መሠረታዊ ክርስትና ትምህርት

# Basic Teaching of Christianity

***By: Samuel Salato / Pastor/***

የመጀመሪያ እትም 1997 ዓ.ም

ሁለተኛ እትም በ1998 ዓ.ም

ሦስተኛ እትም በ1999 ዓ.ም

አራተኛ እትም በ2001 ዓ.ም

**Addis Ababa**
**Ethiopia**

*በመጋቢ ሳሙኤል ሳላቶ*

**ይህንን መጽሐፍ**
**ያለ ደራሲው ፈቃድ**
**ማባዛት ወይም ማሳተም**
**በሕግ የተከለከለ ነው።**

**© Copyright Samuel Salato, 2006**

All rights reserved

**በመጽሐፉ ላይ ያለዎትን ጥያቄ፣ አስተያየትና ገንቢ ሐሳብ ለጸሐፊው በአድራሻ መላክ ይቻላል።**

ሞባይል፡ 251912-12 71 69
**2519-11-83 14 66**
ኢሜል፡ samuel_salato@yahoo.com
ፖ.ሣ.ቁ **22195 ኮድ 1000**

አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

ይህንን ክቡር ስጦታ ለወዳጄ

ለ____________________

በታላቅ አክብሮት አበርክቼአለሁ።

ከ____________________

ቀን____________________

# ምዕራፍ አንድ – መጽሐፍ ቅዱስ

## ትምህርት 1 – የመጽሐፍ ቅዱስ አመጣጥ

« ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና» (1ተሰ 1፥5)

- የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈ መለኮታዊ ሥልጣንና ኃይል ያለው መጽሐፍ ነው (2ጴጥ 1፥19–21)
- መጽሐፍ ቅዱስን ከ40 በላይ የሚሆኑ ጸሐፊዎች በመንፈስ ቅዱስ በመመራት የጻፉት ሲሆን 66ቱ መጻሕፍት ተጽፎ የተጠናቀቁበት ዘመን በአጠቃላይ ሲታይ 1፥500 ዓመታትን ፈጅቶበታል።
- የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት የተጻፉት ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ1400 እስከ 400 ዓ.ዓ ባሉት ጊዜያት ውስጥ ሲሆን አዲስ ኪዳን ደግሞ ከ45 እስከ 100 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ውስጥ ነው።
- የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ነገሥታት፣ ካህናት፣ ገበሬዎች፣ ነቢያት፣ ምሑራን፣ ዓሣ አጥማጆች፣ ግብር ሰብሳቢዎች፣ ሐኪሞች ወዘተ… ሲሆኑ ሌሎችም ይገኙበታል።
- ጥንት ቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፉት ከተክሎችና ከእንስሳት ቆዳ በተሠሩ /ፓፒረስና ብራና/ ጥቅልል ላይ ሲሆን በ1456 ዓ.ም ጆሐን ጎትን በርግ በተባለ በአንድ ጀርመናዊ ሰው ለዚህ ሥራ ተብሎ የጽሕፈት ማተሚያ መሣሪያ ከተፈለሰፈበት ጊዜ ጀምሮ መጽሐፍ ቅዱስ በወረቅት ታትሞ መውጣት ጀመረ።
/ሉቃ 4፥17–20፥ 2ጢሞ 4፥13/
- የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎችንና ቁጥሮችን በመለየት ያዘጋጀው እንግሊዛዊ ጳጳስ ስቲፈን ላንግተን በ13ኛው ምዕተ ዓመት ነበር።

- መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ግዕዝ ቋንቋ መተርጎም የተጀመረው በ4ኛው ምዕተ ዓመት ሲሆን የተጠናቀቀውም በ7ኛው ምዕተ ዓመት ነው።
- መጽሐፍ ቅዱስን በአማርኛ ለመጀመሪያ ጊዜ የተነጎመው አብርሃም /አባ ሮሜ / በ19ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ ነው።
- አዲስ ኪዳን በአማርኛ ለመጀመሪያ ጊዜ ታትሞ የወጣው በ1829 ዓ.ም ሲሆን ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ በ1840 ዓ.ም ታተመ።
- እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ አዲስ ኪዳን በ1034 የዓለም ቋንቋዎች የተተረጎመ ሲሆን ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ በ405 የዓለም ቋንቋዎች መተርጎሙን የሚያሳዩ መረጃዎች አሉ።



- «ካኖን» /Canon /፡– የመጻሕፍት መመዘኛ ወይም መለኪያ ነው። ቃሉ የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ መለኪያ ወይም መስፈሪያ ማለት ነው። ስለዚህ አንድ መጽሐፍ የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ወይም የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑ በካኖን መመዘኛ ማለፍ አለበት።

እነዚህም መለኪያዎች (መመዘኛዎች)፡–

1. የጸሐፊውን ሥልጣን ማወቅ – አንድ መጽሐፍ ከሐዋርያት በአንዱ ወይም ከሐዋርያት ጋር በቆየው አገልጋይ እጅ መጻፍ ይኖርበታል።
2. የመጽሐፉ ሐሳብ ከፍተኛ መንፈሳዊ ምስጢር ያለው ሆኖ የብሉይና የአዲስ ኪዳን ትምህርት ግንኙነት ሊኖረው ይገባል።
3. መጽሐፉ በአብዛኛው አብያተክርስቲያናት ተቀባይነት ሊያገኝ ይገባል።
4. መጽሐፉ በግልፅነት የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለው መሆን ይኖርበታል።

በዚህ መሠረት፣

- በካኖናዊነት የተመዘኑና ተቀባይነት ያገኙ 39 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በ5ኛ መቶ ዓ.ዓ በዕዝራ የተሰበሰቡና የተቀናበሩ መሆናቸውን ብዙ የታሪክ ጸሐፊዎች ያምናሉ።
- 27ቱን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር በካኖን መመዘኛ ያዘጋጀው በ397 ዓ.ም በካርታጎ /cartago / የተሰየመው የመጀመሪያው የቤተክርስቲያን ጉባኤ ነው።

### 1.2 የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አመዳደብ

መጽሐፍ ቅዱስ በውስጡ 66 መጻሕፍትን የያዘ ሲሆን ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን በመባል በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል

ሀ/ የብሉይ ኪዳን 39 መጻሕፍት

- የሕግ/የኦሪት/መጻሕፍት.................................. 5
  ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም
- የታሪክመጻሕፍት................................................ 12
  ከኢያሱ እስከ መጻሕፍት አስቴር
- የግጥምየቅኔ/መጻሕፍት.........................................5
  ከኢዮብ እስከ መኃልየ መኃልይ
- የትንቢትመጻሕፍት............................................ 17

ለ/ የአዲስ ኪዳን 27 መጻሕፍት

- ወንጌላት ---------------------- 4

  ከማቴዎስ እስከ ዮሐንስ ወንጌል
- ታሪክ ------------------------1
  የሐዋርያት ሥራ
- መልዕክቶች........................................... 21

ከሮሜ እስከ ይሁዳ መልዕክት
❖ የትንቢትመጽሐፍ........................................ 1
የዮሐንስ ራዕይ

ሐ/ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ጥቂቶቹ፡-
ሙሴ /እረኛ ወይም የሕዝብ መሪ / ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም
ኢያሱ /የጦር መሪ/ - መጽሐፈ ኢያሱ
ሰለሞን /ንጉሥ/ -መጽሐፈ ምሳሌ መክበብ መኃልየ
ዳንኤል /ጠቅላይ ሚኒስቴር/ - ትንቢተ ዳንኤል
ኤርምያስ /ነቢይ/ - 1ኛ እና 2ኛ ነገሥት
ዕዝራ /መሪ / - መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ 1ዜና
ሳሙኤል /ነቢይ/ - መሳፍንትና ሩት
ኢሳይያስ / ነቢይ / - ትንቢተ ኢሳይያስ
ማቴዎስ /ቀራጩ /- የማቴዎስ ወንጌል
ሉቃስ /ሐኪም/ - የሉቃስ ወንጌልና ሐዋርያት ሥራ
ጳውሎስ /ምሑር/ - 14ቱ የጳውሎስ መልዕክቶች
ጴጥሮስ /ዓሣ አጥማጅ/ - የጴጥሮስ መልዕክቶች
ዮሐንስ /ዓሣ አጥማጅ/ - ዮሐንስ ወንጌል፣ ዮሐንስ መልዕክቶችንና ዮሐንስ ራዕይ

መ/ መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠራባቸው ስሞች:-
- የእግዚአብሔር ቃል ሐዋ 13:48 ዘዳ 28:1 ኤር 42:6
- የጌታ ቃል ሐዋ 13:49 2ተሰ 3:7
- የሕይወት ቃል ፊል 2:16 ዮሐ 1:1
- የእውነት ቃል ኤፌ 1:13
- የምሥራቹ ቃል ሮሜ 10:14-16 ኢሳ 61:1
- የመስቀሉ ቃል 1ቆሮ 1:18
- የሕግ ቃል ወይም የሕግ መጽሐፍ ዘዳ 28:58 ኢያ 1:8
- ቅዱሳን መጽሕፍት 2ጢሞ 3:15
- የክርስቶስ ወነንጌል ሮሜ 1:9 2ቆሮ 4:3-4
- የትንቢት ቃል ራዕ 1:3 2ጴጥ 1:19
- የጸጋው ቃል - ሐዋ 20:32

## 1.3 የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል ለሰዎች ያዘጋጀውን ዘላለማዊ የመዳን ዕቅዱን ይናገራል፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ባሕርይም በቀጥተኛ መገለጥ ከእግዚአብሔር የተሰጠ መሆኑና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት /አነሳሽነት/ በቅዱሳን ሰዎች መጻፉ ነው፡፡
/2ጴጥ 1፥19-21 2ሳሙ 23፥2/

ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስን ሥልጠን በሚከተሉት ነጥቦች እንመለከታለን

« ከእኛ የሰማችሁትን የእግዚአብሔርን ቃል በተቀበላችሁ ጊዜ በእናንተ በምታምኑት ዘንድ በእርግጥ እንደሚሠራ እንደ



እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ ስላልተቀበላችሁት እግዚአብሔርን ያለማቋረጥ እናመሰግናለን» 1ተሰ 2፥13
- ማንም ለገዛ ፈቃዱ ሊተረጉም ሊቀነስና ሊጨምር አይችልም፡፡ /2ጴጥ 1፥20-21 ራዕ 22፥18-19 ዘዳ 4፥2 ዘዳ 12፥32 ምሳ 30፥5-6/
- የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት ነው /2ጢሞ 3፥17/
- የሕይወትና የእምነት ብቸኛ መመሪያ ነው /መዝ 119፥9-11፥105/
- የማይለወጥ፣ የማይሻርና የማይደከም ፍጹም የሆነ እርስ በርሱ የማይጋጭ ነው፡፡ /ሉቃ 16፥17 ማቴ 24፥35/
- በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የሚሰጡ የፀጋ ስጦታዎችን ሁሉ ይፈትናል፡፡ ቃሉን ሊተካ የሚችል መገለጥም ሆነ ስጦታ የለም፡፡ /1ተሰ 5:19-21/
- ፍጥረትን ሁሉ የፈጠረና ያፀና ደግፎም የያዘ ነው፡፡ /ዘፍ1:3 ዕብ 1:3፥ 2ጴጥ 1:2-21/
- የመሥራት ሥልጣን አለው /ኢሳ 45:23፡ 55:11 ኤር 23:29ዕብ 4:12/
- የመንቀልና የመትከል ሥልጣን አለው /ኤር 1:9-10/

## 1.4 የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅም

- እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን እውነት ለማወቅና ሌሎችንም ለማሳወቅ የምንጠቀምበት ነው /2 ጢሞ 3:14-17 ያዕ 1:22-25 ዮሐ 20:31፥ 8:11/
- የእግዚአብሔርን በጎ ፈቃድ ምን እንደሆ የምናውቅበት ነው:: /ዘዳ. 29:29፥ ኤፌ 5:17፥ 1ተሰ. 5:17-18/
- ሰው ከዘለዓለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት የሚሸጋገርበትን መንገድ የሚያሳይ ብርሃን ነው፡፡ /መዝ. 119:105-107/
- የአማኞችን መንፈሳዊ ሕይወት የሚያሳድግ ምግብና ሥነ ምግባራዊ ሕይወት መመሪያ ነው፡፡ /1 ጢሞ 4:11-16 1ጴጥ.2፥2-3 /
- ለመቀደስ፣ ከኃጢአት ነፃ ለመውጣትና በረከትንም ለማግኘት /ዮሐ 17:17፥ ኤፌ 5:26 ፥ ያዕ 1:25፥ መዝ 119፥9 /
- እግዚአብሔርን እንዳንበድል ይጠብቀናል /መዝ 119:11/
- ወደ ፍጹምነት ሕይወት ያሳድጋል ቆላ 1:28
- ለመንገዳችን ብርሃን ነው /መዝ 119:105 /
- መከናወንን ይሰጣል /ኢያ 1:7-8 ዮሐ 15፥7 2ነገ. 18:6-7 ዘካ. 6:15/
- ለመንፈሳዊ ውጊያ ያዘጋጃል /ኤፌ 6:10-18/
- የእግዚአብሔር ሰዎች ያለፉባቸውን የእምነት ልምምዶችን እያየን በቂ ትምህርት በማግኘት በሕይወትና በአገልግሎት ፍሬያማ ለመሆን /1ቆሮ 10:11 ሮሜ 15:4/

ይህም የክፍሉን አጠቃላይ ሐሳብ በዝርዝር ማየትና ማወቅ የምንችልበት መንገድ ነው ። በዚህ ሂደት ውስጥ መጠየቅና መልስ ማግኘት የሚገባን መሠረታዊ ነጥቦች፡-

ማን? /ተናጋሪው ወይም ጸሐፊው/
ለምን?/መልዕክቱ የተጻፈበት ምክንያት/
ምን? /ሊያስተላልፍ የፈለገው መልዕክት/
መቼ? /መልዕክቱ የተጻፈበት ጊዜና የነበረው ሁኔታ/
የት? /መልዕክቱ የተጻፈበት ሥፍራ ወይም ቦታ/
ለማን? /የመልዕክቱ ተቀባይ/ የሚሉ ናቸው

2/ የመተርጎም ሂደት / Interpretation/
የክፍሉን ሐሳብና አባባል በሌላ ቃላት በግልጽነት ማየትና መረዳት የምንችልበት መንገድ ነው። ይህ እውነትን ሳያዛቡ የክፍሉን ሐሳብ በግልጽ ትርጉም የማስቀመጥና መልዕክት የማግኘት ሂደት ነው።

3/ የማዛመድ ሂደት /Application/
ከዚህ ክፍል ምን እማራለሁ? ምን መፈጸም አለብኝ? ምን መተው አለብኝ? እንዴት መኖር አለብኝ?... ወዘተ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የቃሉን ትርጉም ለሕይወታችን በማዛመድ ራሳችንን የምናይበትና ቃሉ የሚለንን ተግባራዊ የማድረግ ሂደት ነው። /ያዕ. 1:22-25/

7. መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት ማድረግ የሚገባን ቅድመ ዝግጅት

- መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት በሩጫ የሚደረግ ነገር አይደለም ጊዜ መወሰን፣ አስፈላጊ ነገሮችን ማዘጋጀት፣ ዕቅድ ማውጣትንና ለዕቅዱ መገዛትን ይጠይቃል።
- መጽሐፍ ቅዱስን፣ ለጥናት የሚረዱ ማጣቀሻ መጻሕፍትን፣ ማስታወሻ ደብተር፣ የተለያየ ቀለም ያላቸው እስክሪብቶችን፣ ፀጥታ ያለበት ምቹ ቦታና ሰዓት ማዘጋጀት።

- የምናጠናውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልና ከተሰጡ አጠናን ዘዴዎች አንዱን መምረጥና መወሰን።

- በጸሎት አእምሮንና ልብን አዘጋጅቶ መጀመር። ምክንያቱም ጥናት ፈቃደኝነትንና ትዕግሥትን እንዲሁም የተዘጋጀ አእምሮንና ልብን ይጠይቃል። አእምሮንና ልብን መክፈት ከስሕተት ለመታረም፣ ያልተስተካከለውን ሕይወት ለማስተካከልና ለእግዚአብሔር እውነት ብቻ ለመገዛት ጥሩ ቁልፍ ነው። /ሐዋ 17:11-12 ሉቃ 24:45/

- ቃሉን በተከፈተ ልብ በማስተዋል ማንበብ፣ መስማትና ማዳመጥ ቃሉንም ለመታዘዝ ዝግጁ ሆኖ መቅረብ

/ዕዝ 8:2-3 8 ሐዋ 10:33 ሉቃ 24:32-34/

⏭ የሰው ተፈጥሮአዊ አእምሮ ብቻውን ትክክለኛውን የቃሉን ምስጢር መረዳት ወይም ማወቅ ስለማይችል «ያስተምራቸው ዘንድ መልካሙን መንፈስ ሰጣቸው» ተብሎ እንደተጻፈ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛ ደራሲና አስተማሪ ለሆነው መንፈስ ቅዱስ በመስጠት መቅረብ ነው::

<u>መንፈስ ቅዱስ ፡–</u>

- በቃሉ ያለውን የእግዚአብሔርን ሐሳብ ይገልጣል
- ወደ እውነት ሁሉ ይመራል
- ያስተምራል
- የሰማነውንና የተማርነውን ቃል ያሳስበናል

## 8/ <u>የጽሞና ጊዜ መውሰድ /Devotional times/</u>

/መዝ 1፥2 መዝ 119፥10–11፥ 15–16/

ሀ ለጽሞና ጊዜ ጠቃሚ ሐሳቦች

- የጽሞና ጊዜ አስፈላጊነትና ጥቅም ማወቅ
- ሁል ጊዜ ቃሉን መራብና መጠማት/ማቴ. 5:6/
- የጽሞና ጊዜን መወሰንና በትጋት መጠቀም/ዘፍ 32:24/
- የጽሞና ጊዜን አለማቋረጥ
- በጸሎት መጀመርና በምስጋና መዝጋት

ለ. የጽሞና ጊዜን የማሳደግ መንገዶች

- ዕለት ዕለት በተወሰነ ሰዓትና ስፍራ ላይ መገኘትና በፀጥ በእግሩ ሥርማረፍ/ሉቃ10፥38–42 ማር 6፥31/
- በድካምሳይሆን በንቃ አእምሮና በተዘጋጀ ልብ መጀመር
- እግዚአብሔር ለቃሉ አእምሮአችንንና ልባችንን እንዲከፍት መጸለይና የሚናገረንን ለመስማት ዝግጁ ሆነን መቅረብ /መዝ. 85:8፥ ሐዋ 10፥33 1ሳሙ 3፥10/
- እምነት በተሞላ ሕይወት ከእግዚአብሔር ዘንድ የጸሎትን መልስ በመጠበቅ መጸለይ
  /መዝ (40):1 መዝ. 5:3 ዕን 2:1/
- የእግዚአብሔር መንፈስ ከቃሉ ያስተማረንን እውነት በየዕለቱ በማስታወሻ ደብተራችን ላይ ማስፈር ያነበብነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍልና የተቀበልነውን መልዕክት በአእምሮአችን ማሰላሰል።
  /ኢያ 1:8 መዝ 1፥2 መዝ 119፥15–16/
- ከጌታ በተማርነውና በተቀበልነው ቃል መኖርና መጠበቅ መዝ. 19:10–11፤ ዮሐ. 14:23/

ሐ. የጽሞና ጊዜ መውሰድ ጥቅም

- ◊ መንፈሳዊ ኃይል ለማደስና ጥንካሬ ለማግኘት /ማቴ. 4:4/
- ◊ ለዕለቱ ተግባራችን ከእግዚአብሔር ዘንድ መመሪያ ለመቀበል



- ◊ ጥበብ ለማግኘት /ኢሳ 33:6/
- ◊ ለነፍሳችን መንፈሳዊ ዕረፍት፤ሰላምና በረከት ይሰጣል።
  /ዘዳ. 28:2፤ መዝ. 19:8፤ 46:10-11/
- ◊ ለዕለቱ መንፈሳዊ ጦርነት ያዘጋጃል /ኤፌ 6:10–17/
- ◊ ለሌሎች የምናስተላልፈውን መልዕክትና ራዕይ ከጌታ ለመቀበል /ሕዝ. 3:1–4/
- ◊ በዙሪያችን ካሉ መንፈሳዊና ሞራላዊ ውድቀቶች ራሳችንን ለመጠበቅ /1ጢሞ. 6:11፤ 2ጢሞ 2:22/
- ◊ በቃል በፀጋና በመንፈስ ፍሬ ሁሉ ለማደግ /1ጢሞ 4፥13–16/
- ◊ የእግዚአብሔር ቃል በሕይወት ስለማይኖር ቃሉን ለመቀበል /ዘዳ 8:3 ማቴ 4:4/

የጽሞና ጊዜ በእያንዳንዱ ቀን ለጸሎት፣ ቃሉን ለማጥናትና ለማሰላሰል በእግዚአብሔር ፊት ልባችንን የምንቆይበት የተወሰነ ሰዓት ነው። ስለሆነም አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ የተሞሉለት ምቹ ሥፍራና ጊዜ ሊሆን ይገባል። /2ነገ 4:8–10 ፊል 1፥22/

የእግዚአብሔር ቃል ፍጹምና እውነት የሆነ የማዳንና የማስታረቅ ኃይልን የተሞላ፣ የማይለወጥ ዘላለማዊና ሁሉን የሚሠራ፣ በሰው ልብ ተዘርቶ ለሰው ዳግም ልደትን የሚሰጥ፣ የሚያሳድግ፣ ወደ ሕይወትም የሚመራ በዘመናት ሁሉ ሕያው ሆኖ የሚኖር ነው።
ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃልየሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ በግልም ሆነ በቡድን ስንማርና ስናነብ፣ ስናጠናም ትኩረት ተሰጥቶበሙሉ ልብ አእምሮንናመንፈስን በማዘጋጀት በጸሎትና እምነት ጭምር መሆን አለበት።እግዚአብሔር የቃሉን ምስጢርና ኃይል በመንፈስ ቅዱስ በኩል ይገልጥልናል። /2 ጴጥ 1:19/

*« ከእርሱም ይልቅ እጅግ የፀና የትንቢት ቃል አለን። ምድርም እስኪጠባ ድረስ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ እስኪወጣ ድረስ ሰው በጨለማ ስፍራ የሚበራን መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየተጠነቀቃችሁ መልካም ታደርጋላችሁ። » /1ጴጥ. 2:1–3/*

*«ሰው ከእግዚአብሔር ቃል በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም።» /ማቴ 4:4፡ ዘዳ. 8:3፡ /*

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምንነትና አመጣጥ በሚመለከት ተወያዩበት
2. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ስለመሆኑ ማረጋገጫው ምንድነው?
3. ካኖን ማለት ምን ማለት ነው?
4. መጽሐፍ ቅዱስ በተመረጡ ቅዱሳን እጅ በሚጻፍበት ጊዜ በዚህ ሥራ ላይ የጸሐፊዎችና የመንፈስ ቅዱስ ግንኙነት እንዴት ነበር የሥራ ድርሻቸውስ?
5. መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና መከተል ያለብን መርሆችንና መጠቀም ያለብንን ስልቶች ዘርዝሩ
6. መጽሐፍ ቅዱስን መተርጎም የሃይማኖት መሪዎች ተግባርና ሥልጣን ብቻ ነው ለሚሉ ሰዎች ምላሻችሁ ምንድን ነው ለምን?
7. መጽሐፍ ቅዱስ እስትንፋስ እግዚአብሔር ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት መጽሐፍ ነው የሚያሰኙ ልዩ ባሕርያትስ ምንድን ናቸው?
8. መጽሐፍ ቅዱስ የሚጠራባቸው ምሳሌያዊ ስሞች ምንን የሚያመለክቱ ናቸው?



# ምዕራፍ ሁለ`

## የእግዚአብሔር መለ`ታዊ ማንነት

### ትምህርት 2 –

**2.1 <u>እግዚአብሔር፡–</u>**

**እግዚአብሔር የሚለው ቃል ከግዕዝ የተገኘ ሲሆን «እግዚዕ» ማለት ጌታ «ብሔር» ማለት ዓለም ወይም ሕዝብ በመሆኑ እግዚአብሔር ማለት የዓለም ጌታ ማለት ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪና ገዢ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባትና የሰው ልጆች ሁሉ አምላክ ነው።**

**የሰው አእምሮ በጊዜ፣ በቦታ፣ በመረዳትና በማስተዋል አቅሙ የተወሰነ በመሆኑ ስለ እግዚአብሔር ማንነት ሙሉ በሙሉ መረዳት አይችልም።**

**ሀ/ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርያት**

- ◊ **መንፈስ ነው /ዮሐ 4፡24/**
- ◊ **ዘላለማዊ ነው /ዘፍ 21፡39 ዘጸ 3፡13–14/**
- ◊ **ሁሉን ቻይ ነው /ዘፍ 17፡1፥ ማቴ 19፡26 ሉቃ 1፥37/**
- ◊ **በሁሉም ስፍራ ይገኛል / መዝ. 139፡7–10 /**
- ◊ **አይለወጥም /ሚል 3፡6፤ መዝ. 102፡25–27/**
- ◊ **ሁሉን ዐዋቂ ነው /ሮሜ 11፡33–36፤ ኢሳ 40፥13–14፤ መዝ.147፡4–5፤ 139፡1-2/**
- ◊ **በራሱ ብቁ ሆኖ የሚኖር ነው /1ጢሞ. 6፡16፤ 1፡17፤ ዘዳ. 32፡12፤ 39/**
- ◊ **ከሁሉ የበላይ ባለሥልጣን ነው። /ዳን 4፡35 ሮሜ 9፡20–21 ኢሳ 46፡9/**

ለ/ የእግዚአብሔር የሥነ-ምግባር ባሕርያት

ቅዱስ ነው /ዘሌ 19፡2 1ጴጥ 1፡15/

ጻድቅና ቅን ፈራጅ ነው /መዝ 119፡137፤ ኢሳ. 33፡22/

እውነተኛና ታማኝ ነው /ዘዳ 7፡9፤ 32፡4 /

መሐሪ፣ ቸርና ታጋሽ ነው /ዘጸ 34፡6 /

ፍቅር ነው /1ዮሐ 4፡7-10፤ ኤር. 31፡3/

ሐ. እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች የገለጠበትና ሰው እግዚአብሔርን ማወቅ የሚችልበት መንገዶች፡-
« ደግሞም ሰው አይቶኝ አይድንም ፊቴን ማየት አይቻልህም»
/ዘጸ 33፥20/

1. <u>የሰው ሕሊና</u>
የሰው ሕሊና በራሱ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት መንገድ ነው።እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር መልካምና ክፋውን መለየት እንዲችል በውስጡ የተከለለት የግብረ ገብነት ወይም የሞራላዊ የሕሊና ምስክርነት አለው።/ዘፍ 2፡17/
ስለዚህም የእግዚአብሔርን ቃል ያልሰሙ እንኳ በተፈጥሮ ከሕሊናቸው ምስክርነት የተነሣ እግዚአብሔርን ማወቅ ይችላሉ።
/ቲቶ 1፡15-16/

2. አጠቃላይ መገለጥ

ሀ/ በፍጥረት /ዘፍ 1፥1-31 መዝ 19፥1-6 102፥25-27
ቆላ 1፥15-17 ሐዋ 17፥24-25/

ለ/ በታሪክ /ሐዋ 17፥26-27 መዝ 78፥1-72 ሐዋ 14፥16-17/
እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ማንነቱንና ፈቃዱን ገልጧል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉ መንፈሳዊ ምስጢራትን የተሞሉና ያልተጻፉ በዓለም ላይ የተፈጸሙ የዘመናት ታሪኮች ሁሉ የእግዚአብሔርን ሉዐላዊነትና ሁሉን ቻይነት የሚገልጡ ናቸው። ታሪክን ሁሉ የሚቆጣጠር የታሪክ ጀማሪና ፈጻሚ እግዚአብሔር ራሱ ነው።

3. ልዩ መገለጥ

ሀ/ በመጽሐፍ ቅዱስ /ዘጸ 3፥14-15 ኢሳ 66፥1 ዮሐ 1፥1 ሉቃ 24፥44/
ሰው የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን መጽሐፍ ቅዱስ በማጥናት በመስማትና በማመን እግዚአብሔርን ሊያውቅ ይችላል።



እግዚአብሔር ራሱን በመጽሐፍ ቅዱስ ከገለጠበት መንገድ አንዱ ስሙን በማሳወቅ ነው።

❖ የእግዚአብሔርን ማንነት የሚገልጡ የብሉይ ኪዳን ዋና ዋና ስሞች ከዕብራይስጥ የተወሰዱ ናቸው።
እነዚህም፡-

➢ «ኤሎሂም» ኃያል /ብርቱ/ ማለት ነው።
ይህ ስም እግዚአብሔር የሁሉ ፈጠሪ ገዥና ጻድቅ ፈራጅ መሆኑን የሚገልጥ ነው።
/ዘፍ1፥1 ኤር 32፥27-28 ዘዳ 10፥17-18/

➢ «ያህዌህ» /Jehovah/ «ያለና የሚኖር »
«...እግዚአብሔር መሐሪ፣ ሞገስ ያለው፣ ታጋሽም፣ ባለብዙ ቸርነትና እውነት እስከ ሺ ትውልድም ቸርነትን የሚጠብቅ ...»
/ዘጸ 3፥14 34፡5-7/

➢ «አዶናይ» ይህ ስሙ እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ ባለቤትና የሚገዛም ጌታ መሆኑን የሚገልጥ ነው።
/ዘፍ 19፥2 ኢያ 3፥11 ኢሳ 6፥8 መዝ 8፥1፡9/

❖ ባሕርይውንና ሥራውን የሚገልጡ ጥምር ስሞች፡-

- ያህዌህ - ይርኤ - እግዚአብሔር ያዘጋጃል /ዘፍ 22፡13-14/
- ያህዌህ -ራፋ -እግዚአብሔር ፈዋሽ /ዘጸ 15፥26/
- ያህዌህ - ንሲ - እግዚአብሔር ዓላማዬ /ዘጸ 17፥8-15/
- ያህዌህ -ሻሎም -እግዚአብሔር ሰላማችን /መሳ 6፥24/
- ያህዌህ - ጽድቅኒ -እግዚአብሔር ጽድቃችን /ኤር 23፥6/
- ያህዌህ - ሻማ - እግዚአብሔር እዚህ አለ /ሕዝ 48፥35/
- ያህዌህ - ማካዶ ሽኮም - የሚቀድስ እግዚአብሔር /ዘሌ 22፡32-33/
- ያህዌህ - ሮይ - እግዚአብሔር እረኛዬ / መዝ 23፥1/
- ኤልሻዳይ - ሁሉን ቻይ አምላክ /ዘፍ 17፥1/
- ኤልኦላም - የዘላለም አምላክ /ዘፍ 21፥33/

❖ የማዕረግ ስሞች፡-

➢ ያህዌህ ሳቦት - የሠራዊት ጌታ /1ሳሙ 1፡3 ኢሳ 6፡3 5፥ 48፡2፤ አሞጽ 5፡27/

ስለዚህ እግዚአብሔር አብ፡-

- የፍጥረት ሁሉ አባት ነው/ሐዋ17፥24-27 ኤፌ 3፥14 /
- የእስራኤል ሁሉ አባት ነው /ዘጸ 4፥22 /
- የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነው /ኤፌ. 1:3/
- የአማኞች ሁሉ አባት ነው / ገላ 3፥26/

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የእግዚአብሔር አብን ስም እየጠራ ማንነቱን ገልጧል። /ማቴ 10:32-33 ፡ 19:26 ዮሐ 14:1-2 ፡ 17:24-25/

## 2.4 እግዚአብሔር ወልድ /ኢየሱስ ክርስቶስ/

- ኢየሱስ ፡- የግሪክ ቃል ነው። ትርጉሙም «አዳኝ» ማለት ነው።
- ክርስቶስ፡- ማለት ደግሞ በግሪክ ቋንቋ «የተቀባ» ማለት ነው።
- ኢየሱስ ክርስቶስ ማለት ለማዳን ተቀብቶ የመጣ ጌታ ማለት ነው።
- ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ከመወለዱ በፊት ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የነበረ ዘላለማዊ አምላክ ሁሉን የፈጠረ የሥላሴ አንዱ አካል ነው።
- ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም የተወለደ የእግዚአብሔር ልጅ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ የሆነ ስለ ሰው ልጅ ኃጢአት በመስቀል ላይ የተሰቀለ፣ የሞተና ሞትን አሸንፎ የተነሣ፣ በክብር ያረገና በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ ዳግም በታላቅ ኃይልና ግርማ ሊመጣ ያለ ጌታ ነው።

  /ማቴ 16:16 1ቆሮ 15:27 ሐዋ 1:9 ኢሳ 9:6-7 ዮሐ 1:1 ራዕ 1:8/

ሀ. የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጥ በብሉይ ኪዳን፡-

1. ሁሉን በሚችል አምላክነቱ

   ለአብርሃም የተገባውን ተስፋ ቃል ለማስፈጸም፡- ዘፍ 18:1

   በጽድቅ ፈራጅነት፡- /ዘፍ 19:1/

   ተስፋ ለመስጠት፡-/ ሆሴ 1:7/



2. እንደ እግዚአብሔር መልአክ /መልዕክተኛ/

   ለአጋር /ዘፍ 16:1/

   ለያዕቆብ /ዘፍ 31:1 /

   ለሙሴ /ዘጸ 3:2/

   ለእስራኤል /ዘጸ 14:19 /

   ለበለአም /ዘኁ 22:22/

   ለጌዴዎን /መሳ 6:1 /

ለ. ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠራባቸው መለኮታዊ ስሞች

- ☒ አልፋና ኦሜጋ /መጀመሪያም መጨረሻም የሌለው።
  /ራዕ 1:8 22:13/
- ☒ በእግዚአብሔር ማንነት«እኔ ነኝ»/ዮሐ8:58ዮሐ 10፥9-15/
- ☒ አማኑኤል /ማቴ 1:22 ኢሳ 7:14/
- ☒ የእግዚአብሔር ልጅ /ዮሐ 6፥69፥ ራዕ 2:18/
- ☒ ጌታ /ማቴ 7:21 ሉቃ 1:43 መዝ 110:1/
- ☒ የእግዚአብሔር ቃል /ዮሐ 1:1፥ 1ዮሐ 1:1፥14 ራዕይ 19:13/

ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው መሆኑን የሚገልጡ ሁኔታዎች

- ☑ ከድንግልማርያም ተወልዶአል/ማቴ1:182:11ሉቃ1:30-38/
- ☑ ዕድገቱ በግልፅ ተመዝግቧል/ማቴ 2:8 26:12 ዮሐ 2:21/
- ☑ በሰው መጠሪያ ስም ተጠርቷል
  - ኢየሱስ /ማቴ 1:21/
  - የሰው ልጅ /ማቴ 8:20 11:18/
  - የአብርሃም ልጅ /ማቴ 1:1/
  - የዳዊት ልጅ /ማቴ 10:47/

☑ መድከሙ - ዮሐ 4፡6

☑ መራቡ - ማቴ 4፡2 21፡18

☑ መጠማቱ - ዮሐ 19፡28

☑ መፈተኑ - ማቴ 4፡1 ዕብ 2፡18

ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕርይ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ መሆኑ በእግዚአብሔር ቃል በግልጽነት ተቀምጧል።

« እርሱ /ወልድ/ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም» /ፊል 2፡6/

እርሱም /ወልድ/ የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው የሚታዩትና የማይታዩትም ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና/ቆላ 1፡15-17/

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሎ ሲጠራ ከአብ የተሰጠ መለኮታዊ ስም እንጂ ወልድ በአብ ተፈጠረ ለማለት ወይም ወልድ ጅማሬ እንዳለው የሚያመለክት ቃል አይደለም።/ዕብ 5፥5-6 ፤ 7፥3 /

## 2.5 እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ

መንፈስ ቅዱስ የሚለው ስም ከዘላለም ለነበረው ላለውና ለሚመጣ ለእግዚአብሔር ሕልውና መገለጫ ነው። ይህ ቅዱስ መንፈስ የራሱ አካል ያለው እግዚአብሔር የሆነ ከእግዚአብሔር የወጣ /የሠረጸ/ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ለአማኞችና ለቤክርስቲያን የተሰጠ ዓለምን ስለ ኃጢአት የሚወቅስ የእውነት መንፈስ ነው። መንፈስ ቅዱስ የሥላሴ ሦስተኛ አካልና ከአብና ከወልድ ጋር በመለኮት በኃይልና በሥልጣን እኩል የሆነ መለኮታዊ አካል ወይም ሕላዊነት ያለው ነው። /ዮሐ 15፥26 ፤ 16፥7-15 /



ሀ/ የመንፈስ ቅዱስ አካል /ሕላዊነት/ ማረጋገጫ

- ስሜት አለው - ሮሜ 15፡30 ኤፌ 4፡30 ኢሳ 63፡10 ዕብ 10፡29
- ዕውቀት አለው - ነህ 9፡20 1ቆሮ 2፡10-12
- ፈቃድ አለው - 1ቆሮ 12፡11
- ያጽናናል - ዮሐ 16፡7
- ይመሰክራል -ዮሐ 15፡26 ሮሜ 8፡16
- ይመረምራል - 1ቆሮ 2፡10
- ይናገራል - ራዕ 2፡7
- ያስተምራል- ዮሐ 14፡26
- ይጮኻል - ገላ 4፡6
- ይመራል - ሮሜ 8፡14
- ያዝናል - ኢሳ 63፡10
- ይማልዳል - ሮሜ 8፥26

ለ/ የመንፈስ ቅዱስ ገላጭ ስሞች

- ◆ መንፈስ ቅዱስ /ሉቃ 11፡13/
- ◆ የክርስቶስ መንፈስ /ፊል 1፡19 ሮሜ 8፥9/
- ◆ የእግዚአብሔር መንፈስ /ሮሜ 8፥14 1ቆሮ 3፥16/
- ◆ የተስፋ መንፈስ /ሮሜ 15፥13/
- ◆ የሕይወት መንፈስ /ሚል. 2፥15 ሮሜ 8፥2፥ 11/
- ◆ መልካም መንፈስ /ነህ 9፥20/
- ◆ አጽናኝ /ዮሐ 14፥16፥ 15፥26/
- ◆ የዘላለም መንፈስ /ዕብ 9፥14/
- ◆ የክብር መንፈስ /1 ጴጥ 4፥14/
- ◆ የእምነት መንፈስ /2ቆሮ 4፥13/
- ◆ የኃይልና የፍቅር መንፈስ /2ጢሞ 1፥7/

- የእውነት መንፈስ /ዮሐ 14:17 15:26/
- የጸጋ መንፈስ /ዕብ 10:29/

## 2.6 የሥላሴ አንድነት ከሚገልጡ ተግባራት ጥቂቶቹ

| ሥራ | አብ | ወልድ | መንፈስ ቅዱስ |
|---|---|---|---|
| መፍጠር | ዘፍ 1:3 | ዮሐ 1:1፤ ቆላ. 1:15-17 | ዘፍ 1:2 ኢዮ 26:12-13 |
| ታላቁ ተልዕኮ | ኢሳ. 6:8፤ ማቴ. 9:37-38 | ኢሳ. 61:1፤ ማቴ. 28:20 | ሐዋ. 1:8፤ 13:2 |
| በጌታ መወለድ | 1ዮሐ 4:9 | ፊል. 2:6-7 | ሉቃ 1:35 |
| በጥምቀት | ማቴ 28፥18-20 | ማቴ 28፥18-20 | ማቴ 28፥18-20 |
| በደህንነት | 1ቆሮ. 1:30-31 | 1ዮሐ 5:11-12 | ኤፌ 1:13-14፤ 1ቆሮ 6:11 |
| ስጦታዎችን ማደል | ሐዋ. 11:17 | ኤፌ. 4:7-8 | 1ቆሮ. 12:4-11 |
| በጸሎት | ዮሐ 16:23 | ዮሐ 14:13-14 | ሮሜ 8:26 |
| ትንሣኤን መስጠት | 1ተሰ. 4:14፤ ሐዋ. 2:24 | ዮሐ 11:25-26፤ 5:21 | ሮሜ 8:11 |

## 2.7 የሥላሴ አንድነት ከሚገልጡ መለኮታዊ ባሕርያት ጥቂቶቹ፡-

| ባሕርይ | አብ | ወልድ | መንፈስ ቅዱስ |
|---|---|---|---|
| ዘላለማዊ | መዝ. 90:2 | ራዕይ 1:18 | ዕብ. 9:14 |
| ሁሉን ቻይ | ዘፍ. 17:1 | ዮሐ. 6:39-40 | ዘካ. 4:8 |
| በሁሉ ቦታ መገኘት | ኤር. 23:24 | ማቴ. 28:20 | መዝ. 139:7 |
| ሁሉን ማወቅ | ኢሳ. 40:27-28 | ዮሐ. 2:25 | 1ቆሮ. 2:11 |
| አለመለወጥ | ሚል. 3:6 | ዕብ. 13:8 | ዕብ. 9:14 |
| ቸርነት | ዘፀ. 34:6 | ማቴ. 9:36 | ነህ. 9:20 |
| እውነት | ዮሐ 17:3 | ዮሐ 14:6 | ዮሐ. 16:13 |
| ቅዱስ | ዘሌ. 19:2 | ሐዋ. 3:14 | ኤፌ. 4:30 |
| ፍቅር | 1ዮሐ. 4:16 | ዮሐ. 15:9 | 2ጢሞ. 1:7 |



- አብ የምክር፣ የሐሳብና የፈቃድ ምንጭ የሆነ አካል ነው። ኤፌ 1:1፥ ሐዋ 22:1
- ወልድ ከዘላለም ከአብ የተገኘ አንዲያ ልጁና ፈቃዱን፣ ምክሩንና ሐሳቡን ፈጻሚ ሆኖ የተገለጠ መለኮታዊ አካል ያለው ነው። /ዮሐ 15:1፥ ኤፌ 1:13 ዘፍ 1:2/
- አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ ዓይነት መለኮታዊ ባሕርይ እኩል አምላክነትና ዘላለማዊነት አላቸው
- አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በምክር አንድ ናቸው። በሕልውናቸው አይቀዳደሙም በሥልጣንም አይበላለጡም።
- አንዱን ስንጠራ ሁሉን እየጠራን ነው አንዱን ስናመልክ ሁሉን እያመለክን ነው አንዱ በሚሠራበት ሁሉም በአንድነት ይሠራሉ። አንዱ የሚያውቀውን ሁሉም ያውቃሉ። የማይለያይ፣ የማይከፋፈል የማይጨፈለቅ አንድነት አላቸው። አንዱ ከሌላው ሳይቀድም ለዘላለም በሦስትነትና በአንድነት ይኖራሉ ይሠራሉ። እንግዲህ በእምነት መቀበልና መኖር የሚገባን ከሰው ተፈጥሯዊ አእምሮ በላይ የሆነ ትምህርተ ሥላሴ ትልቁ ምስጢር እዚህ ላይ ነው። /1ቆሮ. 5:24፤ ፊል 3:21፤ ራዕ 22:17/

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> በዚህ ዓለም በዓይናችን የምናያቸው ነገሮች የእግዚአብሔርን ባሕርይ መግለጽ ስለማይችሉ ምሥጢረ-ሥላሴን በምሳሌ ለማስረዳት ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል።

## የውይይት ጥያቄዎች

1. እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበትና የሰው ልጅም እግዚአብሔርን ማወቅ የሚችልበት መንገዶችን በተመለከተ ተወያዩበት።
2. ልጁ ክርስቶስ እግዚአብሔር አብን እንዴትና በምን ገለጠው? (ዮሐ 1:18) ይመልከቱ.
3. መንፈስ ቅዱስ አምላክ ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫው ምንድን ነው?
4. ሙሴ በብሉይ ኪዳን በእግዚአብሔር መለኮታዊ አንድነት ላይ ያተኮረው ከምን የተነሣ ነው? (ዘጸ 6:4) ይመልከቱ
5. የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርይ አንድነትና አካላዊ ሦስትነት እንዲሁም የሦስቱ አካላት ሥራ ክፍፍል በተመለከተ ተወያዩ
6. ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆኖ የመወለዱ አስፈላጊነትና ጥቅም በዝርዝር ተመልከቱ።



# ምዕራፍ ሦስት፡- *መላዕክት*

## ትምህርት ሦስት –

### 3.1 የመላዕክት አፈጣጠርና ባሕርያቸው

**መላዕክት የሚለው ቃል በእብራይስጥ «መላክ» በግሪክ «አንጀል» የሚል ሲሆን ትርጉሙ መልዕክተኛ ማለት ነው። መላዕክት በፍጥረታቸው ረቂቃን ሆነው የተለያየ የሥልጣን ደረጃ ያላቸው ከእግዚአብሔር ሥልጣን በታች የሚገኙ መናፍስት ናቸው። /መዝ 104፥4/**

**መላዕክት በእግዚአብሔር የተፈጠሩ ፍጥረቶች ሲሆኑ የተፈጠሩበት ጊዜና ሁኔታ በውል አይታወቅም። ሆኖም ግን ሰው ከመፈጠሩ በፊት እንደተፈጠሩ እንረዳለን። /ኢዮ 38:6–7 ቆላ 1:16 መዝ 148:2–5/**

**መልአክ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ 273 ጊዜ ተጠቅሶአል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መላዕክት የሚሰጠውን እውነተኛና ትክክለኛ ሐሳብ መረዳት ለመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚሰጠው ጠቄሜታ የጎላ ነው። በተለይም በቅዱሳን መላዕክትና በወደቁት ወይም በርኩሳን መላዕክት መካከል ያለውን የሥራ ልዩነት ጠንቅቀን ባወቅን ቁጥር መንፈሳዊ ዕውቀትም ሆነ ለመንፈሳዊ ውጊያ ያለን መረዳት ይጨምራል።**

- **መላእክት መናፍስት ናቸው /ዕብ 1:14 መዝ 104:4/**
- **ከሰው ልጆች ይልቅ የላቀ ኃይል አላቸው። /2ሳሙ 4:15–16 ራዕ 3:1 2ጴጥ 2:11/**

- መላእክት በሚታይ ነገር አምሳል የመገለጥ ችሎታ አላቸው

/ዘፍ 19፡1-6 ሐዋ 1፡10-11፣ ማቴ 28፡2-3/

- መላእክት የመናገርና የመሥራት ችሎታ አላቸው።

/ማቴ 28፡5-7፣ 1ጢ.ዋ4፡1-2/

- መላዕክት ቅዱሳን መላዕክትና የወደቁ መላዕክት ተብለው ይጠራሉ /ራዕ 12፡7-12 ሉቃ 10፡18 ይሁዳ ቁ 6/

## 3.2 የቅዱሳን መላዕክት ስም

- ሚካኤል-የመላዕክት አለቃ /ይሁዳ ቁ 9፣ ዳን 12፣1/
- ገብርኤል - በእግዚአብሔር ፊት የሚቆም /ሉቃ 1፡19/
- ሱራፌል - እሳተ ነበልባል /ኢሳ 6፡2/
- ኪሩቤል- የእግዚአብሔር ዙፋን የሚከቡ/ሕዝ 10፡1/
- የሰማይ ሠራዊት - /ሉቃ 2፡13/
- እልፍ አዕላፋት - /ራዕ 5፣11/

## 3.3 የቅዱሳን መላዕክት ተግባር

- የእግዚአብሔርን ድምፅ ይሰማሉ /መዝ 103፣20/
- የእግዚአብሔር ታማኝ መልዕክተኞች ናቸው።

/መዝ 103፡20-21 ሉቃ 1፣26-33/

- የእግዚአብሔር ፍርድ አስፈጻሚዎች ናቸው።

/ዘፍ 9፡12-13 ሐዋ 12፡23፣ ማቴ 13፣39/

- የቅዱሳን አገልጋዮች ናቸው።

/ዕብ 1፡14 ዳን 12፣2 ዳን 10፣21፣ መዝ 34፣7/

- እግዚአብሔርን ቀንና ሌሊት ያመልኩታል

/ኢሳ 6፡3 ራዕ 5፡11-14/

- የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸው

/ሉቃ 2፣13 ማቴ 4፣11 ሉቃ 22፣43/



## 3.4 ርኩሳን /የወደቁ/መላዕክት (ራዕ 12፡10)

ሀ/ የሰይጣን እና የሠራዊቱ አወጻደቅ ውጤት

- ✓ ሰይጣን በዕብራይስጥ ቋንቋ ‹ዲያብሎስ› በግሪክ ‹ከሳሽ› ተብሎ ይጠራል።
- ✓ ሰይጣን በእግዚአብሔር የተፈጠረ ልዩ ውበትና ክብርን የተጎናጸፈ የእግዚአብሔር መልአክ ነበር።

/ኢሳ 14፣12-14 ሕዝ 28፣11-18 /

- ✓ ከትዕቢቱ የተነሣ በእግዚአብሔር ላይ አመጸ ከሰማይም ተጣለ ለዘላለምም ወደቀ /ሉቃ10፡18 ራዕ 12፡ 7-9/
- ✓ ከሰይጣን ጋር ሌሎችም መላዕክት አብረውት በአመፅ ምክንያት ወደቁ ገምሶቹ ለፍርድ ቀን በጥልቁ በግዞት እየተጠበቁ ሲሆን ገምሶቹ በምድር ላይ ከአለቃቸው ከዲያብሎስ ጋር ሆነው ይሠራሉ /ይሁዳ ቁ.6፣/
- ✓ እስከ ፍርድ ቀን የታሠሩ መላዕክት /2ጴጥ. 2፣4 /
- ✓ ያልታሰሩ ተንቀሳቃሽ አጋንንት / ማር 1፣23-26 ሉቃ 8፣26-33 1ጴጥ 5፣8/
- ✓ ለጊዜው የታሠሩ አጋንንት / ራዕ. 9፣1-11/

ለ/ የሰይጣንና የሠራዊቱ ዋና ዋና ስሞች

- የዚህ ዓለም ገዢ /ዮሐ 12 16፡11፣ 14፡30/
- የዚህ ዓለም አምላክ /2ቆሮ 4፡4/
- ዲያብሎስ/ከሳሽ/ /ራዕ 12፡10/
- ክፉው /ማቴ 13፡19/
- አጋንንት /ማቴ 12፡24-28/
- ርኩስ መንፈስ /ማር. 5፡8 ሉቃ. 4፡33፣ 36/
- ፈታኝ /ማቴ 4፡31 1ተሰ 3፡5/

## የውይይት ጥያቄዎች

1. መላዕክት መቼ ተፈጠሩ ከፍጥረት በፊት ወይስ በኋላ የተፈጠሩበት ዓላማና ተግባራቸውን ግለጽ
2. የወደቁ ወይም ርኩሳንና ቅዱሳን መላዕክት እኩል ዕውቀት ኃይልና ሥልጣን አላቸውን ለምን
3. ቅዱሳን መላዕክትና ርኩሳን መላዕክት የሚለያዩት በባሕርይ ወይስ በተግባር
4. ሰይጣን የሚጠራባቸው ስሞች ማንነቱን እንዴት ይገልጡታል?
5. ሰይጣንና መናፍስቱ ዋና ተግባሩ አድርጎ ያነጣጠረው በምን ላይ ነበር ለምን ይመስላችኋል?
6. ቅዱሳን መላዕክት ያማልዳሉን ለምን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ



# ምዕራፍ አራት

## ትምህርት ደህንነት

### ትምህርት 4 – ሰው

እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በራሱ መልክና አምሳል ከፈጠረ በኋላ የሕይወትን እስትንፋስ ከራሱ በመስጠት ሰው ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ይልቅ የከበረ እንዲሆን አድርጎታል። ስለዚህ ስለሰው ሁለንተናዊ ተፈጥሮ ማወቅና መረዳት ለእግዚአብሔር ሰው እጅግ አስፈላጊ ነው። /ዘፍ 1፡26 ኢሳ 45፡12 ኢዮ 33፡4/

በእግዚአብሔር «መልክና አምሳል» የሚለው ሀሳብ አካልን ወይም ቅርጽን የሚያመለክት ሳይሆን አስተሳሰብን፣ ዕውቀትን ፣ ቅድስናን ፣ ፍቅርን... ወዘተ የሚያመለክት ሆኖ ሰው የእግዚአብሔር የባሕርይ ተከፋይ መሆኑን ለመግለጥ ነው።
/ዘፍ 2፡19–20 ቆላ 3፡10 2ጴጥ 1፡2–11/

#### 4.1 የሰው አካላዊ አፈጣጠር

- የሰው ሥጋዊ አካል የተበጀው ከምድር አፈር ነው። /ዘፍ 2፡7/
- የሰው ሥጋዊ አካል የሚያስፈልገውን ሁሉ ከዚህ ምድር ማግኘት እንዲችል ተደርጎ ተፈጥሮአል። /ዘፍ 2፡16/
- የሰው ሥጋዊ አካል እንዲሞትና ከትንሣኤው በኋላ የከበረ አካል እንዲለብስ ተወስኖአል /2ቆሮ 5፡1–15/

#### 4.2 <u>ሰው ከሌሎች ፍጥረታት የሚለይበት ምክንያት</u>

- በመለኮታዊ ምክክር ተፈጥሮአል «እንፍጠር»
- በእግዚአብሔር ቀጥተኛ ሥራ ተሳትፎ ተፈጥሯል
- በእግዚአብሔር መልክና አምሳል ተፈጥሯል /Image/ ።
- የመናገር፣ የመግባባትና የመለየት ተሰጥኦ አለው

- አለመታዘዝ፡- የሰማነውን በሙተው በሌላ መንገድ መጓዝ ወይም ለመስማት እምቢ ማለትና ሰምቶ አለማድረግም ነው።/ሮሜ 5፡19 2ቆሮ 10፡6 ዕብ 2፡2-3 ኤፌ 2፡2-5 ዕብ 4፡6-11/
- በኃጢአት መወለድ፡- አዳም በወደቀ ጊዜ ዘሩ ሁሉ አብሮት በኃጢአት ወደቀ። ስለዚህ ሰው ሁሉ የውርስ ኃጢአት አለበት። /ሮሜ5፡12/

## 5.2 የኃጢአት ባሕርያት

- ዓላማን መሳት፡- ይህም የተሳሳተ መንገድ መከተል፣ የእግዚአብሔር ሞገስና ክብር ማጣት ከክብር ቦታ መውደቅና መቋሰል እንዲሁም እግዚአብሔርን ደስ አለማሰኘት ነው።
  /ኢሳ 1፡3-4 53፡4-5፣ ሮሜ 8፡2-8/
- ጽድቅን ማጣት፡- ራሳቸውን የማይገዙ፣ ፈርሃ እግዚአብሔር የሌላቸው የአምላካችንን ጸጋ በርኩሰት (በሴሰኝነት) የሚለውጡ ናቸው።
  /ይሁዳ 1፡4 መዝ. 14፡1-7፣ 49፡12/
- ፍትሕ ማዛባት/ፍርድ ማጣመም/ የእግዚአብሔርን እውነት በመስወር ለሰው ሊደረግ የሚገባውን አለማድረግ ነው።
  /ዘሌ 19፡15 መዝ 82፡1-4፤ ዕንባ. 1፡3-4/
- አመፃ፡- ለእግዚአብሔር ፈቃድ አለመታዘዝና አለመገዛት ነው።
  /ኢሳ 1፡2 1ጢሞ 1፡9-11፤ 1ዮሐ 3፡4/
- ምኞት፡- በራሱ ውስጣዊ ፍላጎት መነዳት(መወሰድ) ነው።
  /1ዮሐ2፡16 1ጴጥ 4፡3 ያዕ 1፡14/
- ክፋት፡- ለሰውና ለፍጥረት ሁሉ ፍቅርና ርኅራኄ ማጣትና በጭካኔ መንፈስ መሞላት ነው።
  /ሮሜ 3፡12 2ተሰ 3፡2፤ ሮሜ 1፡29-31/

## 5.3 <u>የኃጢአት ዓይነቶች</u>

1. የውርስ ኃጢአት -/ ሮሜ 5፡12-14/
2. የድፍረት ኃጢአት -/ መዝ 19፡12-13/
3. የተሰወረ ኃጢአት - /ምሳ 28፥13/



4. ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ ምኞት - /ማር 7፡21-23/
5. አለማዊነትን የመምሰል ባሕርይ –
/ሮሜ 12፡2 1ዮሐ2፡15-17፤ ቆላ. 2፡8፤ 1ጢሞ. 4፡7-8/
6. የሥጋ ሥራ - /ገላ 5፡19-21 ቆላ 3፥5-9/

## 5.4 የኃጢአት ውጤት

- በክፋት ማደግ ፡- ሰው ኃጢአትን በሕይወቱ ሲለማመድ በክፋት እየበረታ ይሄዳል - ዘፍ 6፡5 2ጢሞ 3፡2-9 ዘፍ 4፡5-8
- አመፅን መጨመር፡- በኃጢአት ውስጥ ያለ ሰው ውስጣዊ ዕረፍት ስለሌለው ለአመፃ ተግባር ድፍረትን እየተሞላ ይሄዳል /ሮሜ 1፥18 ኢሳ 57፡20-21 ማቴ 24፡12/
- መከራ፡- ሰው ኃጢአትን እየጨመረ በሄደ ቁጥር በሕይወቱ መከራ ይበዛበታል ያገኘዋል
  /ዘፍ 4፡13-14 ሮሜ 2፥9/
- የሕሊና ወቀሳ/guilt/፡-
  /ዘፍ 3፡8 ዮሐ16፡8፤ መዝ. 51፡3/
- የአስተሳሰብ ብክለት/Pollution/፡-
  /መዝ. 53፡1-3፤ ፊል. 3፡19፤ 2ቆሮ. 11፡3/
- በጨለማ ውስጥ መኖርና መመላለስ፡-
  /ኤፌ 5፡7-13 ዮሐ 3፡19-21/
- ለማይረባ አእምሮ አልፎ መስጠት
  (a depraved mind) /ሮሜ. 1፡21-28/
- ሞት፡- ኃጢአት በሰው ሕይወት ላይ የሚያመጣው ክፉ ውጤት ሞት ነው። /ያዕ 1፥15/
  ይህም፡-

1. ከእግዚአብሔር መለየት
   /መንፈሳዊ ሞት/ ኤፌ 2፡12
2. በጎ ሕሊናን ማጣት /ዕብ 9፡14/
3. ነፍስ ከሥጋ መለየትን ያጠቃልላል። /ዘፍ 3፡19/

ስለዚህ በኃጢአት ምክንያት በእግዚአብሔር መልክና አምሳል የተፈጠረ የከበረ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ለመታየት አፈረ። የእግዚአብሔር ቁጣ በሰዎችና በፍጥረት ሁሉ ላይ ከመምጣቱም በላይ ሰው ሰውን ለመበደል /እርስ በርስ ለመጠፋፋት/ ራሱን ለክፍ ሥራ አሳልፎ ሰጠ። ኃጢአትም እንደተላላፊ በሽታ በአንድ አዳም ምክንያት ለሰው ዘር ሁሉ ደረሰ፤ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ካለው ጽኑ ፍቅር የመነጨ የተትረፈረፈ ጸጋና የጽድቅ ስጦታ ደግሞ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በተከፈለው መስዋዕትነት የተነሣ በእርሱ ያመኑ ሁሉ ጻድቃን ይሆኑ ዘንድ የእግዚአብሔር ሀሳብና በጎ ፈቃዱ ሆነ። /ሮሜ 5፡12-21/

# ትምህርት 6 – ንስሐ

## 6.1. የንስሐ ትርጉም

ንስሐ ማለት አንድ ሰው ከልቡ ፈቃደኝነት እግዚአብሔርን ለመምሰል በሐሳቡና በድርጊቱ ከነበረበት ሁኔታ ውስጥ ፈጽሞ መውጣት፣ መለየትና መለወጥ ሲሆን ይህም ኃጢአቱን በመናዘዝና በመጸጸት ከፍጹም ልብ በእንባ ወደ እግዚአብሔር መመለስ ማለት ነው። ስለዚህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስና የመጥመቁ ዮሐንስ የስብከታቸው መጀመሪያ «የእግዚአብሔር መንግሥት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ» የሚል ነበር።/ማቴ 3፡1 ማር 1፡14–15/

## 6.2 የንስሐ አስፈላጊነት

- ሰው ሁሉ ኃጢአተኛ ስለሆነ ንስሐ እንዲገባ እግዚአብሔር አዝዞአል /ሮሜ 3፡23 ሐዋ17፡30/
- ሰው ወደ እግዚአብሔር መቅረብና መታረቅ የሚቻለው በንስሐ ሕይወት ነው። /ሐዋ 20፡21/
- የኃጢአት ስርየት የሚገኘው በንስሐ ነው/ሉቃ 24፡47/
- ደህንነት መለወጥና የሕይወት ጸጋን የምናገኘው በንስሐ ነው /2ቆሮ 7፡10–11/
- አለመታዘዝና ንስሐ አለመግባት ለጥፋት ይዳርጋል፡/ምሳ 29፡1 ሉቃ 13፡3 ምሳ 28፥13/

## 6.3 ስለንስሐ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

- ✓ ንስሐ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን ሰው ከጥፋት ተመልሰው ከእግዚአብሔር ጋር የሚታረቅበት ብቸኛ መንገድ መሆኑ ይታወቃል። /ዮናስ 3፡1–10/
- ✓ የመጥመቁ የዮሐንስ ስብከት መሪ ቃል ንስሐ ነበር። /ማቴ 3፡1–2/
- ✓ የጌታ ኢየሱስ ስብከት ለንስሐ ነበር። /ማቴ 4፡17/
- ✓ ደቀመዛሙርትም ንስሐ እንዲሰብኩ አዘዛቸው /ማቴ 6፡12/
- ✓ የጳውሎስ ስብከት ሰዎችን ወደ ንስሐ መጥራት ነበር /ሐዋ 13፡38–39/
- ✓ ሰው ሁሉ ንስሐ እስኪገባ ድረስ ጌታ ወዶ ይታገሳል። /2ጴጥ 3፡9/

በአጠቃላይ የወንጌል መልዕክት ሰውን ለንስሐ መጥራትና በክርስቶስ በኩል ከእግዘለአብሔር ጋር ማስታረቅ ነው። /ሐዋ 2፡37-38/



## 6.4 የንስሐ ውጤት

- በሰማያት ታላቅ ደስታ ይሆናል /ሉቃ 15፡7–10/
- የኃጢአት ይቅርታ ያመጣል። /ሕዝ 18፥27–28፤ መዝ 51፥7 2ዜና 7፥14/
- ለመንፈስ ቅዱስና ለጸጋው ሙላት ሕይወትን ያዘጋጃል። /ሐዋ 2፡38/
- በረከትንና ፈውስን ያመጣል። /ኤር 4፡1–2 2ኛ ዜና 7፥13–15፥ ኢሳ 57፥16–19/
- ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ያለውን ኅብረት ያድሳል። /ፊል 1፡10–16/
- የሕይወት መታደስንና መነቃቃትን ይሰጣል /ዕዝ 9፡9/
- የነፍስ ሰላምና ዕረፍትን ይሰጣል/ ዘፍ 4፡13–14/
- አዲስ ልብና አዲስ መንፈስ ይሰጣል። /መዝ 51፥10፥ ሕዝ 18፥31፤36፥26/
- እግዚአብሔርን የማወቅ እውቀት ይሰጣል /ኤር 31፥34 ሆሴ 4፥6፤ 5፥15/

ስለዚህ እውነተኛ ንስሐ ከልማዳዊ ጸጸትና ከሃይማኖታዊ ሥርዓት የተለየ ፍሬ ያለበት በአስተሳሰብ በአካሄድና በተግባር የሕይወትን ለውጥ የሚያመጣ የደህንነትንም መንገድ ለመከተል በር ከፋች ሲሆን ፍጹም መታዘዝና እምነትም የሚገለጽበት የእግዚአብሔር መልካም ሐሳብና ፈቃድ ነው። /2ቆሮ 7፡9–11 ማቴ 3፡7–10/

# ትምህርት 7 – ደህንነት

የደኅንነት ትርጉም ፡– ደህንነት ማለት ሰው ከኃጢአት ፣ ከእግዚአብሔር ቁጣ፣ ከገሃነም ፍርድ፣ ከሰይጣን ባርነትና ከሞት ፍርሃት ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን ማምለጥና ከዘለዓለም ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት መሻገር ማለት ነው። /1ጢሞ1፡15 ዕብ 2፡14–15 ሮሜ 8፡1–2 ሐዋ 26፡17–18/

## 7.1 የእግዚአብሔር የማዳኑ ዕቅድ

- ከምሕረቱ ባለጠግነት የተነሣ ለሰው ሁሉ አስቀድሞ የመዳንን መንገድ አዘጋጅቷል። /ዘ ፍ 3፡15፤ ኤፌ 1፡4፤ 2፡4–7/
- እግዚአብሔር በባሕርይው ፍቅር ስለሆነ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአል/ ዮሐ 3፡16/
- የሰውን ልጅ የኃጢአት ዕዳ በሞቱ እንዲከፍልና በደሙ ከአብ ጋር እንዲያስታርቅ አንዲያ ልጁን ወደ ዓለም ልኳል /1ዮሐ 4፡9–10፤ 2ቆሮ. 5፡19/

- ✓ እምነት የጸሎትን መልስ ይወስናል። /ያዕ 1፡6-8 ማር 11፡24/
- ✓ ያለ እምነት የሚቀርበውን መስዋዕት እግዚአብሔር አይቀበልም። /ዕብ 11፥4፤ መዝ. 147፡11/
- ✓ ያለ እምነት ድል ማድረግና መውረስ አይቻልም። /ዘኁ. 13፥30፤ 14፥4-9 1ዮሐ 5፥4/

## 8.3 የእምነት ዓይነት

1. <u>የማያድን እምነት</u>
   «እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ አንተ ታምናለህ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል» ፍሬ የሌለው እምነት ሊያድን አይችልም /ያዕ. 2፡14-26/

2. <u>የደኅንነት እምነት</u> «ጸጋው በእምነት አድኖአችኋል» /ኤፌ 2፡8-10 ሮሜ 10፡9/

3. <u>ትንሽ /ጎዶሎ/ እምነት</u>
   «እናንተ እምነት የጎደላችሁ...» ትንሽ እምነት ከእግዚአብሔር እጅ ለምንቀበለው ነገር ሁሉ እንቅፋት ነው።
   /ማቴ 6፡30-32፥ 14፡31፥ 8፡26፥ ማቴ. 17፡18-20/

4. <u>ትልቅ እምነት</u>
   «በዚያን ጊዜ ኢየሱስ መልሶ አንቺ ሴት እምነትሽ ታላቅ ነው እውነት እላችኋለሁ በእስራኤል እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም አላት።» ከሁሉ በላይ ግን ሚጹሕና ትልቅ እምነት ያለው ሰው የበለጠ እግዚአብሔን ደስ ያሰኛል።
   /1ጢሞ. 1፡5፥19 ገላ. 5፡6፥ 2ነገ. 3፡15-18/

5. <u>የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ የሆነ እምነት</u>
   የዚህ አይነት እምነት ለሁሉ አይሆንም። ይህም የክርስቶስ አካል የሆነችውን ቤተ ክርስቲያን ለማነጽ እና አንድን የተለየ ተግባር ለማከናወን የሚረዳ እምነት ሲሆን በአገልግሎታችንም የእግዚአብሔርን ተአምራዊ ሥራዎችን ለማየት ይጠቅማል። /1ቆሮ. 12፡9፥ 2ተሰ. 3፡2/
   እምነት በባሕርይው የሚያድግና በፍቅር የሚሠራ ነው። ስለዚህ እምነታችንን ለማሳደግ ሁሉ ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት/መመገብ/ ቃሉን በመታዘዝ ሲሆን እንዲሁም የእምነት ጠላት ከሆኑት ከፍርሃት፣ ከጥርጥር፣ ከአለማመን፣ ከኃጢአትና ከአለማወቅ ልባችንና መንፈሳችንን በመጠበቅ አለብን። /ያዕ 1፡6-8፤ ዕብ. 3፡12፥ 2ቆሮ. 5፡6፥/



## 8.4 የእምነት ውጤት

- እምነት በሕይወት ያኖራል /ዕብ 10፡37-39 2ቆሮ 5፥6-9፥ /
- እምነት ዕረፍትን፣ ሰላምን፣እርግጠኛነትንና ደስታን ይሰጠል። /ዕብ. 11፡1 ኢሳ 26፡3 ዮሐ 14፡1/
- እምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰማያዊና ምድራዊ በረከትና ስጦታን ያመጣል። /ማቴ 21፡21-22፤ ዮሐ 14፡12፥ ዕብ. 4፡16/
- እምነት ዓለምንና ጠላትን የምናሸንፍበት ኃይል ነው። /ዕብ 11፡32-34 ማቴ 21፡21 1ዮሐ 4፡5/
- እምነት የመሰጠትን ሕይወት ይሰጣል። /ገላ 2፥19-20፤ 1ሳሙ. 1፡27-28፤ ዘፍ. 22፡1-19/
- እምነት ከፉ ፍላጻዎችን የምናጠፋበት ጋሻ ነው። /ኤፌ 6፥16 1ጴጥ 5፥8-9 1ጢሞ 6፥12/
- እምነት ሕይወትን ያፀናል፤ በድፍረት ይሞላል። /መዝ. 118፡6-8፤ 125፡1፤ 112፡7-8 2ቆሮ 1፡24/

# ትምህርት 9 - ቅድስና

ቅድስና በዕብራይስጥ «ካዶሽ» /kadosh/ በግሪክ /Hagios/ ሲሆን ትርጉሙ ለእግዚአብሔር ክብርና አገልግሎት የተለየ ማለት ነው። ይህም አንድ ሰው ሥጋውን መንፈሱንና ነፍሱን ከሚያረክስ ኃጢአት በመራቅና በመለየት ራሱን ለአምላኩ ለእግዚአብሔር መቀደስ ማለት ሲሆን፡- ቅድስና ወይም መቀደስ የሚለው ቃል የሚከተሉት መሠረታዊ ትርጉሞች ይኖሩታል፡- ዘፀ 39:30

1. መለየት፡- ከኃጢአት፣ ከዓለምና ከሰይጣን ሥራ መራቅ /ዘሌ 20፥26 ኢሳ 52፥11 1ጴጥ 2፥11-12/
2. መውጣት ፡- ከማንኛውም ከፉ ነገር ጋር ያለውን ኅብረት መቁረጥ /መዝ 1፥1-6 2ቆሮ 6፥7/
3. መንጻት፡- ከኃጢአትና ከሚያረክስ ነገር ሁሉ በቃሉ ውሃ መታጠብና ንጹሕ መሆን /ዘጸ 30፡17-21፤ ሕዝ. 36፥25 /

4. መስጠት፡- ለእግዚአብሔር ራስን ሕያውና ቅዱስ መስዋዕት አድርጎ ማቅረብ /ሮሜ 12፥1-2/

### 9.1 የቅድስና ምንነት፡-

- ቅድስና የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው /1ጴጥ 1፡15፥ ገላ. 19፡2/
- ቅድስና ከእግዚአብሔር ባሕርያት አንዱ ነው /1ተሰ 4፡3 1ሳሙ 2፡2/
- ቅድስና ለእግዚአብሔር ክብር የሚሆን ነው /ዘጸ 28፡36/
- ቅድስና ለአንድ ዓላማና ግብ ለተለየ ሕይወት መሠረት ነው /2ዜና 29፡5/
- ቅድስና ከእግዚአብሔር የተሰጠ በረከትና ስጦታም ነው። /1ቆሮ. 6፡11/
- ቅድስና እግዚአብሔርን የመምሰል መንገድ ነው /1ጢሞ 4፡8 6፡6-7/
- ቅድስና በደህንነትና በጽድቅ መሠረት ላይ የታነጸ ዕድገት ያለው ሕይወት ነው። /1ዮሐ. 5፡18/
- ቅድስና ለእግዚአብሔር ተለይቶ የመኖር ሕይወት ነው። /መሳ. 13፡4-5፥ ኢሳ. 52፡11/

### 9.2 የቅድስና አስፈላጊነት

ለእግዚአብሔር ያለንን ፍርሃትና አክብሮት ለመግለጥ /2ቆሮ 6፡20 ዘጸ 19፡21-22 20፡18-20/
ክርስቶስን ለመምሰል /ሮሜ 8፡29-30 2ቆሮ 2፡14-16/

ለመንፈስ ቅዱስ ሥራ ምቹ ለመሆን /ሮሜ 8፡5 13-14 15፡15-16/
የእግዚአብሔርን ክብር ለማየት /ዕብ 12፡14 1ዮሐ 2፡28-29/
ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ኅብረት ለመጠበቅና ለማጠንከር /1ዮሐ 1፡6-10 ዘፍ 3፡8-10/

### 9.3 የቅድስና ደረጃዎች

1. የደኅንነት ቅድስና/Positional Sanctification or Holiness/ ምንም እንኳን ሥጋ ለባሾች ብንሆንም ጌታ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኛችን አድርገን በተቀበልን ጊዜ በተፈጸመ ፈጣን የመቀደስ ወይም መለየትና መንጻት ሂደት የደህንነት ቅድስና ተፈጽሟል።/1ቆሮ 6፡11 ዮሐ 17፡19 ዕብ. 10፡10 ቲቶ 3፥3-7/

2. የሚያድግ ቅድስና /Progressive sanctification /
   - በቅድስና ሕይወት መኖር /2ጴጥ 3፡17-18/
   - የቅድስናን ፍሬ ማፍራት /መዝ 132፡18/
   - ራስን ማንጻት /ይሁዳ 20-21 2ቆሮ 7፡1/
   - በእምነት ለጌታ መኖር /ገላ 2፥19-21/

3. ፍጹም የሆነ ቅድስና /Complete sanctification/ ይህ ዓይነቱ ቅድስና የሚገኘው ምድራዊ ከሆነው ሥጋዊ ሕይወት ተለይተን ሰማያዊ አካል በምንለብስበት ጊዜ ነው። /ዕብ 12፡23-24፥ 1ዮሐ 3፡2-3 1ተሰ 3፡12-13/

### 9.4 እንዴት እንቀደሳለን?

በእውነተኛ ንስሐ ወደ እግዚአብሔር ስንመለስ፡-

➢ እግዚአብሔር ራሱ ይቀድሰናል።

/ዘጸ 29፥43-44 ዘሌ 20፥8፥ 21፥8/

➢ ቃሉ ይቀድሰናል።

/ዮሐ 15፥3 17፥17-19 ኤፌ 5፥26፤ ሕዝ. 36፡25/

➢ መንፈስ ቅዱስ ይቀድሰናል /1ቆሮ 6፥11 2ተሰ 2፥13/

➢ የክርስቶስ ደም ይቀድሰናል/ዕብ 9፥14 13፥12 1 ዮሐ 1፥7/

### 9.5 የቅድስና በረከቶች

- የእግዚአብሔርን ክብር ማየት /መዝ 17፡15፥ 1ዮሐ. 3፡2-3/
- ከክርስቶስ ጋር የጠበቀ ሕብረትን መፍጠር /1ቆሮ 1፡7-9/
- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ለመቀበልና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር አብሮ መሥራት /1ቆሮ1፡7/
- የተስፋውን በረከት መውረስ /ኢያ 3፡5/
- የድል ሕይወት መኖር /ኢያ 7፡10-13/
- ውስጣዊ ሰላም፥ ዕረፍትና ደስታን ማግኘት /ሮሜ 14፥16-18፥ ፊል 4፥4-7/
- መንፈሳዊ ድፍረትን መሞላት። /2ቆሮ. 4፡2፤ 1፡12/
- መለኮታዊ ባሕርይ ተካፋይ መሆን /2ጴጥ. 1፡2-3/
- እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት ማትረፍ/1ጢሞ. 6፡6/

ቅድስና የሚያጠቃልለው የሰውን ሁለንተና /ሥጋ፤ ነፍስና መንፈስ/ እንዲሁም ኑሮውን ሁሉ ሲሆን እግዚአብሔር አምላካችን ቅዱስ በመሆኑ ለእርሱ የተለዩ ሰዎችም ሁሉ ቅዱሳን ሊሆኑ ይገባል። በክርስቶስ ሥራ አምነው የዳኑ ሁሉ በሕይወታቸው በቅድስና ሕይወት ያድጋሉ። በክርስቶስ ዳግም መምጣቱም ጊዜ ቅድስናቸው ፍጹም ይሆናል። /ዘሌ 19፥2፥ 1ተሰ 5፡23 1ጴጥ 1፡15-16፥ 2ቆሮ. 7፡1/

# ትምህርት 10 – ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ

## 10.1 መንፈስ ቅዱስ ሥራ በብሉይ ኪዳን ዘመን

- ➢ መንፈስ ቅዱስ ፈጣሪ ነው
  /ዘፍ 1፥2 መዝ 104፥30 ኢዮ 33፥4ኢሳ 40፥12–14/
- ➢ ነገሥታትን /የሕዝብ መሪዎችን/ ይቀባና በኃይል ይሞላባቸው ነበር።
  /1ሳሙ 16:13 ዘኁ 11:24–30 2ነገ 9:6 መሳ 6:34ዘጸ 18:15/
- ➢ አንዳንዶችን ለተለየ አገልግሎት በጥበብና በብልሃት ይሞላባቸው ነበር። /ዘፍ 41:38 ዘጸ 31:1–11/
- ➢ ስለ መሲህ መምጣትና ስለ አገልግሎቱ በነቢያት አፍ ተናገረ /ኢሳ 6:7 11:1–3 61:1–3/
- ➢ በነቢያት ላይ ይወርድ ነበር።
  /2ሳሙ 23:2 2ዜና 15:1–28/
- ➢ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ እንደሚወርድ በብሉይ ኪዳን የተነገረ ትንቢት ነው። /ኢዩ 2:28–32፣ ሐዋ. 2:17–21/

## 10.2 መንፈስ ቅዱስ ሥራ በአዲስ ኪዳን ዘመን

- ➢ ኢየሱስ ክርስቶስ በድንግል ማርያም ማሕጸን መጸነሱ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነበር። /ሉቃ1:30–35/
- ➢ የኢየሱስ የማስተማር ፣ የመስበክ፣ የመፈወስና አጋንንትን የማስወጣት አገልግሎት ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ ቅባት ነበር። /ሉቃ 3:16–19 ሐዋ 10:38 ማቴ 12:20/
- ➢ በሐዋርያት እጅ የተከናወነው አስደናቂ አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ነበር። /ሐዋ 2:43 ሮሜ 15:18–19/
- ➢ አማኞችን ለወንጌል አገልግሎት ይለያል፣ ይቀባል፣ ይልካል /ሐዋ 13:1–3 16:6–10/
- ➢ ለቤተክርስቲያን አገልጋዮችን መሪዎችንና እረኞችን ይሾማል /ኤፌ 4:11 ሐዋ 20:28/
- ➢ በክርስቶስ በኩል ለሚመጣው ትውልድ ሁሉ የተሰጠ ተስፋ ነው። /ዮሐ 7:37–39 ሐዋ 2:38–39/
- ➢ በአማኞች ውስጥ ሆኖ የመንፈስን ፍሬ እንዲያፈሩ ያደርጋል። /ዮሐ 14:16–17 1ቆሮ 6:19 ገላ 5:22/
- ➢ ለአማኞች የጸጋ ስጦታዎችን ያድላል። /1ቆሮ 12:4-11/

## 10.3 <u>የመንፈስ ቅዱስ ሥራ አስፈላጊነት</u>

- ▪ ያለ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንግሥት ምስጢር ማወቅ አንችልም/ሮሜ14:17 1ቆሮ 2:10–16 ሉቃ 17:21/



- ▪ ያለ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር እውነት ማወቅ ስለማይቻል /ዮሐ16:12 ማቴ 16:15–17/
- ▪ ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ከኃጢአት ነጻ መሆን ስለማይቻል /ሮሜ 8:2 6:14/
- ▪ ያለ መንፈስ ቅዱስ ለአገልግሎት ኃይል፣ ለቃሉና ለጸሎት ትጋት ሊኖረን አይችልም። /ሐዋ 1:8 6:4/
- ▪ ያለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል አጋንንትን መቃወምና ሥራውን ማፍረስ ስለ ማይቻል /ሐዋ. 19:13–16፥ ኤፌ.6 16–17/
- ▪ ያለ መንፈስ ቅዱስ ምሪት በእግዚአብሔር ፈቃድና ሐሳብ ውስጥ መኖርና መመላለስ አንችልም።
  /መዝ. 143:10 ሮሜ 8:12–14/
- ▪ ያለ መንፈስ ቅዱስ ነፍሳትን ለክርስቶስ መማረክ አንችልም /ዮሐ 16:8 ሐዋ2:37/
- ▪ ያለ መንፈስ ቅዱስ የማይነቃነቅ ጠንካራ መሠረት ያለው የእምነት ሕይወት ሊኖረን አይችልም /ኤፌ 3:16/

## 10.4 የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በደኅንነት ውስጥ

- ስለ ኃጢአት ይወቅሳል /ዮሐንስ 16፥8–11/
- ዳግም ልደት ይሰጣል /ዮሐ 3፥5 ቲቶ 3፥5 /
- በአማኙ ውስጥ ያድራል /ዮሐ 14፥17 1ቆሮ 6፥19/
- ያትማል /ኤፌ 1/13 ፥ 4፥30/
- ያጠምቃል /1ቆሮ 12፥13 ሐዋ 11፥15–17/
- የርስታችን መያዣ ነው /2ቆሮ 5፥5 1፥22 ኤፌ 1፥14/

## 10.5 የመንፈስ ቅዱስ ሥራና ባሕርይ ገላጭ ምሳሌዎች

- እሳት – የኃጢአትን ቆሻሻ ያቃጥላል ሕይወትን ያጠራል
  /ማቴ 3፥11–12 ሉቃ 3፥16 ሐዋ 2፥2–3/
- ዘይት/ቅባት – ይቀድሳል ለአገልግሎት ይቀባል ኃይልና ሥልጣን ይሰጣል።
  /ዘጸ 30፥25–30 1ሳሙ 16፥1፥11–13፥ 1ዮሐ 2፥20፥ 27/
- ነፋስ – ሕይወት ሰጪና ከሰው እውቀትና ቁጥጥር ውጭ በራሱ ፈቃድና ሐሳብ የሚሠራ መሆኑን ያሳያል።
  /ሕዝ 37፥9–10 ዮሐ 3፥8 ሐዋ 2፥1–2/

- ርግብ – የዋህነትና የሰላም ምሳሌ ናት ። ይህ የመንፈስ ቅዱስ ባሕርይ የኢየሱስም ባሕርይ ነው።

  /ዘፍ 8፥10–11 ማቴ 3፥16 10፥16/

- ማህተም – የሥልጣንና የበለቤትነት ማረጋገጫ ምልክት ነው። የመንፈስ ቅዱስ ማህተም ደህንነታችንና በክርስቶስ ደም የተገዛን የእግዚአብሔር ንብረት መሆናችንን ያረጋግጣል።

  /ኤፌ1፥13 4፥30 ሮሜ 8፥16፥ 1ቆሮ 6፥19–20/

- መያዣ – ወደ ፊት ለሚፈጸም ነገር አሁን የተሰጠ ቀብድ ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ሊሰጠን ላለው ርስት ውል መያዣ ነው። አማኙ በዚህ መያዣ አማካይነት ሰማያዊ ሕይወት ደስታ፣ ሰላምና ዕረፍት አሁን በዚህ ምድር ይለማመዳል፤ /2ቆሮ 1፥22 5፥5 ኤፌ 1፥14/

- ወይን ጠጅ – በወይን ጠጅ መስከርና በመንፈስ ቅዱስ መሞላት መካከል ያለውን ንጽጽር ምንነቱና ውጤት ተቃራኒ ሲሆን ተመሳሳይነቱ ወይን ጠጅም ሆነ መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ውስጥ በሙላት በሆነ ጊዜ ያን ሰው በራሱ ቁጥጥር ሥር የማድረግ ኃይል ስላለው ነው። መንፈስ ቅዱስ በወይን ጠጅ የተመሰለው። እንግዲህ በአጠቃላይ እነዚህ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌዎች ሁሉ የመንፈስ ቅዱስን ሥራና ባሕርይ የሚገልጡ ናቸው።

## 10.6 <u>የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት</u>

«ዮሐንስ በውሃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አለ።»

Baptism in the Holy Spirit " Clothes with power from on high" or immersing in full control of Holy Spirit.



➢ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

/ማቴ 3፥11 ማር 1፥8 ሉቃ 3፥16 ዮሐ 1፥33 ሐዋ 1፥5 ፤ 11፥16 ፤ 19፥1–7 1ቆሮ 12፥13 ገላ 3፥27 ኤፌ 4፥5 /

የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የማይጨበጥና የማይዳሰስ ሆኖ ነገር ግን አማኙን በእግዚአብሔር ኃይል ደስታና ሰላምን እየሞላ ውስጣዊ ማንነቱን ለውጦ የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርይና የጸጋ ስጦታዎች ተካፋይ እንዲሆን የሚያበቃ ቅጽበታዊ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። አንድ አማኝ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አማካይነት ከአዳማዊነት ባሕርይ ነጻ በመውጣትና በክርስቶስ አካል በመዋሄድ ዕለት ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየተሞላ የጌታን ዓላማ የሚፈጽም ይሆናል /2ጴጥ 1:3–9 1ቆሮ 12፥12–13 ዮሐ 15፥1–5/

- ከክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ተልዕኮና ዓላማ አንዱ ተከታዮችን በመንፈስ ቅዱስ ማጥመቅ ነበር።
  /ማቴ 3:11 ማር 1:8 ሉቃ 3:16፥ ዮሐ 1:33/

- የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከክርስቶስ ያገኘነውን ዳግም ልደትና ጽድቅ ፍጹም የሚያደርግ ወይም የሚያረጋግጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው ።
  /To complement the regenerating and sanctifying work of the Holy Sprit/

- የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ወንጌልን በፍጹም ግልጽነት ለመናገር የክርስቶስን አዳኝነት ለመመስከርና የእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ አደራ ለመወጣት ድፍረት፣ኃይልና ጥበብ የምናገኝበት ነው። ለዚህም ከበዓለ ሃምሳው መንፈስ ቅዱስ መውረድ በኋላ የሐዋርያው ጴጥሮስ አገልግሎት በቂ ምሳሌ ነው።
  ኢ.ሳ 61:1-3 ሐዋ 1:8 2:14–41 4:33 1ቆሮ 2:4–5
- በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ የልጅነት መብትና የእግዚአብሔር አብ ተስፋ ቃል ፍጻሜ ማረጋገጫ ነው።
  /ሉቃ 11:11–13 ሐዋ 1:4 11:16–17 ሮሜ 8:15 ገላ 4:6/

- በሐዋርያት ሥራ ላይ እንደምናየው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ውጫዊ መግለጫ ከሆነው በአዲስ ቋንቋ/ልሳን/ ከመናገር ጋር እጅግ የተቆራኘ ነው።

/External manifestation of speaking in toungue/

/ሐዋ 2:4 10:45–46 19:6 1ቆሮ 12–14/

ይህ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚሰጥ ልሳን ከተፈጥሮ ዕውቀትና ልምምድ ውጭ መለኮታዊ የሆነ ቅጽበታዊ ስጦታ ነው። ዓላማውም እግዚአብሔርን በመንፈስ ለማወደስ፣ ለማክበር፣ ለማምለክ፣ ምስጢርን ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገርና ራስን ለማነጽ ነው። /1ቆሮ 14:2 4 14 39 –40/

ስለዚህ ደህንነትና የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የሚነጣጠሉ አይደሉም። ምክንያቱም አንድ አማኝ በሕይወቱ የማያቋርጥ

መንፈሳዊ በረከት ለመለማመድ በፀጋ ተሞልቶ ጌታን ለማገልገልና በመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ክርስቶስን ወደ መምሰል ሕይወት ለመድረስ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና ሙላት ወሳኝ ነው። ስለዚህ ሰው በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ገብቶ የዘላለምን ሕይወት ካገኘ በየዕለት እንቅስቃሴው የእግዚአብሔርን ምሪት ሊያገኝ ይገባዋል። ለዚህም አማኞች ሁሉ በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅና በየዕለቱም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየተሞሉ በሕይወታቸው መለወጥ ማደግና በመንፈስ ፍሬ ተሞልተው መገኘት ይጠበቅባቸዋል።
/2ጴጥ 1፡1-11/

## 10.7 በመንፈስ ቅዱስ ለመጠመቅና ለመሞላት ምን ማድረግ አለብን?

- ንስሐ በመግባት በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን /ዳግም መወለድ /ሐዋ 2፡37-39/
- ጌታን በጸሎት መጠየቅ ወይም መለመን /ሉቃ 11፡13
- የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትም ሆነ ሙላት የሚፈልግ ሰው ከሁሉ በፊት ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኝበት በቂ ጊዜና ምቹ ሥፍራ እንዲኖረው ያስፈልገዋል። /ሐዋ. 1፥14 2፥1-41/
- መጠማት በንጹሕና በተከፈተ ልብ መቅረብ /ዮሐ 7፡37-39 ማቴ 5፡6 ኢሳ 41፡17 ሐዋ. 10፡44/
- በጌታና በተስፋ ቃሉ ማመን /ሉቃ 24፡49 ማር 11፡24፥ ሐዋ1፡4-5/
- ዕለት ዕለት ቃሉን መመገብና በቃሉ መሞላት /ሐዋ 10፡33 44 ቆላ 3፡16/
- መታዘዝ /ሐዋ 5፡32/

## 10.8 የመንፈስ ቅዱስ ሙላት

« መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ... »
/ኤፌ.5፥18-20፥ ሉቃ 4፡1-14፥ ሐዋ 4፡8-31 7፡55፥ 13፡9፥ 52 ኢሳ 40፥29-31፥ 2ቆሮ 4፥16/

ከቃሉ እንደምንረዳው፥ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ የሚከናወን ሲሆን የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ግን የሚቀጥልና የማያቋርጥ የየዕለት ልምምድ መሆኑ ነው። ይህም በየዕለቱ የሚገጥመንን መሰናከል ሁሉ አልፈን የእግዚአብሔርን ዓላማና ፈቃድ ለመፈጸም ኃይል የምናገኝበት መንገድ ነው። እንደ አስፈላጊነቱ መንፈስ ቅዱስ እየደጋገመ ለአምልኮ፣ ለአገልግሎት ለወንጌል ምስክርነትና ከሰይጣን ከዓለምና ከሥጋችን በየዕለቱ የሚገጥመንን መንፈሳዊ ውጊያ በአሸናፊነት እንዲንወጣ በኃይል ይሞላናል። እንዲሁም ይህ ሙላት ሕይወታችንና የየዕለት እንቅስቃሴያችን በመንፈስ ቅዱስ ምሪትና ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ይረዳል። ሐዋርያትም የከፉን ኃይላት ሥራ ኃጢአትንና ዓለምን



አሸንፎ ከጌታ የተቀበሉትን አገልግሎትና ሩጫ በድል የፈጸሙት በአንድ ጊዜ ጥምቀት ብቻ ሳይሆን ዕለት ዕለት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመሞላት ነበር።

## 10.9 ለመንፈስ ቅዱስ ሙላት እንቅፋት የሚሆኑ ነገሮች፡-

ከጌታ ጋር ትክክለኛ ሕብረት አለማድረግ ወይም በክርስቶስ ፍቅር አለመሞላት /ዮሐ. 15፡7፥ 9/
ንስሐ ያልገባንበት የተሰወረ ኃጢአት /መዝ. 19፡12-13/
በስህተት ትምህርት መያዝ /2ኛ ዮሐ 1፥9/
ለሌሎች ይቅርታ አለማድረግ ኃጢአት /ማር. 11፡25/
የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል በእምነት አለመቀበል /ያዕ. 1፡6-8/
በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ላይ የሚቀርብ ትችትና ነቀፋ።
/ሐዋ. 2፡13 1ኛ ቆሮ 12፥4-6/
ሬደላዊ ዕውቀትና ጥበብ /1ቆሮ 2፡14 2ቆሮ 3፡6/

## 10.10 በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሠራ ኃጢአት

- መሳደብ ይቅር የማይባል ኃጢአት /ማቴ 12፡31-36፥ ማር 3፡22-30/
- ማክፋፋት/ ዕብ 10፡29 1ዮሐ 5፡8/
- ማመጽ /ማስመረር/ ኢሳ 63፡10-11፤ ዕብ 3፡15-16/
- መቃወም /ሐዋ 7፡51 ሐዋ 6፡3 ዕብ 3፡19 ሮሜ 1፡24/
- መፈታተን /ሐዋ 5፡9 ዘዳ 6፡16 ማቴ 4፡7/
- ማሳዘን /ኤፌ 4፡30-31 /
- ማታለል /መዋሸት/ ሐዋ 5፡3-4/
- ማዳፈን /ማጥፋት / 1ተሰ 5፥19/

## 10.11 የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውጤት

- የኢየሱስን ክብር ይገልጣል/ ዮሐ 16፡14 ሐዋ 7፡55-56/
- አዲስ ራዕይ ይሰጣል /ሐዋ 2፡17 10፡9-48/
- ጽድቅን የሚፈልግና የሚጠግ፣ ኃጢአትን የሚኮንን ሕይወት ይሰጣል። /ሐዋ 16፡8 ሐዋ 5፡1-11 15 28-29/
- ለወንጌል ምስክርነትና ለአገልግሎት ኃይል ይሰጣል! /ሐዋ 1፡8፥ 4፡33፥ 11፡19-21/
- በመንፈስ እግዚአብሔርን ማምለክ፣ ምስጢርን ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገርና ራስን የማነጽ ሕይወት /1ቆሮ 14፡2 4 14 ኤፌ 5፡18-20/
- የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችንና የመንፈስ ፍሬዎችን በአማኞች ሕይወት መግለጽ /1ቆሮ 12፡4-11 ገላ 5፡22/
- ለጸሎትና ለምልጃ የሚተጋ ሕይወት ይሰጣል። /ሐዋ 2፡41-42 3፡1 ሮሜ 8፡26/

- ለእግዚአብሔር ቃል ጥማትና በቃሉም ጥልቅ መረዳትን ይሰጣል። / ዮሐ 16፡13 ሐዋ2፡42 17፡10-11/
- በኃጢአት፣ በዓለምና በክፉ ኃይላት ሥራ ሁሉ ላይ ሥልጣንና የማሸነፍ ኃይል ይሰጣል። /መሳ. 15፡13-15፤/
- የአገልግሎት ጸጋን ያነሳሳል /2ጢሞ 1፥6-7/
- ለሕይወት ተሐድሶና መነቃቃትን ይሰጣል /2ቆሮ 4፥16 መሳ 13፥25 ሮሜ 12፥11/
- አማኞች በመከራ ውስጥ እንዲጸኑ ጸጋውን ያበዛል /ሐዋ 7፥55 13፥50-52/

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ስለመንፈስ ቅዱስ ተጨማሪ ማብራሪያ በክፍል ሁለት ትምህርተ ሥላሴ ውስጥ ይመልከቱ።

## ትምህርት 11 - አምልኮ ጸሎትና መንፈሳዊ ውጊያ

### 11.1 <u>አምልኮ</u>

« ዕዝራም በሕዝቡ ሁሉ ላይ ከፍ ብሎ ሕዝቡ ሁሉ እያዩ መጽሐፉን ገለጠ በገለጠውም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ቆሙ ዕዝራም ታላቁን አምላክ እግዚአብሔርን ባረከ፡፡ ሕዝቡም ሁሉ እጃቸውን እየዘረጉ አሜን! አሜን! ብለው መለሱ። ራሳቸውንም አዘንበሉ በግንባራቸውም ተደፍተው ለእግዚአብሔር ሰገዱ።» /ነህ 8፥5-6/

#### ሀ/ የአምልኮ ትርጉም

አምልኮ የሚለው ቃል በዕብራይስጥ «አበድ» /Abad/ ተብሎ ሲጠራ በግሪክ «ላትሪያ» /Latreia/ ይባላል። ይህም ለአንድ ጌታ ብቻ የተገዛ ባሪያ ሊያቀርበው የሚገባ ፍጹምና ሁለንተናዊ አገልግሎት ማለት ነው። ስለዚህ ለእግዚአብሔር የሚቀርበው የቅዱሳን አምልኮ ስግደትን፣ ውዳሴን፣ ምስጋናን፣ አክብሮትን፣ ዝማሬን፣ መስዋዕትን በማቅረብ የሚገለጥ ሲሆን እግዚአብሔርን መስማት፣ መታዘዝ፤ካለን ነገር ሁሉ ለወንጌል አገልግሎት መስጠትና መልካም ሥራን ሁሉ መፈጸምን እንዲሁም በተሰጠና በተቀደሰ ሕይወት ለእግዚአብሔር ክብር መኖርን የሚያጠቃልል ነው። ይህም የተስተካከለ የሕይወት አቅጣጫ ሲሆን በሁለንተናዊ ሕይወትና ኑሮ ላይ እግዚአብሔርን ማንገሥ ማለት ነው። /መዝ 2፡6 5፡7 138፡2/

#### ለ. ለምን እናመልካለን?

- እግዚአብሔር አምላክ ስለሆነና አምልኮ ስለሚገባው ነው /ራዕ4፡9-11 ዮና 1፥8-9 ኢያሱ 24፥15 ዘዳ 6፡13-15/
- የተፈጠርነው እግዚአብሔርን ለማምለክ ነው /ፊል.2፡10-11 ራዕ 5፡13/



- ከዓለም ርኩሰት ተለይተን በክርስቶስ ደም የተቀደስነው እግዚአብሔርን ለማምለክ ነው። /ዕብ 9፡13-14 ኢያ 24፥21-22 ያዕ 1፥26-27፤ ዘዳ. 7፡6/
- ለእግዚአብሔር ሰው አምላኩን ማምለክ ሥራው ነው። /1ዜና 23፡30፥ ዮናስ 1፡8-9/
- አምልኮ ጠላትን ከምንዋጋበት መንገድ አንዱ ነው /2ዜና 20፥20-22 መዝ149፥6-9፤ 18፡3/
- አምልኮ ለእግዚአብሔር ያለንን መውደድ፣ መገዛትን መታዘዝንና አክብሮትን የምንገልጽበት መንገድ ነው /ዘዳ 13፡4 ኢያ 22፡5/
- አምልኮ ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣውን በረከትና ፈውስ ከምንቀበልበት መንገድ አንዱ ነው። /2ነገ 3፡15 ዘጸ 23፡25-26/
- ለእግዚአብሔር የሚገባውን መስዋዕት ማቅረብና እርሱን ደስ ለማሰኘት ነው። /ነህ 8፡8-10፤ 1ጴጥ. 2፡5፤ ዕብ. 12፡28/

#### ሐ. እንዴት ማምለክ እንዳለብን ማወቅ

- በእውነትና በመንፈስ፡
« ...እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል» /ዮሐ 4፡23-24፤ ራዕ 1፡10፤ ፊል 3፡3/
- ሁለንተናን ሕያውና ቅዱስ መስዋዕት አድርገን ለእግዚአብሔር በመስጠት፡
ከመስዋዕት ሁሉ ይልቅ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው በተሰጠና በተቀደሰ ሕይወት በትሕትና ወደ ፊቱ መቅረብ ነውና /ሚክ 6፥6-8 ሮሜ 12፡1-2፤/
  - በመዝሙር፣ በውዳሴና በመንፈሳዊ ቅኔ እግዚአብሔርን ማክበር /ኤፌ 5፡19-20 ቆላ 3፡16-17 መዝ 98፡4-9፤104፡33-34/
  - ለእግዚአብሔር የሚገባውን የምስጋና መስዋዕት መሰዋት /2ዜና 33፡16፤ መዝ. 50፡23፤ መዝ. 117፡1-2፤ዕብ. 13፡15፤/
  - በመስማት፣ በመታዘዝ፣ በመስጠትና በማካፈል ጌታ ከሰጠን ነገር ሁሉ ማለት ነው። /ያዕ 1፥27፤ ሉቃስ 21፡1-4፤ 8፡3/
  - በቅድስናና በንጹሕ ሕልና ማምለክ። /ኢያ 24፡19-24፤ ያዕ. 1፡26-27፤ 2ጢሞ 1፡3 ዘፍ 35፡2-3
  - እግዚአብሔርን እንደ አምላክነቱ መጠን አውቀንና ተረድተን ማምለክ፤/ኢያሱ 24፡14-18፤ 2ነገ. 17፡32-34፤ ዮሐ. 4፡22/
  - እግዚአብሔርን በመውደድ ከልብና ከነፍስ ፈቃድ ማምለክ /ዘዳ. 6፡4-5 1ዜና 28፡9፥ ኢያ. 24፡15፥ 22-24 ዘዳ. 11፡13/
  - በግልና በሕብረት ማምለክ ዘፍ 24፡26 1ዜና 29፡20

#### መ. የአምልኮ እንቅፋቶች

- የኃጢአት እሥራት ምሳ 5፡22
- ይቅርታ ሳይደራረጉ ወይም አንድ ልብ ሳይኖራቸው አብሮ ማምለክ /ማቴ 5፡23-26
- በአምልኮ ውስጥ የመንፈስ አንድነትን ማጣት

- ጸሎት እንቆቅልሽን ለመፍታትና ምስጢርን ለመግለጥ የጥበብ ቁልፍ ነው። /ዳን 2:17-23 2 ነገ 6:8-13/
- ጸሎት ከፈተናና ሊመጣ ካለው መከራ የማምለጫ መንገድ ነው /ሉቃ 21:36 መዝ 32:6/
- ጸሎት ለሰው ችግር ከእግዚአብሔር ዘንድ መፍትሔ ለማምጣት ነው /ኤር 42:2-4 ሐዋ 12÷5 እስ 4÷15-16/
- ጸሎት ለሰው ሕይወትና ኑሮ ሁለንተናዊ ፈውስን ያመጣል /2ዜና 7÷12-16 ያዕ 5÷14-16/
- ጸሎት ለመንፈሳዊ አገልግሎትና ውጊያ ኃይል ይሰጣል። /ሉቃስ 6:12-19÷ ሐዋ. 1:14፤ ሐዋ. 4:31/

ሐ/ የጸሎት ዓይነቶች /ፊል 4:6 ኤፌ 6:18 ቆላ 4:2-4/

1. <u>የንስሐ ጸሎት</u> /ማቴ 4:17÷ ሉቃስ 18:13 ሐዋ 17:30/

የእውነተኛ ንስሐ ባሕርያት፡-
- ከልቡ ይጸጸታል። /2ቆሮ 7:9-10/
- በደሉን ያውቃል /መዝ 51:3-4/
- በእግዚአብሔር ምሕረት ይታመናል /መዝ 51:1/
- ሕይወትን ይቀድሳል /መዝ 51:7 1ዮሐ 1:7-9/
- የንስሐ ፍሬ ይታይበታል። /ማቴ. 3:8÷ ሉቃ. 19:8/

2. <u>የልመና ጸሎት</u>
/1ዜና 4:10÷ ማቴ 7:7 ዮሐ 16:24 ሉቃ. 11:9-13÷ ያዕ 1:5-6/
ለልመናችን ከእግዚአብሔር የምናገኘው መልስ፡- ከእግዚአብሔር ፈቃድና ጊዜ ጋር የሚስማማ ከሆነ የእሺታ መልስ እናገኛለን። ነገር ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ጊዜው ካልደረሰ ቆይ /ታገስ/ የሚል ሲሆን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆነና የማይበጀን ከሆነ እምቢ የሚል ነው። ስለዚህ ለጸሎታችን መልስ ከእግዚአብሔር ዘንድ እስከምናገኝ ድረስ በትዕግሥትና በእምነት መጠበቅ አለብን። /1ዮሐ. 5:14-15÷ ዕንባ. 2:3÷ ያዕ 4:2-3/

3. የምልጃ ጸሎት /ሕዝ 22:30 1ዮሐ 5:16/

ለምልጃ ጸሎት ምሳሌ ከሆኑት ጥቂቶቹ፡-
አብርሃም- ዘፍ 18:22-32
ሙሴ - ዘጸ 32:32 ዘዳ 9:25-29
ሳሙኤል - 1ሳሙ 12:11-23



ነህምያ - ነህ 1÷4-11
ዳንኤል - ዳን 9÷1-23
ጌታ ኢየሱስ - ሉቃ 22:31-32 ፤ 23÷34
ሐዋርያው ጳውሎስ - ሮሜ 9÷1-3፤ 10÷1

4. የሥልጣን ጸሎት

እግዚአብሔር ሥልጣን የሰጠን እንድንጠቀምበት እንጂ ሁል ጊዜ በፊቱ እያለቀስን እንድንኖር አይደለም። ይህ የሥልጣን ጸሎት በክፉ ኃይላት ላይ፣ በበሽታ፣ በሚገጥመን ሁኔታና በሚያስፈልገን ነገር ሁሉ ላይ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመጸለይ /በማዘዝ/ የምንጠቀምበት ነው።
/ያዕ 5:17-18 4:7 ማቴ 12:29 መዝ 149÷6-9/

5. <u>የምስጋና ጸሎት /Thanksgiving/</u>

ይህ ጸሎት ስለተደረገልን ነገሮች ሁሉ እግዚአብሔርን ስለመልካም ሥራው የምናመሰግንበት ጸሎት ነው።
/ሉቃ 17:15-18 መዝ 103:2÷ መዝ 54:6-7/

6. <u>የአምልኮ ጸሎት /Praise or worship/</u>

እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በእውነትና በመንፈስ ሊሰግዱለት ይገባል» /ዮሐ 4:24/
ይህ ጸሎት እግዚአብሔር ስላደረገልን ነገር ብቻ ሳይሆን በምንም ሁኔታ ውስጥ ቢንሆን እንኳ እግዚአብሔርን ስለማንነቱ የምናመሰግንበት ጸሎት ነው።
መዝ 106:1-10፤ ኢዮ 1:21-22፤ ፊል 4:6፤ ዕንባ. 3:13-18/

7.<u>የመስጠት ጸሎት /Prayer of submission/</u>

ይህ ጸሎት ራስን ሙሉ ለሙሉ ለጌታ የመስጠት ጸሎት ነው። ይህ ጸሎት ከሌሎች የሚለይበት ነገር ቢኖር ሌሎች ጸሎቶች ለእግዚአብሔር የምናቀርባቸው መስዋዕቶችን ሲሆኑ በመስጠት ጸሎት ለእግዚአብሔር መስዋዕት አድርገን የምናቀርበው ራሳችንን በመሆኑ ነው። /ሮሜ 12:1 ሉቃ 22÷39-45 ሐዋ 20÷36-38/

መ. ጸሎት በሁለት መንገድ ይቀርባል /ራዕ 8:3-4/
1. የግል ጸሎት
የግል ጸሎት እያንዳንዱ አማኝ በወሰነው ሰዓትና ቦታ ብቻውን በመሆን ከእግዚአብሔር ጋር የሚነጋገርበት የጸሎት ልምምድ ወይም ዓይነት ነው። ነህ 1:4 ዳን 6:10 ሉቃ 2:36-38 ,6:11

2. የሕብረት ጸሎት

ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ አማኞች በአንድ ልብና በአንድ መንፈስ ሆነው ከላይ የተዘረዘሩ የጸሎት ዓይነቶችን ሁሉ በመስማማት የሚጸልዩበት የአንድነት ጸሎት ነው። የእግዚአብሔር ቃል አንዱ ሺ ሁለቱ አሥር ሺ ያሳድዳሉ ይላልና ብዙ ድል ለመቀዳጀት የኅብረት ጸሎት የበለጠ ኃይል አለው። /ዘዳ. 32:30 ሐዋ 4:24 ሐዋ 1:14,12;5

ሠ. ጸሎታችን እንዳይሰማ የሚያደርጉ ነገሮች

- ⇨ ኃጢአት /መዝ 66:18 ኢሳ 59:1-2 ኢያ 7:6-13/
- ⇨ እንደፈቃዱ አለመጸለይ /1ዮሐ 5:4-15 ያዕ 4:3/
- ⇨ የእምነት ማነስ /ያዕ 1:6-8/
- ⇨ ሳይስማሙ መጸለይ /ማቴ 18:19-20/
- ⇨ ለሌሎች ይቅርታ ሳያደርጉ መጸለይ /ማር 11:25-26/

ረ. የጸሎት ውጤት

- ➢ የእግዚአብሔርን ሰማያዊ አጀንዳ ይገልጣል /ዳን 9:20-27/
- ➢ ራዕይን ይሰጣል፥ ያሰፋል፤ /ሐዋ 10:9 13:1-3/
- ➢ የጠላትን ምሽግ፥ ዕቅዱንና ሥራውን ማፍረስ። /1ሳሙ 7:8-11 2ዜና 20:5-11 2ቆሮ 10:3-6/
- ➢ ሥጋዊና መንፈሳዊ ፈውስና በረከትን ያመጣል /ሉቃ 11:9-13 ያዕ 5:15 2ዜና 7:14/
- ➢ የሞትን አዋጅ ይሽራል። /አስ. 4:15-16 ሐዋ 12:1-11፤ ኤር. 33:1/
- ➢ በእግዚአብሔር የመታመንና የመመካትን ሕይወት ይሰጣል /ፊል 4፥6/
- ➢ ለመዝጋትና ለመክፈት የሥልጣን ቁልፍ ነው። /ማቴ 7-8 ያዕ 5:17-18/
- ➢ ሕይወትን ይለውጣል፤ ያንጻል ያሳድጋል። /ይሁዳ 1:20፤ 1ቆሮ. 14፤4/
- ➢ መንፈሳዊ ኃይል ያድሳል፤ መነቃቃትን ያመጣል። /ሐዋ. 4:31/

ጸሎታችንን ማቅረብ ያለብን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ፣ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣በመደገፍ በእምነትና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሊሆን ይገባል። /ዮሐ 15:16 16:24 ሮሜ 8:26 ማር 11:23 1ዮሐ5:14/ አንድ የእግዚአብሔር ሰው ሲናገር እንዲህ አለ። «እየሰበክ እያስተማርክና እየዘመርክ በመኖርህ ወደ መንግሥተ ሰማያት ትገባለህ ብዬ ለመናገር አልደፍርም ነገር ግን እየጸለይክና አምላክህን እየለመንክ ወደ ሲዖል ልትገባ እንደማትችል ላረጋግጥልህ እችላለሁ። ምክንያቱም እርሱ የሰዎችን ጩኸትና ልመና የሚሰማ ቸር አምላክ ነውና »



በጸሎት ሕይወት ፍሬያማ ለመሆን እምነት በተሞላ ሕይወት ባለመታከትንና በትጋት መጸለይን ይጠይቃል። ስለ ጸሎት የተሰጠን ትዕዛዝና ትምህርትም ይኸው ነው። /1ነገ 18፥41-46 ሉቃ 18፥1-7፥ ማቴ 26፥41 ቆላ 2፥4 1ተሰ 5፥17 ማር 13፥35-37/

11.3 መንፈሳዊ ውጊያ

መንፈሳዊ ውጊያ አማኝ ከሰይጣን፣ ከዓለም፤ ከኃጢአት ኃይልና ከራሱ ሥጋዊ ክፉ ምኞት ጋር የሚያካሂደው መንፈሳዊ ጦርነት ነው። ሰይጣን የጽድቅ ጠላት ስለሆነ በምድር ላይ በጽድቅ የሚመላለሱትንና የእግዚአብሔርን መንግሥት ሥራ ለማሰናከል የሚዋጋ የክፋት መንፈሳዊ ተቃዋሚ ነው። ይህ ውጊያ አማኞች በሥጋና በደም ኃይል የሚያካሂዱት አይደለም። «በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና» በእግዚአብሔር ዕውቀት ላይ በትዕቢት የሚነሣውን የሰውን ሀሳብ ሁሉ እናፈርሳለን። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና በሰማያዊ ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጅ። /2ቆሮ 10፥3-6 ኤፌ 6:10-12 ያዕ 4:7-8 1ጴጥ 5:8-9/

ሀ/ የሰይጣን ጠላትነት መቼ ተጀመረ?

የመጀመሪያ አፈጣጠሩ ለጠላትነት አልነበረም። ነገር ግን ከክብሩና ከውበቱ የተነሣ ልቡ ታበየና በእግዚአብሔር ላይ አመጸ በዚህ ምክንያት ከነሠራዊቱ ከሰማይ ተጣለ።ስለዚህ ሰይጣን ከውድቀቱ ማግስት ጀምሮ የጽድቅ ሁሉ ጠላት ሆነ። /ሕዝ 28:12-15፥ ኢሳ 14:12-15 ዘፍ 3:14-15/

ለ. የሰይጣን ውጊያ መንገዶች

1. በሀሳብ፦ ነገር ግን እባብ በተንኮል ሔዋንን እንዳሳታት ሐሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለውጥ ብዬ እፈራለሁ። ሰይጣን ክፉ መንፈስ ስለሆነ ሰውም በፍጥረቱ መንፈሳዊ ክፍል ስላለው ክፉን ሐሳብ ወደ ሰው አእምሮ ያስገባል፡ ያሳስታል። /ዘፍ. 3:1-5፥ 2ቆሮ 11:3-4 ዮሐ. 13:2/

2. በኃጢአት፡- የሥጋ ፈተና ኃጢአት ሲሆን ኃጢአት ደግሞ ሰውን ከእግዚአብሔር እንደሚለይ ሰይጣን ስለሚያውቅ አማኞችን ወደ ኃጢአት ይገፋፉቸዋል። /ዘፍ 3፡ 1ዮሐ. 3:4-5/

3. በክስ፦ ሰይጣን የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ቅዱሳንን ካሳተና ሳይስቱም ቢሆን ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት መክሰስ ዋና ተግባሩ ነው። /ኢዮ 1:6 ዘካ 3:1 ራዕ 12:10/

ስለዚህ ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ምሕረት ያልተረዳ አማኝ ከእግዚአብሔር ይቅርታን ካገኘ በኋላ

እንኳ ባለፈው ኃጢአቱ ራሱን እየከሰሰና እየኮነኔ በደካማነትና በውድቀት ስሜት ታስሮ እንዲኖር ያታልላል።
/ሮሜ 5:8 1ዮሐ 1:7 9፥ 21፥ ዕብ 2:17፤4:5 ሮሜ 8:1/

4. ሥጋን መውጋት፣ ፍላጻዎችን መላክና መከላከል /መቋቋም/ አማኞች የአምላካቸውን ተልዕኮ እንዳይወጡ ለማድረግ ነው። /2ቆሮ 12:7፣ ኤፌ 6:16 1ተሰ 2:18/

5. የዓለምን ክብርና ምድራዊ ጥቅም በማሳየት:-ይህም አማኞች ከእግዚአብሔር ፍቅር ይልቅ ለሥጋዊ ጥቅም ክብርና ሥልጣን ቅድሚያ በመስጠትና ዓለምን በመውደድ ካምላካቸው ጋር እንድጣሉ በማድረግ ነው::
/ማቴ 4፥8፥ 26:14–16 ዮሐ. 13:27 2ጢሞ 4፥9 1ዮሐ 2:15-17/

6. በስሕተት ትምህርት:–
የሰይጣን አንዱና ትልቁ መሣሪያ የስሕተት ትምህርት ነው ይህም በተለያየ መልኩ ሊገለጥ ይችላል።

- ሰው መንፈስ (አምላክ) መሆን ይችላል ብሎ ማስተማርና ማታለል።/ዘፍ. 3:4–5/
- የወንጌልን መልዕክት በማዳከም /በመሸቃቀጥ//2ቆሮ 2፥17
- የቤተክርስቲያንን ሕልውናና ከክርስቶስ የተሰጣትን ሥልጣን ለማስጣል ማጭበርበር
- አማኞችን ቀስ በቀስ ወደ አምልኮተ ባዕድ ለመምራት መሞከር /ዘጸ 32፥1፤ 1ሳሙ. 28:6፤ 1ነገ. 11:4–10/
- የክርስቶስን ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክነትን ባሕርይ መካድ /1ዮሐ 4፥2–3/
- የእግዚአብሔርን ሦስትነትና አንድነትን / ምስጢረ ሥላሴን / መካድ /1ዮሐ 2፥22–23/
- በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተገኘውን ደህንነት በሥርዓትና በሕግ ሥራ መተካት/ገላ5፥1–12/
- አማኞች ነቢያቶቻቸውንና መሪዎቻቸውን እንደ ክርስቶስ እንድያዩና እንዲያመልኩ በማድረግ /ሐዋ 5፥36–37፥ 16:16–24/
- በእግዚአብሔር ፍቅር ምህረትና ጸጋ ሽፋን አማኞች ከኃጢአት እንዳይለዩ ማድረግ /1ዮሐ 3፥6–9 2ጴጥ 2፥17–19 /
- መናፍስታዊ አሠራሮችን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ማስመሰል... ወዘተ /2ቆሮ 11፥13–15 ዘጸ 7፥10–11፥22 /

7. ለሰይጣን ፈቃድ የተገዙ ሰዎችን በመጠቀም በቅዱሳንና በእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ ላይ ለአመጽ ተግባር ወይም ለተቃውሞ መቀስቀስና ማሰለፍ::
/ሐዋ. 4:15–30፤ 16:16–24 .13:50/

ሐ/ አማኞች በመንፈሳዊ ውጊያ በድል አድራግነት መወጣት የሚችሉበት መንገዶች:–



- በጸሎት ኃይል የሰይጣንን ክፉ ሐሳብና ዕቅድ ፈጥኖ በመንቃትናበማፍረስ /2ቆሮ 2:11 ያዕ 4:7 1ዮሐ 3:8/
- ለእግዚአብሔር ፈቃድና ሐሳብ ራስን በመስጠት። /ሮሜ 12:1-2 ራዕ 12:11/
- በእግዚአብሔር ቃል በመሞላት። /ማቴ. 4:1–11/
- በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመሞላትና በመንፈስ ምሪት በመመላለስ /ሮሜ 8:5 2ሳሙ. 5:17–25/
- በቅድስና ሕይወት በመመላለስ ኃጢአት ለሰይጣን ትልቅ መሣሪያ ስለሆነ በኃጢአት ውስጥ ሆኖ መንፈሳዊ ውጊያ መዋጋት አይቻልም እግዚአብሔር ከኃጢአት ጋር ስለማይተባበርና አብሮም ስለማይወጣ ነው /ኢያ 7:1–10/
- አስፈላጊ የሆኑ መንፈሳዊ የጦር መሣሪያዎችን በመታጠቅ ወይም በመልበስና እግዚአብሔር የሰጠንን ሥልጣን በመጠቀም። /ኤፌ 6:10–18፤ 1ሳሙ. 17:39–49፤ መዝ. 149:6–9/

እንደ እግዚአብሔር ቃል በቅድስና ለሚመላለስ ክርስቲያን በሰይጣን ላይ የሚቀዳጀው ድል ዛሬ ከሁለት ሺ ዓመታት በፊት በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ተረጋግጧል፤ የእግዚአብሔር ቃል «የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል» ይላልና ደግሞም የዚህ ዓለም ገዥ ሰይጣን እንደተፈረደበት ይናገራል። ይህ ሁሉ የሚያሳየን አማኙ የተሰጠውን ሥልጣን ባለማወቅ ለሰይጣን በር ካልከፈተ በስተቀር ሰይጣን በአንድ አማኝ ሕይወት ምንም ሥልጣን የለውም:: ስለዚህ በክርስቶስ በኩል የእግዚአብሔር ልጅነት ሥልጣን ያገኘ አማኝ ሁሉ በየዕለቱ በጸሎት፣እየተጋ በእግዚአብሔር ቃልና በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እየተሞላ ይህንን ውጊያ ለመቋቋምና ለማሸነፍም ኃይልና ሥልጣን ተሰጥቶታል ሃሌ ሉያ!!
/1ዮሐ 4:4 ሮሜ 16:20 መዝ 149፥6–9/

## ትምህርት 12 – የአማኝ ሥልጣንና የአማኞች ኅብረት

### 12:1 – የአማኝ ሥልጣን

አንድ አማኝ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኝ አድርጎ በተቀበለበት ቅጽበት ከእግዚአብሔር የልጅነት ሥልጣን እንደተቀበለ የእግዚአብሔር ቃል ይናገራል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስምይህንን ሲያጸና «እነሆ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣንን ሰጥቻችኋለሁ የሚጎዳቸውም ምንም የለም»በማለት ለደቀመዝሙርት የሰጣቸው ሥልጣን ያረጋግጣል። /ዮሐ 1:12 ሉቃ 10:19/

### 12.2 የአማኝ ሥልጣን የሚገለጠው:–

1. በኢየሱስ ክርስቶስ ስም

ጌታ ኢየሱስ ይህንን ሥልጣን ከአብ ተቀብሎ ከመገለጡ በፊት የብሉይ ኪዳን አማኞች በጠላት ላይ የእግዚአብሔርን ስም ይጠሩና ድል ያደረጉ ነበር::
1ሳሙ 17:45 መዝ 118: 11-12 ዘዳ 4:24

ለ/ በአማኞች ኅብረት ውስጥ የሚከናወኑ ነገሮች፤–

- ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዘውን ያለማቋረጥ የሚፈሰውን የሕይወት በረከት መቀበል /መዝ 133፡1–3/
- የክርስቶስ ደቀመዛሙርት መሆናችንን ለሌሎች ማሳየት /ዮሐ. 13፡34–35/
- አንዱ ለሌላው የመኖር፥ የመደጋገፍና የመሸካከም ሕይወት ማወቀና መለማመድ። /ሐዋ 2፥44–45 ገላ. 6፥2 ፊል. 2፥4/
- ለፍቅርና ለመልካም ሥራ መነቃቃት /ዕብ 10፥24/
- በጠላት ላይ ብዙ ድል መቀዳጀት /ዘዳ 32፡30/
- ለአንድ ዓላማ በአንድ ልብና በአንድ ሐሳብ መስማማትና መነሣሣት ይኸውም ለወንጌል ሥራ ወይም የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋት ነው።። /ሉቃ. 10፡1–11፥ ሐዋ. 2፡46–47፥ 6፡7/
- በተለያየ ጸጋ ስጦታዎች አንዱን አካል ማነጽና ማሳደግ /1ቆሮ 12፡4–11 ሮሜ 12፡4–8 ኤፌ 4፡11–13/
- የጌታ መገኘት ወይም ከጌታ ጋር አብሮ መሥራት /ማቴ. 18፥19–20 ዮሐ.17፥9–11፥20–23/

ሐ/ ኅብረትን የማሳደግ መንገዶች

- ✓ በቅንነት መልካምና በጎ የሆነውን ማሰብና ማድረግ /ምሳ 4:27-28 ፊል 4:8-9/
- ✓ በጸሎት፣ መንፈሳዊና ሥጋዊ ማዕድ አብሮ በመካፈል /በመቁረስ/ ሐዋ 2፥42/
- ✓ በትህትና፣ በየዋህነት ፣ በትዕግሥትና በፍቅር በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት በመጠበቅ /ኤፌ 4፡2–3/
- ✓ በታማኝነት ምስጢርን መጠበቅና እርስ በርስ እውነትን መነጋገር ወሳኝ ነው /ምሳ 11:13 ኤፌ 4:25/
- ✓ በሐሳብ መስማማት በአንድ ልብና በአንድ መንፈስ መሆን /ፊል 2፥1–2 ሐዋ 4፥32/
- ✓ እርስ በርስ በመተያየትና፣ በመነቃቃት።። / ዕብ 10፡24–25/
- ✓ ሌላውን ከራስ ይልቅ የሚሻል አድርጎ በመቁጠር /ፊል 2፡3–8/
- ✓ አንዱ የሌላውን መከራ መካፈል 1ጴጥ 3:8/
- ✓ የደካሞችን ድካም መሸከምና ከራሳችን ይልቅ ባልንጀራችንን ደስ ማሰኘት /ሮሜ 15:1-3/
- ✓ ከወገናዊነት አሠራርና አመለካከት ነፃ በመሆን
- ✓ የራስን ጥቅምና ክብር ባለመፈለግ /በመተው/



መ/ የኅብረት እንቅፋቶች

- ኃጢአት /ዘፍ 3፡11–13/
- በጋራ ለጸሎትና ለቃሉ ጊዜ አለመስጠት /ሐዋ 2፥41–42/
- እርስ በርስ አለመከባበር /ትምክህተኛነት /ገላ 3፥28 ሮሜ 12፥9–10/
- የራስን ጥቅም ብቻ መፈለግ /ማር 10፡35–41/
- አንዱ የአካል ክፍል ሌላውን የአካል ክፍል ጥቅምና አስፈላጊነት አለማወቅ /1ቆሮ 12፡15–26/
- አንዱ ሌላውን አለመስማት፣ አለመታዘዝና ትሕትና ማጣት /ዮሐ13፥14/
- አድልዎዊ አገልግሎት መስጠት /ሐዋ 6፡1 ፊል 2፡3/
- የጠላት ወይም የሰይጣን የማለያየትና የማከፋፈል አሠራር /1ቆሮ1፥11–13 ፤ 11፥18/
- አንዱ ለሌላው የይቅርታና የምሕረት ልብ ማጣት /ማቴ 18፥21–22፤ 35/

የአማኞች ኅብረት ከሰብዓዊ ድርጅት ኅብረት የሚለይበት መንፈሳዊ፥ አንድ ልብ፣ አንድ ሐሳብ፣ አንድ መንፈስና ቅድስናን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው።። ይህም አንድነት የሚመጣው እያንዳንዱ አማኝ በግል ሕይወቱ የእግዚአብሔርን ዓላማ ሲያውቅና ስለመንፈሳዊ ኅብረት ትክክለኛ መረዳትና መስጠት ሲኖረው ብቻ ነው።። /ሮሜ 12:4-5 1ቆሮ 12:12-13 ፊል. 2፡1–2/

## የውይይት ጥያቄዎች

1. መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክና አምሳል ፈጠረው ይላል ሰውስ እግዚአብሔርን እንዴት ሊመስል ይችላል?
2. ኀጢአት በሰውና በፍጥረት ላይ ያመጣው ክፉ ውጤቶች ምንድ ናቸው?
3. መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው ይላል በምን እንዴት? (2 ቆሮ 5:17) ይመልከቱ
4. ሰው የደህንነት ጥሪ ሰምቶ በክርስቶስ የማመንና ያለማመን ፈቃድና ምርጫ አለውን ለምን?
5. በመዳንህ እርግጠኛ ነህን ምን ማረጋገጫ አለህ?
6. የመንፈስ ቅዱስን ኃይል የምንቀበለው እንዴትና መቼ ነው?
7. የአማኞች ኅብረት አስፈላጊነት፣ኅብረትን የማሳደግ መንገዶችና ለኅብረት እንቅፋት በሆኑ ነጥቦች ላይ ተወያዩ
8. ለሰው በኃጢአት መውደቅ ዋና ምክንያት የሆነው ሰው ራሱ ወይስ ሰይጣን?
9. ሞት የሚገባና ሞት የማይገባ ኃጢአት ዓይነቶች ምንድን ናቸው? (1ዮሐ 5:17 ሮሜ 1 :28-32)



# ምዕራፍ አምስት

## ቤተክርስቲያንና አገልግሎቷ

### ትምህርት 13 – ቤተክርስቲያን

#### 13. 1 ቤተክርስቲያን

ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል የተወሰደው «ኤክሊሽያ» ከሚለው ከግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም «ማህበር » «ጉባኤ» ማለት ነው። አማኞች በመጀመሪያ ጊዜ ቤት ለቤት፣ በት/ቤት፣ በወንዝ ዳርና በሚመቻቸው ስፍራ ሁሉ ለጸሎት ለአምልኮና ለቃለ እግዚአብሔር ትምህርት ይሰበሰቡ ነበር። በዚህ ኅብረት የሚታቀፉ ሁሉ የክርስቶስ ተከታዮች ስለሆኑ እግዚአብሔርን ለማምለክ ሲሰበሰቡ ቤተክርስቲያንን ይመሠርታሉ። ስለዚህ ቤተክርስቲያን ማለት ከዓለም ተጠርተው የወጡ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው የዳኑና እርሱን የሚያመልኩ አማኞች የተሰበሰቡበት ኅብረት ማለት ነው። /ሐዋ 16:13–15፤ 12:5፥12፤ 2:41–47 ሮሜ 16:5/

ሀ/የቤተክርስቲያን ሁለት መልክ ወይም ገጽታ፡–

1. የማትታይ /ዓለም አቀፋዊ /ቤተክርስቲያን
   በቤተ እምነት ፣ በአህጉራት እና በመልካዓ ምድር አቀማመጥ የማትለያይና የማትወሰን በክርስቶስ አምነው የዳኑ እውነተኛ ክርስቲያኖችን ብቻ ያቀፈች በሰው ዓይን የማትታይ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዓይን የምትታይ ዓለም አቀፋዊ ቤተክርስቲያን ናት። /2ኛ ጢሞ 2፥19 ሮሜ 10፥11–13 ራዕ 7፥9–10/

2. የምትታይ /አጥቢያ / ቤተክርስቲያን
   በየቤተ እምነቱ ስያሜ የምትጠራ በአህጉራትና በመልካዓ ምድር አቀማመጥ የተወሰነች የተለያየ መልክና መንፈሳዊ ሕይወት እድገት ደረጃ/ ያላቸውን አባላት ወይም መንጋ ያቀፈችና በምድር ላይ የክርስቶስ ተቋም ሆና የምትታይ አጥቢያ ቤተክርስቲያን ናት። ለዚህም ሰባቱ የእስያ አብያተክርስቲያናት ጥሩ ምሳሌ ናቸው።/ሐዋ 13፥1፤ 20፥17–28 ራዕ 1፥4–5፤ ሐዋ. 9:31/

ሰ. ቤተክርስቲያን የምትጠራባቸው ስሞች

- የክርስቶስ አካል /1ቆሮ 12፡12-27 ኤፌ 1፡23/
- የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ /1ቆሮ 3፥16-17 2ቆሮ 6፡16/
- የክርስቶስ ሙሽራ /2ቆሮ 11፡2 ራዕ 22፡17/
- የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን /ሐዋ 20፡28፥ 1ጢሞ 3፥5/

ሐ. ቤተክርስቲያን በምድር ላይ የመኖሩዋ ዓላማዎች
/ማቴ 28፥19-20 ማር 16፥15 ሉቃ 24፥48/

- የክርስቶስ ምስክር መሆን /የጠፉትን በወንጌል መድረስ/
- ያመኑትን ማጥመቅ
- ማስተማርና የክርስቶስ ደቀመዝሙር ማድረግ
- ለምድር ጨውና ብርሃን የሚሆን ተግባር ማከናወን /ማቴ 5-13/

መ. የክርስቶስና የቤተክርስቲያን ግንኙነት መልክ ምን ይመስላል?

- ራስና አካል /ኤፌ 1፡23 5፡23/
- ግንድና ቅርንጫፍ /ዮሐ 15፡1/
- አዛዥና ሠራዊት /2ጢሞ 2፡4/
- እረኛና መንጋ /ዮሐ 10፡16 ዕብ 13፡20/
- ባልና ሚስት /ሙሽራና ሙሽሪት ኤፌ 5፡31-32 ራዕ 19፡7/

ሠ. የቤተክርስቲያን ሥልጣንና ተግባሩዋ
/ማቴ 16፥17-19 18-18 ሉቃ 10፡19/

- እግዚአብሔርን ማምለክ /ዮሐ 4፥23-24 ዕብ 13፥15/
- ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ማዳረስ /ማር 16፥15 ሐዋ 1፥8/
- የምዕመናንን መንፈሳዊ ሕይወት በትምህርት፣ በምክር፣ በተግሳፅ ማሳደግና የክርስቶስ ደቀመዝሙርት ማድረግ። /ማቴ 28፥18-20 2ጴጥ 3፡18 2ጢሞ 3፥14-17/
- ለምዕመናን ሁለተናዊ አገልግሎት መስጠት። /ሐዋ 6፥1፥ ማቴ 14፥13-21 ገላ 2፥10/
- ምዕመናንን ከስህተት ትምህርት መጠበቅ። /ራዕ.2፥2 1ጢሞ 4፥1-2 ሐዋ 20፥28/
- በልዩ ልዩ ጸጋ ስጦታዎች ለተለያየ አገልግሎት የተቀቡትን ጥሪያቸውን በመለየት መሾምና ማሰማራት /ሐዋ 13፥1 ኤፌ 4፥11-13/
- ከጥፋታቸው ተገስፀውና ተምረው የማይመለሱትን አባላት ከምዕመናን ኅብረት ማገድ /1ቆሮ 5፥12 1ጢሞ 1፥19-20/
- በክፉ ኃይላትና አሠራራቸው ላይ እግዚአብሔር የሰጣትን ሰማያዊ ሥልጣንና ኃይል መጠቀም። /መዝ 149፡6-9 2ቆሮ 10፥3-6/



ረ. አማኞች የሚጠራባቸው ስሞች

- ቅዱሳን /ዕብ. 6፡10፤ ፊል 1፥1፤ ፍልሞ. 4/
- ወንድሞች /ሐዋ 9፥30/
- የተመረጠ ትውልድ /1ጴጥ.2፥9-10/
- የንጉሥ ካህናት
- ደቀመዝሙርት /ማቴ 28፥18-20 ሐዋ 9፥19/
- ክርስቲያኖች /ሐዋ 11፥26 1ጴጥ 4፥16/
- ምዕመናን /ኤፌ 1፥1/
- ማህበር /1ጴጥ 5፥3፤ ዕብ. 12፡23/
- የእግዚአብሔር ቤተሰብ/ልጆች/ ኤፌ 2፥19 ዮሐ 1፥12 ሮሜ 8፥14-17/
- የእግዚአብሔር መንጋ /በጎች/ ሐዋ 2፥28 ዮሐ 21፥15-17/
- ሕያዋን ድንጋዮች /1ጴጥ 2፥4-5/
- ቤተመቅደስ /2ቆሮ 6፡16/
- ጻድቃን/ሮሜ 3፡22፥ 5፡19፤ ማቴ. 25፡46/
- የእግዚአብሔር ሕንፃ፥ እርሻ /1ቆሮ 3፡16-17/

## 13.2 ወንጌልን ማዳረስ /Evangelism/

ሀ. ትርጉም

ቃሉ በግሪክ «ኡዋንጌሊዎን» ተብሎ ይጠራል። ትርጉሙ፡- መልካም ዜና ይዞ መምጣት ወይም የምሥራቹን ቃል ላልሰሙት ሁሉ ማብሰር ማለት ነው። ወንጌል ከኃጢአት፥ ከዓለም፣ ከሰይጣን ባርነትና እሥራት በክርስቶስ ነፃ የሚያወጣ መልዕክት ነው። /ኢሳ 52፡7 ናሆ 1፡15 ሮሜ 10፥15/

ወንጌል የብሉይ ኪዳንም ሆነ የአዲስ ኪዳን ቁልፍ መልዕክት ነው ። ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የምድራዊ አገልግሎት ጊዜውን ከመፈጸሙ በፊት ለቤተክርስቲያን ከሰጣት አደራ የመጀመሪያው ወንጌልን ማዳረስ ሲሆን ይህም የጠፉትን በምሥራቹ ወንጌል መድረስ ሥራ ነበር ። /ዘፍ 3፥15 ሉቃ 4፥17-19፤ ማር 16፥15-16/

ስለዚህ ወንጌልን ማዳረስ ዓላማ የሰው ልጅ ሁሉ ንስሐ በመግባት በኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት በማመን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲታረቅና በአማኞች ኅብረት በመታቀፍ ጌታን በማምለክና በማገልገል የክርስቶስ ደቀመዝሙር እንዲሆን ማድረግ ነው። /ሐዋ 17፡30-31 ፣ 2፥40-47 2ቆሮ 5፡18-19/

ለ. ወንጌል የተጠራባቸው ስሞች፡-

- የእግዚአብሔር ጸጋ ወንጌል /ሐዋ 20 : 24 1ተስ 2:8/
- የመንግሥቱ ወንጌል /ማቴ 24 : 14/
- የክርስቶስ ወንጌል /2ቆሮ 10 : 14 ፣4:4/
- የሰላም ወንጌል /ኤፌ 6 : 15/

- ራሱንና አገልግሎቱን ብቻ ከሌላው የተሻለ አድርጎ መቁጠር፤ ከዚህም የተነሣ በሌላው የመገልገል፥ የመመከር እና የመገሰፅ ልብና መንፈስ ማጣት።
- የወገናዊነት አመለካከት
- የራስን ጥቅም ዝናና ታዋቂነትን መፈለግ
- አንዱ የሌላውን ፀጋ አለማክበርና አለመቀበል
- የመንፈስ አንድነትና ፍቅር ማጣት
- ዕድገት ፍሬና በረከት ማጣት ይታይበታል

### ሠ. ለአገልግሎት የኃይል አስፈላጊነት

ለአገልግሎት መንፈሳዊ ኃይል ወይም ጉልበት ያስፈልጋል እግዚአብሔርም ለሚያገለግሉት ሁሉ ኃይልን ይሰጣል /1ጢሞ 1፥12/

- የእግዚአብሔር ቃል
  1ነገ 19፥3–8 ሕዝ 3፥1–4 ኤር 1፥9–10 ኤፌ 6፥17/
- መንፈስ ቅዱስ
  /ሐዋ 1፥8 ዘካ 4፥6 ሮሜ 1፥9–10 2ጢሞ 1፥7 /
- የእግዚአብሔር ጸጋ /2ቆሮ 12፥9 2ጢሞ 1፥6/
- እምነት /2ጢሞ 1፥5 ማቴ 14፥28–31፤ 21፥21–22 ዕብ 11፥32–34 /
- ጸሎት /ሐዋ 4፥31 ያዕ 5፥15–18 /

### ረ. በአገልግሎት ፍሬ የማጣት ምክንያቶች፦

- በኢየሱስና በቃሉ አለመኖር /ዮሐ 15፥4–8/
- ከመንፈስ ሳይሆን ከሥጋ መዝራት /ገላ 6፥8/
- የእግዚአብሔርን ሐሳብና ፈቃድ አለማገልገል
  /ማቴ 7፥21–23/
- የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ማጣት /ዮሐ 21፥4–6 ሉቃ 5፥1–8 ሐዋ 16፥6–10/
- በተሰጠው ጸጋ ስጦታ አለማገልገል
- አገልግሎት የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ከፍሎ አለማገልገል
  /ዮሐ 12፥4–25 መዝ 126፥5–6 2ጢሞ3፥10–12/
- በእምነትና በታማኝነት አለማገልገል /ማቴ 25፥24/

### 13.6 በመስጠት ማገልገል /ዘጸ. 16፥16–17/

<u>መስጠት፦</u>

ከመስጠት ዓይነት ሁሉ መቅደም ያለበት የሕይወት መስጠት ነው። እግዚአብሔር አስቀድሞ የሚፈልገው ለእርሱ የምናቀርበውን ስጦታችንን ወይም መስዋዕታችንን ሳይሆን ሕይወታችን ነው። ከሁሉ በላይ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ስጦታም ይህ ነው። የሕይወት መስጠት። ስለዚህ ነው እግዚአብሔር ልጅ ሆይ ልብህን ስጠኝ ዓይኖችህም መንገዴን ይውደዱ ብሎ የሚጠይቀን፡፡

<u>« አሁንም አምላካችሁን እግዚአብሔርን ትፈልጉ ዘንድ ልባችሁንና ነፍሳችሁን ስጡ</u>፡ ለእግዚአብሔርም ስም ወደ



ሚሠራው ቤት የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳኑን ታቦትና <u>የእግዚአብሔርን ንዋይ ቅድሳት</u> <u>ታመጡ ዘንድ...»</u> /1ዜና 22:19/ /ሚክ 6፥6–8 ሮሜ 12፥1–2፥ 1ዜና 6፥48፥ 2ቆሮ. 8፥4–5 ምሳ23:26/

### ሀ/ <u>የመስጠት መንገዶች፦</u>

- አሥራት ከማንኛውም ገቢ ከአሥር አንድ እጅ ማለት ነው።
  /ዘፍ 14፥20 28፥22 ሚል 3፥8 ዘሌ 27፥30 ነህ 13፥12/
- መባ (በኩራት)
  /ዘጸ 13፥1 25፥1–6 ዘሌ 27፥30 ሉቃ 22፥23፥ ዘዳ. 26፥1–2/
- ስዕለት /1ሳሙ 1፥11 ዘፍ 28፥20–22 ምሳ 20፥25 ዘፀ. 35፥24፥ ዘዳ 12፥26፥ ዘዳ 23፥21/
- የመስዋዕትነት ስጦታ ከትርፍ ሳይሆን ከጉድለት ጨርሶ የሚሰጥ ስጦታ ነው /ማር 12፥41–44/
- ልግስና፦ ሌሎችን በሚያስፈልጋቸው ሁሉ ለመርዳት የሚሰጥ ስጦታ /መዝ 41፥1 ሮሜ 12፥8 ያዕ 1፥27 ምሳ 19፥17–18/
- ለወንጌል አገልግሎት የሚሰጥ ስጦታ
  /2ቆሮ 9፥6–14 ሉቃ 8፥3/

### ለ/ <u>እንዴት መስጠት እንዳለብን ማወቅ</u>

እግዚአብሔር ከሰጠን በረከት መልሰን ለእግዚአብሔር መስጠት የቃሉ ትዕዛዝ ስለሆነ ለወንጌል ሥርጭትና ለሌሎችም ጥቅም በጌታ ስም ያደረግነው ልግስና ሁሉ ለጌታ እንዳደረግንና እርሱን እንዳገለገልን በማመን ለቃሉ በመታዘዝና ለእግዚአብሔርም ያለን አክብሮትና ፍቅር በመግለጥ በደስታ ሊሆን ይገባል። መስጠት የእምነት ፍሬ ወይም እምነትን በሥራ የመግለጥ/ የማሳየት መንገድ ነው፡፡/ምሳ 3፥9–10 ሚል 1፥6–8 ያዕ 2:14-26/

### ሐ/ <u>ስለመስጠት የቃሉ መመሪያ፦</u>

- በሐዘን ሳይሆን በደስታ መስጠት /ዘዳ. 15፥10/
- ለታይታና ለመታበይ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብር እየሰጠን በትህትና መስጠት
- በልብ እንደታሰበ መጠን መስጠት /ዘጸ 35፥21/
- በስስት ሳይሆን በቸርነትና በልግስና መስጠት
- በግዴታ ሳይሆን በታዛዥነትና በፍቅር መስጠት
- በፍቅርና በእምነት መስጠት
  /2ቆሮ 9፥6–14 8፥1–15 1ዜና 29፥1–17 ዘጸ 35፥4–9/

### መ/ <u>በመስጠት የሚመጣ በረከት</u>

- ለእግዚአብሔር መስጠት መታዘዝ ስለሆነ እግዚአብሔር የሚታዘዙትን ለመባረክ የገባውን ቃል ኪዳን ይፈጽማል /ዘዳ 28፥12፥ ዘዳ. 14፥28–29/
- በሕይወት በኑሮና በአገልግሎት ፍሬ አልባ የሚያደርግ መርገም ይወገዳል /ዘዳ 28፥38–40/

- ብጽዕና ያስገኛል «ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው» ይላልና /ሐዋ 20፥35/
- በሰማይ ሀብት (ሽልማት) ይጠብቃል /ማቴ 6፥19–21/
- የተትረፈረፈ የኑሮ በረከት /ሚል 3፥10–12 ፊል 4፥15–19፡ሉቃ. 6:38/
- የምንቀበለው በረከትና የሚጠብቀን ሽልማት የሚለካው በልግስናችን መጠን ነው /2ቆሮ 9:6/

ሠ/ የአገልግሎትን ዋጋ /ሽልማት/የሚያሳጡ ነገሮች /2ዮሐ 1፥8/

- የአገልግሎትን ዓላማ መሳት /የእግዚአብሔርን ትዕዛዝና ፈቃዱን አለመፈጸም ማለት ነው /1ሳሙ 15:9-15 ዮሐ 20:20-23/
- ከሥጋ መዝራት /1ቆሮ 3፥12–15 ገላ 6፡7/
- ከኃጢአት እሥራት ነፃ ሳይወጡ ማገልገል /2ቆሮ 4:1–2/
- ያለ ፍቅር ማገልገል / 1ቆሮ 13፥1–3/
- ታማኝነት ማጣት /ማቴ 25፥27–30/
- ለታይታ ፣ ለክብር ፍለጋና ለሥጋዊ ጥቅም ማገልገል /ማቴ 6፥2–4 23:5/
- አገልግሎትን ጀምሮ አለመፈጸም /ሉቃ14፥28–30 ቆላ 4፥17 2ጢሞ 4:5 7–8/
- በአገልግሎት ውጤት መታበይ /ሉቃ 17:7–10/
- አድልዎዊ አገልግሎት መስጠት /ፊል 2፥3 1ጢሞ 5፥21፥ ሐዋ. 6:1/

ረ/ ጌታን የማገልገል ውጤት

- ✝ ትዕዛዙንና ፈቃዱን በመፈጸማችን ከእግዚአብሔር ዘንድ የምንቀበለውን ሞገስ፥ ምሥጋናና የመንግሥቱ ወራሾች መሆን /ማቴ. 25:34–40/
- ✝ በመንፈሳዊ ሕይወት ማደግና መታነጽ /1ሳሙ 3፥1፥ 19–21/
- ✝ የእግዚአብሔርን ክብር ማየት /ሉቃ 1፥8–12/
- ✝ ከክፉ መጠበቅ /መዝ 105፥14–15 ,89፥19–23
- ✝ በሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወት መባረክ /1ቆሮ 9:3–12/
- ✝ በእግዚአብሔር መንግሥት ደመወዝ፣ ክብር፣ ሽልማትና ሹመት መቀበል /ማቴ 10:42 ዕብ 6:10 ሉቃ 12፥37/
- ✝ ለሕይወት ደስታንና ተድላን ይሰጣል። /ኢዮ 36፥11/
- ✝ በጌታ መገልገልና መከበር /ሉቃ 12፥37፤ ዮሐ 12፥26/

እንግዲህ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስና ከቅዱሳን አባቶቻችን ሕይወትና አገልግሎት እንደተማርነው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መስዋዕት ወይም አገልግሎት የሕይወት መሰጠት፣ ፍቅር፣ ትህትና፣ ቅንነት፣ ታማኝነትና ቅድስና ያለበት ነው። ስለዚህ



በዚህ ሕይወት እየተመላለስን የእግዚአብሔርን ፈቃድና ሐሳብ በማገልገል እርሱን ደስ እያሰኘን በጌታ የጀመርነውን አገልግሎት በእርሱ ፈጽመን ለሽልማት እንድንበቃ ጌታ በመንፈሱና በጸጋው ይርዳን አሜን።
/2ዜና 29:11፥ ሐዋ 13፥36 ቆላ4፥17 1ቆሮ 15፥58፥ 2ጢሞ 4፥6–8/

## ትምህርት 14 – የውሃ ጥምቀት

### 14.1 የጥምቀት ትርጉም

ጥምቀት «ባፕቲዞ» ከሚባለው ከግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉሙ አንድ ሰው በውሃ ውስጥ ተዘፍቆ/ተነክሮ/ መውጣትን ያመለክታል። ይህ ሥርዓት በብሉይ ኪዳን የልዩ ልዩ መታጠብና መርጨት የሚፈጸመውን የመንጻትና እንዲሁም የመገረዝ ሥርዓቶችን የሚያመለክት ነው።/ዕብ 9፥10 ዘፍ 17፥9–14 ፤ 23–27/ የውሃ ጥምቀት ትምህርትና ሥርዓት የተጀመረው ከብሉይ ኪዳን ወደ አዲስ ኪዳን መሸጋገሪያ ዘመን ላይ በመጥመቁ ዮሐንስ አገልግሎት ነው። ይህንንም የቤተክርስቲያን ራስ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በዮሐንስ እጅ በመጠመቅ የፈጸመውና ለቤተክርስቲያንም ከሰጣት ቅዱስ ሥርዓቶች አንዱ ነው። ይህም የድል አዋጅ መግለጫ የሆነ የበረከት ሥርዓት ነው።
/ማቴ 3:13–17፥ 28:18/

### 14.2 ስለ ጥምቀት ሁለት የተዛቡ አመለካከቶች፡–

- ያለ ጥምቀት አንድ ሰው መዳን አይችልም የሚል የተሳሳተ እምነትና ትምህርት
- ኢየሱስ ክርስቶስ «ጽድቅ» ብሎ የጠራውን የጥምቀት ሥርዓት እንደተራ ነገር መቁጠር ናቸው። /ማቴ. 3:15/

### 14.3 መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

- «በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው...» /ማቴ 28:19–20/
- «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» /ማር 16፥16/
- «ኃጢአታችሁ ይሰረይ ዘንድ ንስሐ ግቡ በኢየሱስ ስም ተጠመቁ» /ሐዋ 2፥38/
- «. . ተነሣና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትም ታጠብ /ሐዋ 22:16/
- «ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና» /ገላ 3፥27/
- «እንደምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን» /ቲቶ 3፥5/

- «ይህም ውሃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል የሰውነትን ዕድፍ ማስወገድ አይደለም። ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነው እንጂ» /1ጴጥ 3፥21/

## 14.4 የጥምቀት አስፈላጊነት

- ኢየሱስ ክርስቶስ በሕይወቱ የውሃ ጥምቀትን በመፈጸም ለቤተክርስቲያን ምሳሌ ሆኖአል የውሃ ጥምቀት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተ አንድ ክርስቲያን ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጋር መተባበሩን የሚያሳይና ቤተ ክርስቲያንም ከምትፈጽማቸው ቅዱስ ሥርዓቶች አንዱ ነው። /ማር 1፥9-11 ሉቃ2፥21-22፥ ሮሜ 6፥3-5 ማቴ3፥13-17/
- የውሃ ጥምቀት የክርስቶስን ትዕዛዝና ቤተክርስቲያንን በመታዘዝ የሚፈጸም ከጽድቅ ተግባር አንዱ ነው። /ማቴ 3፥15 28፥19/
- የውሃ ጥምቀት አንድ አማኝ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ስለመዳኑ ማረጋገጫ ምልክት ወይም ምስክርነት ነው። በራሱ ግን የሚያድን አይደለም። /ገላ 3፥27 ቆላ 2፥12/
- የውሃ ጥምቀት ጥቅም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ለዳኑ ነፍሳት ብቻ ነው። /ሐዋ 2፥38-41/
- የውሃ ጥምቀት እንደ ክርስቶስ ትዕዛዝ በጥልቅ ውሃ ውስጥ በማጥለቅ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም ይፈጸማል። /ማቴ 28፥19 /

## 14.5 የጥምቀት ዋና ዋና ሐሳቦች የሚከተሉት ናቸው፦

- መንጻት - ማር 1፥4
- መለወጥ - ማር 1፥4-8
- መተባበር የሚሉ ናቸው - 1ቆሮ 1፥13



## 14.5 የጥምቀት ዓይነቶች

| የጥምቀት ዓይነት | አጥማቂው | በምን? | ለምን? | የቃሉ መሠረት |
|---|---|---|---|---|
| አንዲት ጥምቀት | መንፈስ ቅዱስ | በክርስቶስ አካል | ለደህንነት /አዲስ ፍጥረት/ መሆን | 1ቆሮ 12፥13<br>ገላ 3፥26-27<br>ኤፍ 4፥4-5<br>2ቆሮ 5፥17 |
| የመጥመቁ ዮሐንስ ጥምቀት | መጥመቁ ዮሐንስ | በውሃ | ለንስሐ | ሉቃ 3፥3 |
| የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት | ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ | በመንፈስ ቅዱስ | ለደኅንነት፣ ኃይልን ለመቀበልና የክርስቶስ ምስክር ለመሆን | ሐዋ 1፥5 8<br>ማቴ. 3፥11<br>ሉቃስ 24፥49 |
| የውሃ ጥምቀት | ቤተክርስቲያን | በውሃ | በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ለመተባበር | ማቴ 28፥19<br>ማር 16፥16 |
| የመከራ ጥምቀት | ዓለምና ጠላት | በመከራ | የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወታችን እንዲፈጸም | ሉቃ 12፥50<br>ማቴ 20፥22<br>ሉቃ 22፥42<br>1ጴጥ. 4፥19 |

## 14.7 የጥምቀት ጥቅም

- የጌታን ሞትና ትንሣኤ ማወጅ ወይም መመስከር።
- አዳማዊነትን አሽንፈን በአዲስ ሕይወት ለመመላለስ የመወሰናችን ማረጋገጫ ነው።
- ከክርስቶስ ጋር ለጽድቅ ሥራ ሁሉ የታዛዥነት መግለጫ ነው።
- ከሞት፣ ከሰይጣን፣ ከኃጢአትና ከዓለም ባርነት ነፃ መውጣታችን አዋጅ ነው።

/ሉቃ 12፥50 ሮሜ 6፥3-4 ቆላ 2፥12/

# ትምህርት 15 – የጌታ እራት

## 15.1 መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ምድር በሚያወጣበት ሌሊት እያንዳንዱ እስራኤላዊ ነውር የሌለበት የበግ ወይም የፍየል ጠቦት አርዶ ደሙን በጉበኑ ላይ እንዲቀባና ሥጋውን ጠብሰው እርሾ ከሌለበት ቂጣ ጋር እንዲበሉ አዘዛቸው፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ፋሲካ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን እስራኤላውያን ከሚያከብሩት ታላላቅ በዓላት አንዱ ሆኖ ለልጅ ልጆቻቸው የተሰጠ ሥርዓት ነው፡፡
- ደሙ የምሕረት ምልክት ነው፡፡ ምክንያቱም የግብፃውያንን በኩር ይመታ ዘንድ የእግዚአብሔር ቁጣ ሆኖ የተላከው የሞት መልአክ የደሙ ምልክት ያለበትን ቤት ሁሉ አለፈ፡፡ ስለዚህም ፋሲካ ማለት አለፈ ማለት ነው፡፡
  /ዘጸ. 12፥3–28 ዘሌ. 23፥4–8፥ ዘኁ. 28፥16–25 ዘዳ. 16፥1–8/
- ይህ በአዲስ ኪዳን የፋሲካ በግ ሆኖ ለሰው ልጅ ኃጢአት ራሱን አሳልፎ የሰጠውን ክርስቶስን የሚያመለክት ነው፡፡
  /ዮሐ. 1፥29 1ቆሮ 5፥7–8 ዕብ. 9፥11–14/
- የጌታ እራት በመጀመሪያ የተደረገው ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት ሌሊት ሲሆን የሥጋውና የደሙ ምሳሌ የሆነው ኅብስትና ፅዋው የጌታ እራት፣ ቅዱስ ቁርባን ወይም እንጀራ መቁረስ ተብሎም ይጠራል፡፡ ይህ ሥርዓት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተክርስቲያን ከሰጣት ቅዱስ ሥርዓቶች አንዱ ሲሆን ጌታ ዳግም እስኪመጣ ድረስ አማኞች ሁሉ ቤተክርስቲያን በወሰነችው ጊዜ እየተሰባሰቡ የጌታን ሞትና ትንሣኤ በማሰብ በሕብረት ሊካፈሉትና ሊያከብሩት የሚገባ ሥርዓት ነው፡፡
  /ማር 14፥22–24 ማቴ.26፥26–29 1ቆሮ.11፥23–30/

ሀ. ኅብስቱ/ሥጋው /

«ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን እንስቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀመዛሙርቱ ሰጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው» አላቸው፡፡

- ሥጋው ስለ ሰው ልጅ ኃጢአት አንድ ጊዜ ፍጹም መስዋዕት ሆኖ ቀረበ፡፡ /ዕብ.10፥10/
- በሥጋው ኃጢአታችንን ተሸከመ፡፡ /1ጴጥ 2፥24–25/
- ሥጋው በመገረፉ ቁስል እኛ ተፈወስን። /ኢሳ. 53፥4–5/
- በሥጋው የእሾህ አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ አደረጉለት፣ ዘበቱበት፣ ተፉበት ራሱንም በመቃ መቱት።
  /ማቴ 27፥28–31 ማር 15፥17–20/
- ሥጋው በጦር ተወጋ፣ ደምና ውሃም ወጣ። /ዮሐ 19፥34/
- ሥጋው ራቁትን ተሰቀለ ከ6–9 ሰዓት በመስቀል ላይ ዋለ
  /ማቴ 27፥45፣ ማር 15፥20/



- ሥጋው ለሦስት ቀን በምድር ሆድ አደረ በሦስተኛውም ቀን የትንሣኤን አካል ይዞ ተነሣ /ማቴ 27፥54/

ለ. ጽዋው /ደሙ/

- ጽዋውንም አንስቶ አመስግኖ ሰጣቸው እንዲህ አለ። ሁላችሁ «ከእርሱ ጠጡ ስለብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው» አላቸው፡፡/ማቴ 26፥27–28/
- ደሙ ለአዲስ ኪዳን የተሰጠ ምልክት ነው
- «ጎኑን በጦር ወጋው ወዲያውም ደምና ውሃ ወጣ።»
  /ዮሐ 19፥34/
- የኃጢአት ይቅርታ/ሥርየት/ የተገኘው በክርስቶስ ደም ብቻ ነው፡፡ «የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነፃናል» /ዕብ 9፥11–14 1ዮሐ 1፥7/

## 15.2 የጌታ እራት የመከፈል አስፈላጊነት

- ጌታ ያደረገልንን ውለታ ለማሰብ /1ቆሮ 11፥25 /
- ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱንና ትንሣኤውን ለሌሎች ለማወጅ/ለመናገር /1ቆሮ 11፥26/
- ራሳችን ለመፈተንና በንስሐ ለመታደስ /1ቆሮ 11፥28–32/
- ለጌታ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያለንን ታዛዥነት፣ ፍቅርና እምነት ለመግለጽ ነው። /ዮሐ 6፥60–69/
- በእርሱ የዘላለም ሕይወት እንዳለን ማረጋገጫ ስለሆነ /ዮሐ 6፥51–58/
- የጌታን ትዕዛዝ ለመፈጸም /ማቴ 26፥26/
- የክርስቶስ የፍቅሩን ጥልቀትና ስፋት መጠን ለማሰብ /ኤፌ 3፥18/

## 15.3 የጌታ እራት የመካፈል ጥቅም

- የጌታን ሞትና ትንሣኤ ለመመስከር የሚያስችለን መታሰቢያ ብርታት ይሰጣል፡፡
- ከክርስቶስና ከወገኖች ጋር ያለንን ኅብረት ያድሳል
  /1ቆሮ 10፥16–17
- ሥጋውንና ደሙን እያሰብን ራሳችንን በቅድስና እንድንጠብቅ ይረዳናል፡፡
- የአዲስ ኪዳንን በረከት ለሌሎች ለማስተላለፍ
  /1ቆሮ 10፥6 ማቴ 26፥26/
- የጌታ ሞቱንና ትንሣኤውን ለማሰብ /1ጴጥ 2፥24/
- የጌታን ዳግም ምጽአት በናፍቆት እንዲንጠባበቅ ያሳስበናል፡፡

### 15.4 የጌታን እራት የሚካፈል አማኝ ሊያደርግ የሚገባው ጥንቃቄ

- ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኝ አድርጎ በመቀበሉና ዳግም ልደት በማግኘቱ እርግጠኛ መሆን
- የጌታን ሞትና ትንሣኤ መረዳትና ማመን /1ቆሮ 11፥27/
- በመንፈስ አንድነት ተጠባብቆ መካፈል /1ቆሮ 11፥33/
- ራስን መመርመርና በንስሐ በመቀደስ መካፈልና በቅድስና ሕይወት መመላለስ።/1ቆሮ 11፥31/
- የጌታን ፍቅር ማሰብና ሞቱን ትንሣኤውን መመስከር፡፡ /1ቆሮ 11:26/

# ትምህርት 16 – ክርስቲያናዊ ጋብቻና የቤተሰብ ሕይወት

## 16. 1 ስለ ጋብቻ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

ክርስቲያናዊ ጋብቻ አንድ ወንድና አንዲት ሴት እንደ እግዚአብሔር ቃል አንድ ሥጋ /ባልና ሚስት/ በመሆን ክርስቶስን የቤታቸውና የሕይወታቸው ራስ በማድረግ በፍቅር ተሳስረው በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በአንድነት የሚኖሩበት ሕይወት ነው።

⇨ ጋብቻ ከመጀመሪያው በእግዚአብሔር የተመሠረተ ነው /ዘፍ 2፥18–25/

⇨ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በትምህርቱ አጽድቆታል። /ዮሐ 2፥11፥ ማቴ 19፥3–6/

⇨ የክርስቲያናዊ ጋብቻ በክርስቶስ አምነው በዳኑ ወንድና ሴት መካከል የሚፈጸም ነው። /ዘዳ 7፥1–3 2ቆር 6፥14/

⇨ አንዳንዶች ለወንጌል ራሳቸውን በመለየትና በሌላም ምክንያት ላያገቡ ይችላሉ። /ማቴ 19፥10–12 1ቆሮ 7፥7–9/

⇨ ክርስቲያናዊ ጋብቻ በፍቅር፥ በቅድስናና በቃል ኪዳን ላይ የተመሠረተ ነው። /ዕብ. 13:4/

⇨ ወላጆቻቸውን ይተዋሉ አንድ ሥጋም ይሆናሉ /ዘፍ 2፥24 24፥57/

⇨ ከሞት በቀር የሚለያቸው የለም። /ማቴ 19፥6 ዘፍ 2፥24፥ ሚል. 2፥12–15/

⇨ ጋብቻ የክርስቶስና የቤተክርስቲያን የፍቅር ትስስር የሚያሳይ ተምሳሌት ነው። /ኤፌ 5፥32/



## 16.2 የጋብቻ ዓላማ

- የእግዚአብሔርን ዕቅድና ዓላማን መፈጸም ነው። /ዘፍ 2፥18 መክ 4፥9–12/
- ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሰው ልጅ የታዘዘውን በረከትና ስጦታ ለመቀበል ነው። /ዘፍ 1፥26–28 መዝ 127፥3 ምሳ 18፥22/
- የክርስቶስና የቤተክርስቲያን አንድነት ምስጢር ለመለማመድ ነው። ይህም ምስጢር ፍጹም የሆነ መስጠት፤ፍቅር፤መታዘዝና መገዛት ያለበት ነው /ኤፌ 5፥32 24 ዮሐ15፥13 17፥22/
- ከኃጢአት ለመጠበቅና በቅድስና ለእግዚአብሔር ክብር ለመኖር ነው። /1ቆሮ 7፥2/

## 16.3 የጋብቻ መሠረታዊ መመሪያዎች

1. ለጋብቻ የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት

- አካላዊ፡– በአካል፤ በዕድሜ፤ በአስተሳሰብ፤ በዕውቀት ወዘተ ብቁ መሆን
- መንፈሳዊ፡– በቃል፤ በጸሎትና በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ብስለት መድረስ
- ቁሳዊ፡– ለኑሮ በሚያስፈልጉ ነገሮች ራሱን ማዘጋጀት ነው

2. <u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ መረዳት /ኤፌ 5፥17/</u>

- ♦ የእግዚአብሔር ፈቃድ በጎና መልካም ነው /ኤር 29፥11 ሮሜ 8፥28/
- ♦ የእግዚአብሔር ፍጹም ፈቃድ ሁለቱም በክርስቶስ ይሆኑ ዘንድ ነው።/ሉቃ 10፥20 2ቆሮ 6፥14፥ ኤፌ. 1፥9–10/
- ♦ የእግዚአብሔር ፈቃድ በቅድስና ላይ የተመሰረተ መሆኑን። /ዕብ 13፥4 1ተሰ 4፡3/
- ♦ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሕይወት መስጠትና መቀደስ እንዲሁም እርሱን ደስ የሚያሰኝ ነው። /ሮሜ 12፥1–2 1ተሰ 4፥3–5/
- ♦ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከምድራዊ ነገር ይልቅ ሰማያዊንና የእግዚአብሔርን ክብር ማስቀደም መሆኑን /ማቴ 6፥33 ቆላ 1፥9–12 /

3. <u>እውነተኛ ፍቅር፡–</u> /ኤፌ 5፡25-26/

ይህም ፍቅር በሚታይ ነገር ላይ የተመሠረተ ሳይሆን ከሁሉ በላይ የልብ ሰላምና ደስታን የሚሰጥ ሆኖ የሁለቱ ተጋቢዎች ፍጹም ፈቃደኝነትና መሰጠት ያለበት ነው።ለክርስትያናዊ ጋብቻና ቤተሰብ ሕይወት መሠረት የሆኑ ሦስት የፍቅር ዓይነቶችን መተግበር ወሳኝ ነው፡፡ እነዚህም

1. መለኮታዊ ፍቅር፡- ይህ መለኮታዊ ፍቅር ከሁሉ የሚበልጥ የፍቅር ዓይነት ነው፡፡ /1ቆሮ 13፡4-7 ኤፌ 5፡25-28/
2. ጾታዊ (ወሲባዊ) ፍቅር /ምሳ 5፡18-19 መኃ 3፡9-11/
3. ቤተሰባዊ ፍቅር (በሥጋና በደም የተዋሄደ ዝምድና ፍቅር) ይህም ባልና ሚስት እንደ እግዚአብሔር ቃል አንድ ሥጋ በመሆናቸው አንዱ ለሌላው በመኖር የሚገባውን በማድረግ፣ በመመገብ፣ በመንከባከብና በመጠንቀቅ ላይ የተመሠረተ ፍቅር ነው፡፡ /ኤፌ 5፡30/ ስለዚህ እነዚህ የፍቅር ዓይነቶች ለጋብቻም ሆነ ለቤተሰብ ሕይወት እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ መሆናቸውን ማወቅ ተገቢ ነው፡፡
4. በቃሉ ላይ የተመሠረተ ጽኑ ቃል ኪዳን

ሀ/ ቃል ኪዳን ክፉንም ሆነ መልካሙን አብሮ ተቀብለው ለማለፍ ያለውን የሕይወት ቁርጠኝነትና ውሳኔ ያሳያል። ጋብቻ ሊፈርስ የማይቻል የዕድሜ ልክ ቃል ኪዳን ነው። በቃሉ ላይ የተመሠረተው ቃል ኪዳን የባልና የሚስት ጠንካራ አንድነትና የሕይወት ውሳኔ ሲሆን እንዲሁም ለእግዚአብሔር ያለውን ፍርሃትና መገዛትን የሚያሳይ ነው ቃል ኪዳኑን ለመጠበቅ ቁርጠኛና ታማኝ መሆንን ይጠይቃል። /ዘዳ 11፥18-21፥ ኤፌ 5፥32 ዘፍ. 2፥18/

ለ/ የጋብቻ ቃል ኪዳን ሁለቱ ተጋቢዎች እንደ እግዚአብሔር ቃል በሰውና በእግዚአብሔር ፊት በፍቅር በቅድስናና በተሰጠ ሕይወት አብሮ ለመኖር የሚወስኑበት ወይም የሚገቡበት የማረጋገጫ ቃል ነው።

ይኸውም በዘፍጥረት 2፥19፥ 23-25 ላይ እንደምናየው

- አንዱ አንዱን የገዛ አካሉ አድርጎ መቀበል «ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት ሥጋም ከሥጋዬ ናት »
- በፍቅር አንዱ ለአንዱ የሚመች ረዳት መሆን ወይም በፍቅር የኑሮ አጋር መሆንና ኃላፊነቱን በጋራ መወጣት ማለት ነው
- መተው /Leaving/ «ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል»
- መጣበቅ (Cleaving) «በሚስቱ ይጣበቃል»
- አንድ ሥጋ መሆን /one flesh/ «ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ»
- መሰጠት /Naked and not ashamed/ «ራቁታቸውን ነበሩ አይተፋፈሩም ነበር» /ዘፍ 2፥24-25 ማቴ 19፡5-6 ማር 10፥7-8/
- አንዱ ለአንዱ ፍጹም ታማኝ ሆኖ ለመኖር የሚወስኑበት ነው። /ሚል. 2፥14-16



16.4 የቤተሰብ ሕይወት

የክርስቲያን ቤተሰብ በሕይወትና በኑሮ እግዚአብሔርን ያስከብር ዘንድና አንዱ ለአንዱ ያለውን ኃላፊነትና ግዴታን በማወቅ ይኖሩ ዘንድ በጋብቻ ውስጥ እግዚአብሔር ያስቀመጠው መለኮታዊ ዓላማ ነው። ይኸውም በምድር ላይ ሊያደርግ ያለው የእግዚአብሔር ዓላማና ፍቃዱ የሆነው የመንግሥቱ ሥራ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚፈጸመው ቤተሰብንና ቤተክርስቲያንን አልፎ ነው። ስለዚህ ትዳር ወይም ለጋብቻ ማሰብና መዘጋጀት ማለት ይህንን የእግዚአብሔርን አደራ ለመሸከምና ለመወጣት እንዲሁም ከራሱ አልፎ የሌላውን ኃላፊነት ለመሸከም መዘጋጀት ማለት ነው።
/1ቆሮ 11፥3 ኤፌ 5፥22-23፤ ሉቃ 14፥28/

ሀ. የባልና የሚስት አንድነት የሚገለጥባቸው መንገዶች፡-

- ስሜት/emotional/ አብሮ መሳቅ፣ መደሰት፣ማልቀስና ማዘን
- ማህበራዊ /Social/ አብሮ መሥራት፣ መብላት፣ መውጣትና መግባት
- ዕውቀት /Intellectual/ አብሮ ማንበብ፣ መወያየት፣ መማማር
- አካላዊ /Physical/ መዳሰስ፣ መነካካት፣ ግብረ ሥጋ ግንኙነት
- መንፈሳዊ /Spritual/ አብሮ ቃሉን ማጥናት፣ መጸለይ፣ ጌታን ማምለክና ማገልገል

ለ. በቤተሰብ ኑሮ ያለመግባባት ምክንያቶች

- አንዱ የሌላውን የባሕርይ ልዩነት ያለመረዳት
- እርስ በርስ አለመተማመን፣ ጥርጣሬ፣ በሐሜትና በወሬ መንፈስ መነዳት
- የገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ጉድለት
- ለጸሎት፣ ለቃሉና ለመመካከር በቂ ጊዜ ካለመስጠት የተነሣ ሰይጣን በባልና በሚስት መካከል ጠብን ይዘራል፡፡
- በሩካቤ ሥጋ ፍላጎት አለመጣጣም (አለመርካት) /ምሳ 5፥18-19 1ቆሮ 7፥3-5/
- አስፈላጊ ያልሆነ የቤተዘመድ ጣልቃ ገብነት
- የሥጋዊና መንፈሳዊ ፍላጎት አለመሟላት
- አንዱ ለአንዱ ግልጽ ያለመሆን
- አለመቻቻልና በሚገጥማቸው ሁኔታዎች ላይ ትዕግሥት ማጣት
- ከቤተሰብ ጥገኝነት አለመላቀቅ /ዘፍ 2፥24/
- ከፊት ላሰቡት ዓላማና ዕቅድ አለመድረስ ወይም የነገሮች አለመሳካት
- ሚዛናዊ ያልሆነ የሥራ ክፍፍል ወይም ጫና
- አንዱ ለሌላው ጊዜ አለመስጠት (የሰዓት አጠቃቀም ችግር)
- አንዱ ለአንዱ ሊያደርግ የሚገባውን ነገር አለማድረግ /ኤፌ 5፥22-33 1ጴጥ. 3፥1-7/

ሐ. ያለመግባባትን በጋራ የመፍታት መንገዶች
/ምሳ 16፥7፤ ኤፌ. 4፡26–27፤ ምሳ. 15፡1/

- ችግር በተከሰተ ቁጥር ብዙ አለመናገር ስሜትን መቆጣጠር መቻል፤ ምክንያቶችን እንደቀላል መቁጠር /ምሳ. 29፡11/
- በሥልጣን/በጉልበት/ሳይሆን በማግባባት ማሸነፍ
- አንዱ ለአንዱ መገዛት፣ መታዘዝንና የመቀባበል ባሕርይ መላበስ
- ነገሮችን በሚዛናዊነት ማየትና ማስቀመጥ መቻል
- ትዕግሥትን መላበስና በሁኔታዎች ሁሉ ውስጥ ጌታ ጣልቃ እንዲገባና እንዲቆጣጠር መጸለይና የራስን መብት መተው
- የእግዚአብሔር ስምና ክብር በእኛ ምክንያት በሌሎች ዘንድ እንዳይጎድፍ መጠንቀቅ
- ለችግሮቹ መልስ ማግኘትና ውሳኔ ላይ መድረስ
- መሸነፍን እንደማሸነፍ መቁጠርና መቀበል
- ከሁሉ በላይ የይቅርታ ልብና መንፈስ ሊኖረን ይገባል

መ. በመንፈስ ቅዱስ የተሞላና በቃሉ እውነት የሚኖር ቤተሰብ ሕይወት ባሕርያት

1. <u>ባል</u>፡–

/1ጴጥ 3፥7 ኤፌ 5፥25–30 ፤ 33 ቆላ 3፥19/

- ለቤተሰብ ሰላምንና የተረጋጋ መንፈስ ያሰፍናል
- ከቁጣ ይልቅ በትዕግሥት ለራሱ ፈውስን ያመጣል
- ቁጣን በመቆጣጠርና መንፈሱንም በመጠበቅ ምሳሌ ይሆናል
- ቃላቱን የሚጠብቅና ባለቤቱን በበጎነት በክብር የሚያስተናግድ ነው ምክንያቱም በዚህ ሕይወት ያለመመላለስ ለጸሎት እንቅፋት መሆኑን ስለሚያውቅ
- ባለቤቱን ማጎሳቆልና ማሳፈር /ማስነወር/ ተገቢ እንዳልሆነ ያስተውላል
- የምጠቀምባቸው ቃላቶች ሚስቱን ለማበረታታትና ለመገንባት የሚረዱ ናቸው
- በየዕለቱ የመንፈስ ቅዱስን ምሪትና እርዳታ የሚጠይቅና በመንፈስ ቅዱስ ፍሬም የተሞላ ሕይወት አለው።

2. <u>ሚስት</u>፡–

/ኤፌ 5፥21–24 1ጴጥ 3፥1–6 ምሳሌ 31፥10–31/

- የባልዋን ልብ በፍቅርና በመታመን እንዲሞላ ታደርጋለች
- የመንፈስ ቅዱስን ኃይል በየውሃትና በቅንነት ታስተውላለች እግዚአብሔርም ትፈራለች
- ራሱዋን በመግዛት ቁጣውን ትቆጣጠራለች



- የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን በሕይወት እየተለማመዱ መኖር በሥጋ የሚታየውን ቁንጅናና ውበት ሁሉ የሚበልጥ መሆኑን በመረዳት ለዚህ ከፍተኛ ስፍራን የምትሰጥ ናት።
- የርኅራኄ ሕግ ከአንደበቷ አይጠፋም
- ከባሉዋ ጋር የምትሠራ ናት
- ለልጆች የእናት ፍቅር የሕይወታቸው ጤንነት ቁልፍ መሆኑን ትረዳለች
- በየዕለቱ ያለማቋረጥ የመንፈስ ቅዱስን ምሪትና ኃይል የምትጠይቅና የባሏንም ፍላጎት ለማሟላት የምትጥር ናት

በመጨረሻም ባልና ሚስት ሊደጋገፉበት የሚገባው ልብ ሕልቃና ለሐና እንደሆነላት ዓይነት ሊሆን ይገባል። ይህም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የውስጧን ስሜት በመረዳት መደገፍና በማጽናናት የሚገለጥ ነው። /1ሳሙ 1፥1–8/

3. <u>ልጆች</u>፡–

/ዘጸ.20፥12 21፡17 ምሳ 1፥8 20፥20 30፥11 ኤፌ 6፥1–3፥ ቆላ 3፥20/

- ⇨ ወላጆቻቸውን ይታገዛሉ ያከብራሉ
- ⇨ የወላጆችን ምክር ትምህርትና ተግሳጽ በትሕትናና በአክብሮት ይቀበላሉ
- ⇨ በወላጆቻቸው ፈቃድ ውስጥ ሆነው ለመኖር የተሰጡ ናቸው
- ⇨ ከሁሉ በላይ በሕይወታቸው ጌታን ደስ በማሰኘት ያድጋሉ
- ⇨ ወላጆችን ለመርዳት ይጥራሉ
- ⇨ በሕይወታቸው በተስፋ የተሞሉ ናቸው
- ⇨ በሥራቸውና በአገልግሎታቸው ታታሪና ፍሬያማ /ውጤታማ/ ናቸው

ሠ/ ልጆችን መያዝና የማሳደግ ኃላፊነት

2. <u>ወላጆች ሊያደርጉት የሚገባ ጥንቃቄ፣</u>

- ➢ ልጅን የሚሄድበትን መንገድ ማስተማርና መምራት /ምሳ 22፥6/
- ➢ ለልጆች በሚያሳዩት ፍቅርና በሚደረግላቸው ነገር ልዩነት አለማሳየት /ዘፍ 27፥1/
- ➢ ልባቸው እንዳይዝል በፍቅር ማቅረብ፣ መምከርና መገሥጽ /ቆላ 3፥21/
- ➢ በተለያየ ምክንያት በአባትና በእናት መካከል የሚከሰተውን የባሕርይ ለውጥና ግጭቶችን ልጆችን አለማሳየት

- ራዕይያቸውን አለመናቅና ተስፋ አለማስቆረጥ
- ልጆች በዕድሜ እየጨመሩ በሄዱ ቁጥር በሕይወታቸው የሚገለጠውን የባሕርይ ለውጥ በመረዳት በትምህርትና በምክር መያዝ አስፈላጊነትን ማወቅ
- የክርስቶስን ፍቅር ይማሩ ዘንድ እውነተኛ የአባትነትና የእናትነትን ፍቅር ማሳየት ይህም በሕይወታቸው ጤናማ መንፈሳዊነትን ይቀርጻልና።

2. <u>ልጆችን በክርስቶስ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የመምራት ደረጃዎች</u>

- ለጌታ መስጠት /Dedicate / 1ሳሙ 1፥28 ዘሌ 12፥6 ሉቃ 2፥22/
- እግዚአብሔርን እንዲፈሩ፣ ጽድቅን እንዲወዱና ኃጢአትን እንዲጠሉ ማስተማር /መዝ 34፥11 ምሳ 1፥7 ዕብ 1፥9/
- መታዘዝን እንዲማሩ ማስተማርና መምራት /ምሳ 13፥24 22፥15 3፥11-12፤ 23፥13-14 29፥17 ዕብ 12፥7-11/
- የዓለማዊነትን ባሕሪይ እንዲለምዱ ከሚያደርጉ ሁኔታዎች ሁሉ መጠበቅና መቆጣጠር «ክፉ ባልንጀራነት መልካሙን አመል ያጠፋልና» /ምሳ 13፥20 28፥7 1ቆር. 15፡33/
- የሰውን አካሄድና ተግባር ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚያይና እንደሚመዝን እንዲያውቁ ማስተማር /መዝ 139፥1-12፥ ዕብ 4፥12፡13/
- በግል ሕይወታቸው ንስሐ በመግባት ጌታን እንደግል አዳኝ አድርገው እንዲቀበሉና የውሃ ጥምቀትም እንዲያገኙ ማድረግ /ማቴ 19፥14/
- መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት በእግዚአብሔር ቃል ዕውቀትና በክርስትና ሕይወት መሠረት እንዲኖራቸው የቤተክርስቲያን አስተምህሮና ቅዱስ ሥርዓቶችንም እንዲያውቁ ማስተማር /ዘፍ 18፥19 መዝ 78፥2-8 ኢያ 4፥21-24 ዘዳ 6፥7/
- የጌታን ቅርብ ወዳጅነትና አባትነትን እንዲያውቁና እንዲተማመኑበት እንዲሁም የክርስቶስን አዳኝነት ለሌሎች እንዲመሰክሩና የእግዚአብሔርን መንግሥት ሥራ እንዲለማመዱ ማስተማር /መዝ 119፥63 ዮሐ 14፡18 ማቴ 28፡19-20/
- ከዓለም እንደተለዩ ፤ ለዚህች ምድር እንግዳ /መጻተኛ/ እንደሆኑና ሰማያዊ ዜጋ መሆናቸውን እንዲያውቁ ማስተማር። /2ቆሮ 6፥14 ያዕ 4፥4 ዕብ 11፥13-16 ፊል.3፥20፥ ቆላ 3፥1-3 1ጢሞ 4፥7-8/
- የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀትና የጸጋ ስጦታዎች አስፈላጊነት እንዲያውቁና እንዲጠሙ ማስተማር /ሐዋ 1፥4-5 1ቆሮ 12፥4-11 ሐዋ 2፥4 - 39/



- እግዚአብሔር እንደሚወዳቸውና በሕይወታቸው በጎ ዓላማ እንዳለው እንዲያውቁ ማስተማር /ሉቃ 1፥13-17 ዮሐ 13፥1 ኤፌ 1፥4-10 29፥11 ዘፍ 28፥10-15/
- በግላቸው ለቃሉና ለጸሎት የተሰጠ ሕይወት እንዲኖራቸውና ይህንም መለማመድ እንዲችሉ ምቹ ቦታና ጊዜ እንዲኖራቸው ማመቻቸት /ዘዳ 6፥5-7፥ ኢያ 1፥8 2ጢሞ 3፥15-17/
- በክርስቶስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወድዱ ሁሉ በዓለም ላይ እንደሚጠሉ፣ በጌታ ስም ስለጽድቅ መከራ መቀበልና መሰደድ በእግዚአብሔር መንግሥት ታላቅ ዋጋ እንዳለው እንዲያውቁ ማስተማር /ማቴ 5፥10-12፥ 2ጢሞ 3፥12/
- ሁል ጊዜ ስለልጆች በንስሐና በምልጃ ጸሎት በእግዚአብሔር ፊት መቆም /ኢዩ 1፥4-5 ኤፌ 6፥18/
- የወላጆች እንዲህ ዓይነት ፍቅርና መሰጠት /መስዋዕትነት/ ልጆቻቸው የእግዚአብሔርን ፍቅር እንዲረዱ በጌታም ያላቸውን እምነት እንዲያሳድጉና ለጌታ ክብር እንዲኖሩ ጥሩ ምሳሌ በመሆን የልጆቻቸውን መንፈሳዊ ሕይወት ይቀርፃል። እግዚአብሔርን በማወቅ፥ በመፍራትና ፍሬያማ ሕይወት በመኖር ልጆቻቸውንም በእግዚአብሔር ፍቅር በመልካም ምሳሌነት የሚያስተዳድር ቤተሰብ ለአገርና ለቤተክርስቲያን በረከት ነው። ስለዚህ የወላጆች ጤናማ መንፈሳዊ ሕይወት የቅድስናና የፍቅር ኑሮ የልጆችን የወደፊት ሕይወት ለመርገም ወይም ለበረከት ምክንያት እንዲሆኑ ሊያደርጋቸው ይችላል። /መዝ. 128፡1-6/

ምሳሌ፡-

- የጢሞቴዎስ እምነት አቋም /2 ጢሞ 1፥5/
- የዔሊ ልጆች ያለ ዕድሜ መሰበር /1 ሳሙ 2፥12 29-34/

ስለዚህ የአንድ ክርስቲያን ቤተሰብ በኑሮ የሚገጥመውን ፈተና ሁሉ አልፎ በእግዚአብሔር በረከት ውስጥ በድል ሕይወት መኖር የሚችለው ባልና ሚስት የልብና የመንፈስ አንድነትን በመጠበቅ በፈርሃ እግዚአብሔር፣ በፍቅር፣ በቅድስናና አንዱ ለሌላው በመስጠት ሕይወት መኖር ሲችል ብቻ ነው። /መዝ 128፥1-6 ኤፌ 5፥21-33/ «እግዚአብሔርም ባረካቸው እንዲህም አላቸው ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው» /ዘፍ1፥28/

## ትምህርት 17 – ቅጣት / Discipline /

«ያለ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም፡.... ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ የሚያሰኝ አይመስልም ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል» /ዕብ. 12፡5–11፤ ምሳ. 3፡11–12/ ቤተክርስቲያን በአንድ አባሉዋ ላይ የሥነ–ሥርዓት እርምጃ የምትወስድበት ምክንያት አንድ አማኝ የእግዚአብሔር ቃልና የቤተክርስቲያንቷ እምነት አቋም የማይፈቅደውን ነገር እያደረገ ሲገኝ ነው። ዓላማውም አንድ አማኝ በኃጢአቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይቶ እንዳይጠፋ ለማዳንና የቤተክርስቲያንንም ቅድስና ለመጠበቅ ነው።
ይኸውም፡

- በግልጽ ኃጢአት ፈጽሞ ሲገኝ
- እንዲጸጸትና እንዲመለስ ለማድረግ /2ጢሞ 2፡25–26/
- ሌላው እንዲማርበት

### 17፡1 – ስለራሳችን ተግባር ማወቅ የሚገባን እውነት

ሀ. ከፉም ሆነ መልካሙ ሥራችን በእግዚአብሔር ፊት የተገለጠ መሆኑንና ወደ ፍርድም እንደሚያመጣ ማወቅ /መክ 12፡14/

- በልብ የተሰወረው ነገር / ዕብ 4፡13 1ቆሮ 4፡5/
- ሥነ ምግባራችን /ሮሜ 2፡6–10 መክ 12፡14/
- አካሄዳችን /ምሳ 21፡2–3 ዘፍ 6፡12 ምሳ 16፡7/
- ንግግራችን /ማቴ 12፡36–37 5፡22/

ለ. በምናደርገው ነገር ሁሉ ኃላፊነትና ተጠያቂነት እንዳለብን ማወቅ/1ቆሮ 4፡2–5፤ ሉቃ12፡47–48 ሮሜ 2፡1–4/

ሐ. ለበጎ ሥራችን ሁሉ ብድራት ወይም ዋጋ መኖሩን በማወቅ ማከናወን /ራዕ 22፡12/

- ታማኝነት ይረጋገጣል /ማቴ 25፡21–26/
- የሥልጣን መጨመር ወይም መወሰድ /ማቴ 25፡14–30/
- ታላቅ ወይም ታናሽ መሆን /ማቴ 5፡19 19፡30/
- ሽልማት ማግኘት ወይም ማጣት /1ቆሮ 3፡12–14/
- ክብር ማግኘት ወይም ማጣት

### 17.2 የሥነ–ሥርዓት ርምጃ የመውሰድ ደረጃዎች /ማቴ 18፡15–18 ቲቶ 3፥10–11/

- መጀመሪያ በግል ማስተማር፣ መምከርና መገሰጽ
- ከሌሎች ጋር በመሆን በቤተክርስቲያን ደረጃ መምከርና መገሰጽ /1ጢሞ 5፡20/



- እንደ ጥፋቱ መጠን በእግዚአብሔር ፊት ራሱን እየመረመረ በጸሎት የሚቆይበት ጊዜ መስጠትና ሌሎች በክፉ ሥራው እንዳይተባበሩ ማድረግ /2ተሰ 3፡14–15/
- ደረጃ ተሰጥቶ እንደጥፋቱ መጠን የቅጣት ጊዜ ገደብ ሊለያይ ይችላል
- ይህም ሆኖ የማይታረምና በመንጋው ውስጥ ችግር የሚፈጥር ሆኖ ከተገኘ ከቤተክርስቲያን አባልነት ማገድ ግዴታ ይሆናል /1ቆሮ 5፡3–5 11–13 1ጢሞ 1፡20/
  በመጨረሻም ጥፋቱን አምነው በታዛዥነት የተቀጣውን ሰው በፍቅርና በምሕረት መቀበል በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ማገልገልና ማጽናናት ከአገልጋዮችና ከቤተክርስቲያን ይጠበቃል። /2ቆሮ 2፥5–10 ፊልሞና 1፥15–20/

### 17.3 ለሥነ–ሥርዓቱ የመታዘዝና የመገዛት ውጤት

- እግዚአብሔርን የመፍራትና የመታዘዝን ሕይወት ይማራል /2ቆሮ 5፡11 10፡6/
- የእግዚአብሔርን ምሕረት ያገኛል
- የመንፈሳዊ ሕይወት ተሃድሶና መነቃቃት ያገኛል /ዕብ 12፡10 2ቆሮ 7፡8–11/
- ከጠላት እጅ ወይም ወጥመድ ያመልጣል /2ጢሞ 2፡25–26/
- ከሕይወቱ የተወሰደበት ፀጋ፣ መንፈሳዊና ሥጋዊ በረከት ምርኮ ይመለስለታል።
- ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር ያለው ኅብረት ይታደሳል
- ጌታን ደስ የሚያሰኝ የትህትናን ሕይወት ይማራል

## ትምህርት 18 – የቀብር ሥነ–ሥርዓት

ሞት የአንድ ሰው ምድራዊ ሕይወት ፍጻሜና ወደ ዘላለማዊ ዓለም መሸጋገሪያ ድልድይ ነው የሰው ዘር ሁሉ በዚህ ጎዳና እንዲያልፍ ፈጣሪው ስለወሰነ በየትኛውም ዕድሜ ክልል ፤ በማንኛውም ጊዜና ሰዓት ይፈጸማል። ሞት በክርስትና እምነት መሠረት ወይም በክርስቶስ አምነው ለዳኑት ወደ ተሻለ ኑሮ የመሸጋገሪያ ድልድይ ሲሆን በአሕዛቦች መረዳት ወደ ሕይወት አልባነት ጥፋት መግቢያ ሆኖ ይታያል። /1ተሰ 4፡13/

### 18.1 ሞት እንዴት መጣ?

ሰው መጀመሪያ ሲፈጠር ለሞት ሳይሆን ከአምላኩ ጋር በኤዴን ገነት ለዘላለም ሕያው ሆኖ እንዲኖር ነበር /ዘፍ. 2፡15፤ 3፡22–24/ ነገር ግን አዳም ባለመታዘዙ ምክንያት የኃጢአት ውጤት የሆነው ሞት ወደ ዓለም ገባ ሰውም ለሞት ተገዥ ሆነ። /ዘፍ. 2፡17 3፡19 ሮሜ 5፡12/

### 18.2 የሞት ዓይነት

- መንፈሳዊ ሞት፡- ሰው የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመተላለፉ ምክንያት ከአምላኩ ጋር የነበረው ኅብረት በመበላሸቱ ከእግዚአብሔር መለየቱን ያሳያል። /ዘፍ 3፡8 4፡13-14 ኤፌ 2፡1-2/
- አካላዊ ሞት፡- የሰው ሥጋ ከነፍስ መለየት ነው። ይህ ዓይነቱ ሞት ለአማኞችም ሆነ ላላመኑት ሁሉ የማይቀር ዕዳ ነው። /ዘፍ 3፡19፥ ዕብ 9፡27 ያዕ. 2፡26/
- ዘላለማዊ ሞት ይህ ዓይነቱ ሞት ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኝ አድርጎ ያልተቀበሉትን ሁሉ የሚጠብቅና ነፍስ በገሃነም እሳት ለዘለዓለም የምትሰቃይበት ነው። ይህም ሁለተኛ ሞት ተብሎ ይጠራል። /ማቴ 25፡41 ራዕ 14፡9-11 21፡8/

### 18.3 የቀብር ሥነ-ሥርዓት

በዚህ ሥነ ሥርዓት ላይ ከሚነበቡ መጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጥቂቶቹ፡-
/ዘፍ 3፥19 ፤ ኢዮ 19፥25-27 ኢሳ 38፥1 ዮሐ5፥24-25፤ 11፥24-26 1ቆሮ 15፥1-57 መክ. 12፥1-8 ራዕ 20፥11-15 ፤ 21፥1-5/

እግዚአብሔር በቃሉ «አፈር ነህና ወደ አፈር ትመለሳለህ» ብሎ እንደተናገረ ቀብር ማለት የሰው ነፍስ ከሥጋው ተለይታ ወደ ፈጣሪዋ ስትሄድ በድን አካሉን /አስከሬኑን/ ወደ አፈር መመለስ /የግባተ-መሬት/ ሥነ-ሥርዓት መፈጸም ማለት ነው።

በዚህ ሥነ-ሥርዓት ላይ የሚደረጉ ፕሮግራሞች፡-

- ለወንጌል ምስክርነት ምቹ ማድረግ
- ኃጢአትና የኃጢአት ዋጋ ሞት መሆኑን፣ በክርስቶስ የሚገኘውን ደህንነት፣ የትንሣኤ ተስፋና የዘላለም ሕይወት ወዘተ መስበክ።
- የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ መሆኑን መግለጥ /ዘኁ. 23፥10 ራዕ 14፥13 መዝ 116፥6/
- ከዚህ ሥርዓት ጋር የሚሄዱ መዝሙሮችን መዘመር
- ግባተ-መሬቱን በጸሎት መፈጸም
- ሐዘንተኞችን በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ማጽናናት /1ተሰ 4፡13-18 2ቆሮ 5፡1-5/

### 18.4 አካላዊ ሞት ለአማኞች የሚሰጠው ጥቅም /ፊል 1፡23/

- ከዚህ ዓለም መከራና ድካም ለማገፍ /ራዕ 14፡13 7፡16-17/
- የማይበሰብሰውንና የማይሞተውን አካል ለመልበስ /1ቆሮ 15፡54/
- በእግዚአብሔር እጅ የተሠራውን ዘለለማዊ ቤት ለመውረስ /2ቆሮ 5፡1-5/



- እግዚአብሔርን በሙላት ለማምለክ /ራዕ 7፡13-15/
- ከቀደሙት እምነት አባቶች ጋር ለመገናኘት /ዕብ 11፡39-40 ራዕ 6፡11/
- የአገልግሎትን ዋጋ /ሽልማት/ ከጌታ እጅ ለመቀበል /2ጢሞ 4፡6-8/
- ጌታ ኢየሱስን ፊት ለፊት ለማየትና ከእርሱም ጋር ለመኖር /ሉቃ 23፡43/

ማሳሰቢያ፡- የዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ዓላማ ሥርዓቶችን በተመለከተ የመጽሐፍ ቅዱስ መሠረታዊ ዕውቀት ለማስጨበጥ እንጂ የተኛውንም ቤተእምነት ፕሮግራም ይዘትና አፈጻጸም ለመገደብ አይደለም።

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ቤተክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው?
   የምትታይና የማትታይ ቤተክርስቲያን በምን ይለያያሉ?
2. ቤተክርስቲያን በምድር ላይ የመኖሩዋ ዓላማ፣ ሥልጣኑዋና ተግባሩዋ ምንድን ነው?
3. የታላቁ ተልዕኮ መሠረተ ሐሳቦች ምንድን ናቸው?
4. ቤተክርስቲያን ያመኑትን ደቀመዝሙር የማድረግ አስፈላጊነት፣ ስልትና ይዘት በተመለከተ ተወያዩ::
5. የቤተክርስቲያን ሥርዓቶች ምንድን ናቸው? ሥርዓቶችን ሁሉ መፈፀም አስፈላጊ ነውን? ለምን?
6. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጋብቻ ፍቺ ጥያቄ ሲመልስ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም ሲል ምን ማለቱ ነው? (ማቴ 19፡3) ይመልከቱ
7. በቤተሰብ ውስጥ ለሚፈጠሩ አለመግባባቶች ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው? እንዴትስ ይፈታሉ?
8. በአሁኑ ዘመን ጋብቻና የትዳር ዓለም ዓለም አቀፋዊ ገጽታ ምን ይመስላል?
9. የክርስቲያናዊ ጋብቻና ቤተሰብ ሕይወት ቅድስና ለመጠበቅ ቤተክርስቲያን ምን ማድረግ አለባት? ምን ይጠበቅባታል?

# ምዕራፍ ስድስት

## የመጨረሻዎቹ ነገሮች

### ትምህርት 19 – የክርስቶስ ዳግም ምጽአት

19.1 ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት ሦስት ዋና ዋና አመለካከቶችን በአጭሩ እንመለከታለን፡–

1. አልቦ–ሺህ አመለካከት/Amillennialism /
   የሺ ዓመት መንግሥት በምድር ላይ አይኖርም የሚል ነው። አንድ ሺ ዓመት የሚለው ቁጥር የሚወክለው በኢየሱስ የመጀመሪያና በዳግም ምፅዓቱ መካከል ያለውን ሙሉ ጊዜ እንጂ በምድር ላይ የሚታይ የእግዚአብሔርን መንግሥት አገዛዝ ዘመን የሚያመለክት አይደለም ነገር ግን ወደፊት የተከበረና ፍጹም የሆነ የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ ይመሠረታል ብለው ያምናሉ።
2. ድህረ–ሺህ አመለካከት /Post millennialism/
   ኢየሱስ የሚመጣው በሺ ዓመት ፍጻሜ በምድር ላይ ፍጹም የሆነ ሰላምና ብልጽግና ከሰፈነና ብዙ ሰዎች በእምነት ወደ ጌታ ከተመለሱ በኋላ ነው የሚል ነው። እነዚህ ሁለቱም ቤተክርስቲያን በሰባቱ ዓመት ታላቁ መከራ ውስጥ እንደሚታልፍና የክርስቶስ ተመልሶ መምጣት፣ የሙታን አካላዊ ትንሣኤና የመጨረሻው ፍርድ የአዲስ ሰማይና የአዲስ ምድር ሥርዓት ከመጀመሩ በፊት በአንድ ጊዜ ይፈጸማል ብለው ያምናሉ። በዚህን ጊዜ ክርስቶስ የሚነግሠው በሰዎች ልብ በማደር እንጂ በምድር ላይ በሚታይ አካል በመሆን አይደለም ይላሉ።
3. የቅድመ–ሺህ አመለካከት/Premillennialism/
   የአንድ ሺ ዓመት ምድራዊ መንግሥት ከመጀመሩ በፊት ክርስቶስ ወደ ምድር ይመለሳል የሚል ነው። በሰባቱ ዓመት መከራ ጊዜ ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ጋር በአየር ላይ እንደምትሆንና በሰባቱ ዓመት ፈጻሜ ላይ ለአንድ ሺ ዓመት መንግሥት አገዛዝ ከክርስቶስ ጋር ወደ ምድር ትወርዳለች ብለው ያምናሉ።

19.2 መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ

| | | |
|---|---|---|
| መዝ 50:2–5 | ማቴ 24:30 | 2ጴጥ 3:11 |
| ኢሳ 13:6–10 | ማር 14:62 | ራዕ 1:7 |
| ሉቃ 21:25–28 | ራዕ 22:121 | ዮሐ2:28 |
| ዕንባ 2:3 | ሐዋ 1:9–11 | ዳን 7:13–14 |



የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ማለት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ ክብር ወደ ምድር የሚመለስበትን ጊዜ የሚያበስር ሲሆን ይህም ከመጽሐፍ ቅዱስ ዐበይት ትንቢቶችና ተስፋዎች አንዱ ነው።
ጌታ ኢየሱስ ገና ከመሞቱ በፊት ነበር በሊቀካህናቱ ፊት በቀረበ ጊዜ «...የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታዩታላችሁ» አላቸው ይህንን ቃል እንደገና ለደቀመዛሙርቶቹም ሲያረጋግጥላቸው እንዲህ አለ፡-
«. . . በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁ ሄጄ ስፍራ ባዘጋጅላችሁ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ» /ዮሐ 14፥1–3/

ሐዋርያው ጳውሎስም የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለአማኞች ሁሉ ታላቅ ተስፋ መሆኑን ሲገልጽ፡–
«. . .የተባረከው ተስፋችን እርሱም የታላቁን የአምላካችንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር መገለጥ እየጠበቅን. . .» በማለት ይናገራል /ቲቶ 2:13/
ሐዋርያው ዮሐንስም፥ «እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል። ዓይንም ሁሉ የወጉትን ያዩታል የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለእርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ።» ሲል ጽፎአል። /ራዕ 1:7/
«ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል» ሐዋ 1:11

19:3 የመምጣቱ ምልክቶች /Last days of preparation/

| | |
|---|---|
| ማቴ 24:3–33 | ዳን 12:4 |
| ሉቃ 21:7–17 25–28 | 2ጢሞ 3:1–5 |
| ማር 13:3–27 | 1ዮሐ 4:1–2 |
| ሉቃ 17:26–29 | |

- ብዙዎች እኔ መስህ /ክርስቶስ/ ነኝ እያሉ በስሙ ይመጣሉ
- ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣል
- ረሃብ፣ ቸነፈር፣ ጦርነትና የምድር መናወጥ ይሆናል እነዚህም የምጥ ጣር መጀመሪያ የሚባሉ ናቸው።
- አማኞች ይሰደዳሉ እርስ በርስም አልፎ ይሰጣጣሉ
- በእምነት የማይጸኑ የሚሰናከሉ ይበዛሉ
- ሐሰተኞች ነቢያትና አስተማሪዎች ይነሣሉ ይበዛሉም
- የትውልዱ ባሕርይና አኗኗር ዘይቤ እንደሎጥና እንደኖህ ዘመን ይሆናል
- ከአመጻ ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች
- ለፍጥረት ሁሉ የጭንቀትና የመከራ ጊዜ ይሆናል
- እውቀትና ምርመራ ይበዛል
- ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል።

- በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል::ይህም ሊሆን ሲጀምር ቤዛችሁ ቀርቦአልና አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሡ

### 19፡4 የክርስቶስ ዳግም ምጽአት

ሀ. ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ የሚጠራባቸው ስሞች /ራዕ 19:11-16/

- ❖ የታመነ /2ጢሞ 2:13/
- ❖ እውነተኛ /ዮሐ 14:6/
- ❖ የማይታወቅ ስም /ማቴ 11:27/
- ❖ የእግዚአብሔር ቃል /ዮሐ 1:1-3/
- ❖ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ /ራዕ 17:14/

ለ. ክርስቶስ ዳግም ሲመጣ የሚታይ ክብርና ውበት፤ /ራዕ 1:13-16/

- እስከ እግሩ ድረስ ሙሉ ልብስ የለበሰ:- የክብርና የቁንጅና ምልክት ነው
- ደረቱን በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ:- የፈራጅነቱ ምሳሌ ነው
- ራሱና ፀጉሩ እንደበረዶ ነጭ ነበሩ:- የቅድስና ምሳሌ ነው
- ዓይኖቹ እንደ እሳት ነበልባል ነበሩ:- የዓለም ፈራጅነቱ ምሳሌ ነው
- እግሮቹ በእቶን የነጠረ የጋለ ናስ ይመስሉ ነበር:- የፍርድ ምልክት ነው
- ድምጹ እንደ ብዙ ውሆች ነበር:- የኃይልና የሥልጣን ምልክት ነው
- ፊቱም በኃይል እንደሚያበራ እንደ ፀሐይ ብርሃን ነው:- የክብሩ ምሳሌ ነው
- አሕዛብንም ይመታበት ዘንድ ስለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል:- የእግዚአብሔር ቃል ነው /ራዕ 19:15/
- የእግዚአብሔርን የብርቱ ቁጣውን ወይን መጥመቂያ ይረግጣል /ራዕ 14:19-20 ኢሳ 63:1-6/
- አህዛብንም በብረት በትር ይገዛቸዋል:: /መዝ 2:9 ራዕ 2:27/

ይህ የክርስቶስ ውበትና ክብር በዘመናት ሁሉ ክብሩን ለማየት የተጠሙ የእግዚአብሔር ልጆች በሙላት ሲያዩት ያለው ተስፋ ነው /ዘጸ 33:18 መዝ 17:15 2ቆሮ 3:18/

ሐ. የክርስቶስ ዳግም ምጽአት እንዴት ይሆናል?

- ተ ሰዎች ሰላምና ደኅንነት ነው ሲሉ ይመጣል /1ተስ 5:3/
- ✝ በድንገት በማይታወቅ ቀንና ሰዓት ይሆናል /ማቴ 24:36-44/
- ✝ በመለከትና በመላዕክት አለቃ ድምፅ ይሆናል /1ተስ 4:16/
- ✝ በታላቅ ክብር በደመና ይመጣል /ማር 14:62፥ ሉቃ 21:27/
- ✝ እየታየ ይመጣል።/ሐዋ. 1:11፥ ራዕ 1:7/
- ✝ ከመላዕክቱና ከቅዱሳኑ ጋር ይመጣል /ማቴ 24:31/
- ✝ በእሳት ነበልባል ይገለጣል /2ተስ 1:6/



- ✝ መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚያበራ ይሆናል /ማቴ 24:27፥ ሉቃ 17:24/
- ✝ የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል። /ማቴ 24:30/
- ✝ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ ሆኖ ይመጣል /ራዕ 19:16?

### 9፡5 ጌታ ሲመጣ የሚከናወኑ ነገሮች ቅደም ተከተል

1. <u>የቤተክርስቲያን መነጠቅ /The Rapture/</u>

- በክርስቶስ የሞቱ አማኞች አስቀድመው ይነሣሉ ይህም የፊተኛው ትንሣኤ ተብሎ ይጠራል /1ተስ 4:16 ራዕ 20:6/
- በምድር ላይ ሕያዋን ሆኖ ያሉ አማኞች በድንገት በቅጽበት ዓይን ይለወጣሉ ከዚያም ጌታን በአየር ላይ ለመቀበል በደመና ይነጠቃሉ /1ተስ 4:17 1ቆሮ 15:51-53/
- ቤተክርስቲያን ጠላቷ የሆነውን ሞትንና ሰይጣንን ለዘላለም ድል ታደርጋለች /1ቆሮ 15:54-57/
- የሙሽሪትና የሙሽራው መገናኛ ጊዜ ወይም የበጉ ሠርግ ግብዣ ጊዜ በአየር ላይ ይሆናል /ራዕይ 19:7-9/
- የመነጠቅ ዕድል ያገኙ ቅዱሳን ሁሉ በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት ይቆማሉ /2ቆሮ 5:10 ሮሜ 14:12/
- ሥራቸው በእሳት ተፈትኖ ሲያልፍ እንደሥራቸው መጠን ደመወዝ /ሽልማት/ ይቀበላሉ /1ቆሮ 3:14-15 ሮሜ 2:6-7 2ጢሞ 4:8 ገላ 6:7-9/
- የመነጠቅ ዕድል ያገኙ ቅዱሳን ከክርስቶስ ጋር ለሰባት ዓመት በአየር ላይ ይቆያሉ
- የሰባቱ ዓመት መከራ ጊዘ ሲያበቃ ለሺ ዓመተ መንግሥት ከክርስቶስ ጋር ወደ ምድር ይወርዳሉ

2. <u>የመጀመሪያው ሦስት ዓመት ተኩል መከራ / The Tribulation /</u>

- ○ በዚህ መከራ ጊዜ ቤተክርስቲያን ከሙሽራዋ ጋር በአየር ላይ ትሆናለች /ሉቃ 21:36 1ተስ 1:10 2ተስ 4:17 ራዕ 3:10/
- ○ በምስጢር ይሠራ የነበረው የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ይገለጣል ሥራውንም በግልጥ ይጀምራል። አሥሩን መንግሥታት ማስተባበርና መምራት አንዱ ተግባር ነው። /ራዕ 17፥12-13/
- ○ በፀሐይ፥ ጨረቃና ከዋክብት ላይ ልዩ ልዩ ምልክቶች /ለውጦች/ ይታያሉ /ኢሳ 13፥10-11 ማቴ 24፥29 ራዕ 6፥12-14 /
- ○ ሰባቱ የቁጣ ማኅተሞች የሚፈቱበት ጊዜ ይሆናል /ራዕ 6:1-17/
- ○ ሁለቱ ምስክሮች ይነሣሉ ወንጌልን ይሰብካሉ በአውሬውም ሥልጣን ይገደላሉ ከሦስት ቀን ተኩል በኋላ ትንሣኤን ያገኛሉ /ራዕ 11፥4-12/
- ○ ሐሰተኞች ነቢያት ታላላቅ ምልክቶችንና ተአምራትን በማድረግ ብዙዎችን ያስታሉ ። /ማቴ 24:24 ራዕ 13:13 2ተስ 2:9-10/
- ○ ከአሥራ ሁለት እስራኤል ነገዶች የታተሙ 144 ሺህ ሰባኪያንና መላዕክት ወንጌልን ይሰብካሉ ብዙ ነፍሳትም ይድናሉ

ከዘላለም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሰቃያሉ:: /ራዕ 20:10/

⇨ የወደቁ መላዕክት እግዚአብሔር አስቀድሞ የወሰነባቸው የዘላለሙ የገሃነም እሳት ፍርድ ይቀበላሉ:: /ማቴ 25:41 2ጴጥ 2:4 ይሁዳ 1:6/

⇨ ፈራጁ ክርስቶስ ነው:: ምክንያቱም እግዚአብሔር አብ የመፍረድን ሥልጣን ሁሉ ለወልድ ሰጥቷልና /ዳን 7:13-14 ማቴ 25:31-46 ዮሐ 5:22-23 2ጢሞ 4:1 ራዕ 20:11-15/

## 19፥6 የጌታን ምጽአት እንዴት መጠበቅ አለብን?

« እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ የሰው ልጅ በማታስቡበት ሳዓት ይመጣልና» /ሉቃ 12:40 ማቴ 24:44-51/

- የጌታ ምጽአት በድንገት ስለሚሆን ነቅቶ /ተዘጋጅቶ/ መጠበቅ /ማቴ 25፥13 24፥44 2ጴጥ 3፥10 ራዕ 16፥15/
- ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊ ምኞትን በመካድ ራሳችንን በመግዛት፣ በጽድቅና እግዚአብሔርን በመምሰል ሕይወት በመኖር /2ጴጥ3፥11–14 ቲቶ 2፥12–13/
- እንደ ልባሞች፥ ቆነጃጅት ማሰሮአችንን በዘይት ሞልተን መብራታችንን አዘጋጅተን መጠበቅ፤ ይህም የጸጋ ሙላት ነው። /ማቴ. 25፥2፤ 1ቆሮ. 1፥7–8፤ ዕብ. 12፥15–17/
- በእምነትና በትዕግሥት ጽናት /ዕንባ 2፡3 ያዕ 5፥7–11/
- በተሰጠን አገልግሎት እየተጋን መጠበቅ /ማቴ 25፥26–30 2ጢሞ 4፡5 ቆላ 4፥17/
- ልብሳችንን በክርስቶስ ደም አጥበን በማንጻት በቅድስና ሕይወት በመኖር /ዕብ 12፥14 ራዕ 22፥14 1ተሰ 5፥23 ፊል 1፥9–11/
- በጸሎት ትጋት /ሉቃ 21፥34–36 2ጴጥ 1፥10–11/
- በክርስቶስ ፍቅር ሙላት መጠበቅ /ራዕ 22፥17 ፥20 ኤፌ 3፥18–19 ፊል 1፥11/
- በመከራ በመጽናት፡-
  - በፈተና የሚጸና የተባረከ ነው ከተፈተነ በኃላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና::
  - እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል
  - እነሆ ቶሎ ብዬ እመጣለሁ ማንም አክሊልህን እንዳይወስድብህ ያለህን አጽንተህ ያዝ:: /ማት 24:13 ያዕ 1:12 ራዕ 3:11/ እግዚአብሔር በጽድቅና በቅንነት ይፈርዳል። ስለዚህ ቤተክርስቲያን የክርስቶስን አደራ ለመወጣት እየተጋች በቅድስና ኑሮ ራስዋን በማዘጋጀት የጌታን ዳግም ምጽአት መጠበቅ ይገባታል።

*ማራናታ» አሜን ጌታ ኢየሱስ ቶሎ ና !!*



# ትምህርት 20 – የሙታን ትንሣኤ

አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል:: ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ ሙታን በሰው በኩል ሆኖአልና:: ሁሉ በአዳም እንደሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና::
ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሣ ካመንን እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል።

## 20፥1 የሙታን ትንሣኤ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

ኢዮ 19፥25–27 ኢሳ 26፥19
ዳን 12፥1–3

## 20፥2 የሙታን ትንሣኤ በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት

ዮሐ 5፡28–29 ሐዋ 24፥15
ዮሐ 6፡39–40 1ተሰ 4፥14–16
1ቆሮ 15፥12–57 ራዕ 20፥13

## 20፥3 እንዴትና በምን ዓይነት ሁኔታ ይነሣሉ?

△ እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል 1ቆሮ 15፥23

△ የቅዱሳን ትንሣኤ የሚሆነው በራሱ ቅደመ ተከተል ሲሆን ይህም የመጀመሪያ ትንሣኤ ይባላል:: ሁለተኛ ሞት በእነርሱ ላይ አይሰለጥንም /1ተሰ 4፥15–17 ራዕ 20፥6/

△ በኃጢአንና በቅዱሳን ትንሣኤ መካከል የአንድ ሺህ ዓመት ጊዜ ልዩነት ይኖራል /ራዕ. 20፡4–5/

△ የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን በሰባት ዓመት መከራ ዘመን ፍጻሜና በሺህ ዓመት መንግሥት ጅማሬ ላይ እንደሚሆን ይገመታል። /ራዕ 20፡4/

△ የኃጢአን ትንሣኤ በአንድ ሺ ዓመት ፊጻሜ ላይ ሲሆን ይህም ሁለተኛ ትንሣኤ ይባላል:: እነዚህን ሁለተኛ ሞት ይጠብቃቸዋል /ራዕ 20፥13–14/

△ ይህ የሚበሰብሰው አካል የከበረውንና የማይበሰብሰውን አካል ይለብሳል። በትንሣኤው ኃይልና በመንፈሱ ሙሉ መዋጀትን በማግኘት የከበረውን አካል ይለብሳል። /ሮሜ 8፡11፥ 2ቆሮ 5፡4–5 1ቆሮ 15፥53–54/

△ የትንሣኤው አካል የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስና ኃይልን የተሞላ ሲሆን ነገር ግን በቁሳዊ ዓለም የማይታገድና የማይከለከል አካል ነው:: /ሉቃ 24፡30–31፤ ዮሐ 20፥19–27/

△ የትንሣኤው አካል ሥጋና ደም ያይደለ ሕመምና ሞትን የማያውቅ የከበረ አካል ነው:: /ሉቃ 24፡39 1ቆሮ 15፥42–44/

△ የሰው ትንሣኤ አካል የከበረውን የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ አካል ይመስላል። /ፊል 3:21 1ዮሐ 3:2/

△ የትንሣኤ በኩር የሆነው ክርስቶስ በደሙ ለተዋጀው ሕዝብ የትንሣኤ ዋስትና ነው። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ የቅዱሳንን ሞት እንቅልፍ ይለዋል::
/ቆላ 1:18 1ቆሮ 15:20-21 1ተሰ 4:13 ራዕ 1:17-18/
« ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ:- አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ»

## 20.4 ቅዱሳን እንደሥራቸው መጠን ከጌታ እጅ ብድራትን ይቀበላሉ

«ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ የማትነቃነቁም የጌታም ሥራ ሁል ጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ»።
/1ቆሮ 15:58 ዕብ 10:35-38 6:10-12 ዕብ 6፥10-12 ማቴ 16፥27/

- ደመወዛቸውን ይቀበላሉ
/1ቆሮ 3:14፥ 2ዮሐ 1:8፥ኢሳ.40፥10-11/
- የማይጠፋውን ዘላለማዊ አክሊል ሽልማት ያገኛሉ።
(A crown that will not last)
  - የሕይወት አክሊል፡- ስለክርስቶስ በብዙ መከራ በፈተናና በማጣት ለሚያልፉ የሚሰጥ ነው።
  /ያዕ 1:12 ራዕ. 2:11፥ ራዕይ 7:13-17/
  - የክብር አክሊል፡- ለአገልግሎት የሚሰጥ ነው። /1ጴጥ 5:4፥ ዮሐ. 12:26፥ ዕብ. 6:10-12/
  - የጽድቅ አክሊል፡- ጻድቃን ለሆኑና የጌታን ዳግም ምፅአት ለሚናፍቁ የሚሰጥ ነው። /2ጢሞ 4:8/
  - የድል አክሊል፡- ለአሸናፊዎች የሚሰጥ ነው።
  /1ቆሮ. 9:25፥ 2ጢሞ 2:5፥/
  - የደስታ አክሊል፡- ለአገልግሎት ፍሬ የሚሰጥ ነው።
  /ዮሐ. 15:16፥ ፊል. 4:1፥ 1ተሰ. 2:19/
- ዘላለማዊ ርስት ወይም ሕይወት ይወርሳሉ
/ሮሜ 8:17 2ቆሮ 5:1-5 ማቴ 25:34 ገላ 4:7/
- እንደታማኝነታቸው መጠን ይሾማሉ።
/ማቴ 24:45-47 25:21፥23፥ ሉቃ 22:28-30/

«እነሆ ቶሎ ብዬ እመጣለሁ ማንም አክሊልህን እንዳይወስድብህ ያለህን አጽንተህ ያዝ ድል የነሣው በአምላክ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን አደርገዋለሁ ወደፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም።» /ራዕ 3:11-12/



# ምህርት 21 - የእግዚአብሔር መንግሥት

## 21.1 በኢየሱስ መጀመሪያ መምጣት የተገለጠ መንግሥት

ሀ/ መንፈሳዊ መንግሥት ነው
ይህ መንግሥት በሥጋ ዓይን የማይታይ መንፈሳዊ ሆኖ በሰው ሕይወት የሚሠራ መንግሥት ነው። ክርስቶስም የመጣው ይህንን የእግዚአብሔርን አገዛዝ ሕግ በሰው ሕይወት ለማስፈን ነው።
/ሮሜ 14:17/
ፈሪሳውያን የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች? ብሎ በጠየቁት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ «እነሆ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና» አላቸው። ምክንያቱም ኢየሱስ ሰው ሆኖ ወደ ምድር በመጣ ጊዜ ይህችን መንግሥት ይዞ መጥቷልና። ስለዚህ ሰዎች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደግል አዳኝ አድርገው በሚቀበሉበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባሉ የእግዚአብሔር መንግሥትም በመንፈስ በውስጣቸው ትኖራለች።
/ማር 1:14-15 ሉቃ17:20-21 ዮሐ 14:23/

ለ/ የእግዚአብሔር መንግሥት በሰዎች መካከል የመኖሩዋ ምልክቶች፡-

- ለንስሐ የደህንነት ወንጌል መሰበክ /ዮሐ 3:3 ማቴ 11:6 4:17/
- በእግዚአብሔር ጣት የአጋንንት መውጣት።
/ማቴ 12:28 ዮሐ 12:31 1ዮሐ 3:8/
- ለድውያን የሚደረግ የፈውስ ተአምራት።
/ማቴ 4:23 9:35 ሐዋ 3:16 ሉቃ 10፥8-9/
- የሰዎች አርነት መውጣትና መቀደስ።
/ማቴ 11:5 ዮሐ 17:17 2ቆሮ 3:17/
- የመንፈስ ቅዱስ ሥራ /ዮሐ 16:8-11 ሐዋ 1:8/
ይሁን እንጂ በአሁኑዋ ዓለም ላይ የእግዚአብሔር መንግሥት ወይም አገዛዝ በሙላት እንዳልተገለጠ እንረዳለን ምክንያቱም ሰይጣን ለጥቂት ጊዜ የዚህ ዓለም ገዢ ሆኖ ይሠራልና።
/ራዕ 12:12 ኢዮ 37:19 ዮሐ 12:31 14:30 16:11፥ 2ቆሮ 4:4 ኤፌ 2:2/

## 21:2 በኢየሱስ ዳግም ምጽአት የሚገለጥ መንግሥት

«በሰማይም እንዲህ የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ተሰሙ የዓለም መንግሥት የጌታችንና የእርሱ ክርስቶስ መንግሥት ሆነች እርሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሣል» /ራዕ 11:15-18/

- ይህን መንግሥት ጌታ ኢየሱስ በዳግም ምጽአቱ ጊዜ አሁን ባለንበት ምድር ላይ የዚህ ዓለም መንግሥትን ሥርዓት አፍርሶ የሚያቋቁመው መንግሥት ነው።
- ይህ መንግሥት የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ የሆነው ክርስቶስ የሚነግሥበትና የሚገዛበት ሆኖ ከእርሱም ጋር ሙሽራዋ የሆነችው ቤተክርስቲያንና የመጀመሪያውን ትንሣኤ ያገኙት ቅዱሳን ለሺ ዓመት ያስተዳድራሉ /ራዕ 2:26-27/

- ይህ መንግሥት ለአውሬውና ለሐሰተኛው ነቢይ ኃይል ይሰጥ የነበረው ሰይጣን ስለሚታሰር ጽድቅ፤ሰላም፤ፍትሕና ብልጽግና የሰፈነበት የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። /ኢሳ 9፡7 ዳን 2፡44 ራዕ 19፡11-16/

ማሳሰቢያ፡- ስለ ሺህ ዓመተ መንግሥት የተሰጠውን ማብራሪያ በትምህርት 19 ላይ ይመልከቱ

## 21.3 ዘላለማዊ መንግሥት

ዘላለማዊ መንግሥት እግዚአብሔር በሙሉ ሥልጣን የሚገዛውና የሚያስተዳድረው ፍጻሜ የሌለው የእግዚአብሔር ጽድቅ አገዛዝ ዘመን ነው። ይህ መንግሥት መንግሥተ ሰማይ፤ ገነት፤ ከዚህች ምድር ያልሆነ መንግሥት፥ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም. . . ወዘተ ተብሎ ይጠራል።

/ራዕ 21፡1-5 ማቴ 5፡10 19-20 ሉቃ 23፡43/

ሀ/ የዘላለማዊ መንግሥት አጠቃላይ ገጽታ ምን ይመስላል? /ራዕ 7፡16-17 21፡1-27 22፡1-5/

- ዘላለማዊ መንግሥት ወደፊት ሊገለጥ ያለው ትንቢት ሲሆን አማኞች በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት አሁን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚለማመዱትና በተስፋም የሚጠባበቁት ፍጹም
- የሆነ የእግዚአብሔር ክብር በሙላት የሚገለጥበት መንግሥት /አገዛዝ/ ነው። /ሮሜ 8፡18-23 ሉቃ 22፡17-18/
- በሺህ ዓመት ፈጻሜ ላይ የነጩ ዙፋን ፍርድ ሂደት እንደተጠናቀቀ በአዲስ ሥርዓት የሚቀጥል መንግሥት ነው።
- አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ከአዲሲቱ ከተማ ኢየሩሳሌም ጋር ከእግዚአብሔር ዘንድ ይወርዳል የፊተኛው ሰማይና ምድርም ያልፋል /ኢሳ 65፡17 66፡22 2ጴጥ 3፡13/
- ዘላለማዊ መንግሥት ሁሉን ቻይ በሆነው በእግዚአብሔር መለኮታዊ ችሎታ የተገነባ፤ የተዋቀረና የሚተዳደር የጽድቅና የሰላም መንግሥት ነው /መዝ 103፡19 ዮሐ 14፡1-3/
- በከተማይቷ ውስጥ መቅደስ የለም የፀሐይና የጨረቃ ብርሃን አያስፈልጓትም ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደሱዋ ብርሃኑዋም ነው።
- የዘር፥ የቀለም፥ የቋንቋ ልዩነት አይኖርም። /ራዕይ 7፡9/
- ክፉ የተባለ ሁሉ ወደዚያ ከተማ ከቶ አይገባም ቀንም ሌሊትም አይሆንም ስለዚህ ደጆቹዋ ለዘላለም አይዘጉም።
- ባሕር ሞትና ሲኦል በዚያ የለም

ለ/ በዘላለማዊ መንግሥት አዲስ የተባሉ ነገሮች

1. አዲስ ሰማይ /ራዕ 21፥1/
2. አዲስ ምድር /ራዕ 21፥1 /
3. አዲሱ ስም /ራዕ 2፥17 ፤ 3፥12 ኢሳ 62፥2/
4. አዲሱ ቤተመቅደስ /ራዕ 21፥22 /
5. አዲስ ብርሃን /ራዕ 21፥23 /



6. አዲሱ ገነት /ራዕ 22፥1-5 /
7. አዲሱ የወይን ፍሬ/ ጠጅ/ (ማቴ 26:29 ማር 14:25)
8. አዲሱ የወይን ፍሬ /ጠጅ / /ማቴ 26፥29 ማር 14፥25/
9. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም /ራዕ 21፥2 ፤ 9-21/

ሐ/ የሺህ ዓመት ኢየሩሳሌምና የአዲሲቷ ኢየሩሳሌም ልዩነት

| | የሺ ዓመት ኢየሩሳሌም | አዲሲቷ ኢየሩሳሌም |
|---|---|---|
| 1 | ቤተመቅደስ አለ /ሕዝ 40፥48/ | ቤተ መቅደስ አይኖርም /ራዕ 21፥22/ |
| 2 | ቀንና ሌሊት አለ /ኢሳ 30፥26 ፤ 60፥19/ | የእግዚአብሔር ክብር ያበራለታል/ራዕ 21፥25/ |
| 3 | መወለድ መሞት አለ /ኢሳ 65፥20/ | የዳኑት ሁሉ እንደ መለአክ ይሆናሉ /ራዕ 21፥4/ |
| 4 | ክርስቶስ ለሺ ዓመት ይነግሣል/ራዕ 20፥4/ | ክርስቶስ ለዘለዓለም ይነግሣል። /ዕብ 12፥22-24 ራዕ 22፥1-7/ |

መ/ በዘላለማዊ መንግሥት የቅዱሳን ኑሮ ምን ይመስላል?

- ድል የነሱት ከዚያ ከቶ አይወጡም የእግዚአብሔር ስም፤ የቅዲሲቱ ከተማ የኢየሩሳሌም ስምና የክርስቶስ አዲሱ ስም በእነርሱ ላይ ይጻፋል። ይህም የዘላለማዊ መንግሥት ዜግነት ማረጋገጫ ነው። /ራዕ 3፡12/
- መርገም፤ ሥቃይ ፤ልቅሶ፤ ጩኸት፤ ሐዘን፤ ጨለማ፤ ረሃብ ጥማት በዚያ የለም። እግዚአብሔር እንባን ሁሉ ከዓይኖቻቸው ላይ ያብሳል።/ኢሳ 25፡8 ራዕ 7፡17/
- ከእልፍ አዕላፋት መላዕክት ጋር በዙፋኑ ፊት ሆነው ያለማቋረጥ አምላካቸውን ያገለግላሉ ያመልካሉ። /ራዕ 7፡15/
- በዘላለማዊ መንግሥት የሚኖሩ ቅዱሳን ሁሉ በገነት ካለችው ሕይወት ዛፍ ፍሬዋን ይበሉ ዘንድ ሥልጣን ይሰጣቸዋል /ዘፍ 2፡9 ራዕ 2፡7 22፡2 14/
- የከበረውን የትንሣኤ አካል ለብሰው እንደ እግዚአብሔር መላዕክት ሆኖ ያለ ኃጢአትና ያለፍርሃት እንደ ሰማይ ፀደል እየደመቁ ከአምላካቸው ጋር ለዘላለም የሚኖሩበት ሕይወት ነው። /ዳን 12፡3፥ ማቴ 13፡43 22፡30/

የእግዚአብሔርን መንግሥት በዚህ መልክ በምናይበት ጊዜ ሰው በኃጢአት በመውደቁ ምክንያት ከእግዚአብሔር መንግሥት ተለይቶ ስለነበር እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ በልጁ በኩል ወደ ቀድሞ ክብሩ ሙላት ለመመለስ ባዘጋጀው በማዳኑ ዕቅድ መሠረት አምላክ ሰው ሆኖ ሲመጣ በንስሐ ወደ እግዚአብሔር በሚመለሱት ሁሉ ሕይወት ይህንን መንፈሳዊ መንግሥት ለማቋቋም ይዞ መጣ እንጂ ከዚያ በፊት የእግዚአብሔር መንግሥት በምድር ላይ የለችም ማለት አይደለም።

እግዚአብሔር «ያለና የሚኖር» ነው መንግሥቱም በጊዜና በቦታ የማይወሰን መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው ከዘላለም እስከ ዘላለም በፍጥረታት ሁሉ ላይ የበላይ ገዢና ተቆጣጣሪ ነው።
/ዘጸ 3፡14 ኢያ 3፡11 መዝ 22፡28 47፡2 135፡6–7/



## ማጠቃለያ፡–

«እኛም እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍጹም አድርገን ማቅረብ እንችል ዘንድ ሰውን ሁሉ በጥበብ ሁሉ እየመከርንና እያስተማርን እርሱን እንሰብካለን። እኔም በብርታት በውስጤ በሚሠራው በእርሱ ኃይል ሁሉ እየታገልሁ ለዚሀ ዓላማ እጥራለሁ»/ቆላ. 1፥28–29/

የቤተክርስቲያንና የአገልጋዮችም ትጋት መስዋዕትነትና አገልግሎት ፍሬ የሚለካውም እዚህ ላይ ነው። አማኞችን ጨርሶ ማስተማር፣ ደቀ መዝሙር ማድረግና ለእግዚአብሔር መንግስት ብቁ እንዲሆኑ መርዳት።/ሐዋ 20፡20-21/

የእግዚአብሔር ዓላማ በክርስቶስ በኩል ልጆች ይሆኑ ዘንድ የተጠሩ ሁሉ እግዚአብሔርን በማወቅና በመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት ክርስቶስን ወደመምሰል ሕይወት እንዲደርሱ ነው።/ሮሜ 8፥29–30/

ለዚህም አማኞች ሁሉ በትጋት እየጸለዩ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመደገፍ በእግዚአብሔር ቃል የተገለጠውን ለክርስትና ሕይወት መሠረት የሆኑ መንፈሳዊ እውነቶችን በሚገባ ለማወቅና ሕይወትን ለማነጽ መጽሐፍ ቅዱስን በትጋት ማጥናትንና በቃሉ የመኖርን ሕይወት ይጠይቃል።/2ጢሞ 3፡16-17/

ቤተክርስቲያንም ከጌታ የተሰጣት አደራ የምሥራቹን ወንጌል ለፍጥረት ማዳረስና የዳኑ ነፍሳትን ወደ ክርስቶስስ ሙላት እንዲደርሱ ለማድረግ ማስተማር፣ ማሳደግና ደቀመዝሙር ማድረግ ሲሆን ለዚህም ዓላማ ቃሉን በሚገባ ማስተማርና መመገብ እንዲችል የመንጋ አደረጃጀትና አቀማመጥ ምቹ እንዲሆን ማድረግ፣ መጽሐፍ ቅዱስ በግልና በቡድን የማጥናት ልምዳቸውን እንዲያዳብሩ ማበረታታትና ጠቃሚ መጻሕፍትን በማቅረብ የመርዳት ኃላፊነት ይጠበቅበታል።/ቈላ.2፡1–3፤ ኤፌ. 1፡16–19/

«ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተፃፈውን የሚጠብቁት ብፁአን ናቸው።» /ራዕ 1፡3/

## የውይይት ጥያቄዎች

1. ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?
2. ስለ ክርስቶስ ዳግም ምፅአት ከተሰጡ ሦስት ዋና ዋና አመለካከቶች በየትኛው ትስማማለህ? ለምን?
3. ያለንበት ወቅት የመጨረሻው ዘመን መሆኑን የሚያመለክቱ ምልክቶችን ዘርዝሩ::
4. በክርስቶስ መጀመሪያ አመጣጥና ሁለተኛ አመጣጥ ምን ልዩነት አለው?
5. በሺህ ዓመት መንግሥትና ዘላለማዊ መንግስት የቅዱሳን ኑሮ ምን ሊመስል ይችላል?
6. በመንፈሳዊ ሞትና ሁለተኛ ሞት መካከል ያለው ግንኙነትና ልዩነት ምንድን ነው?
7. ስለ ሙታን ትንሳኤ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? እንዴት ይነሣሉ? የምድራዊ አካልና ትንሳኤ አካል ልዩነትሳ?
8. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ጌታ ዳግም ምፅአት ሲናገር እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ ይለናል እንዴትና በምን መዘጋጀት አለብን? (ሉቃ 12:40) ይመልከቱ



# ዋቢ መጻሕፍት


- Charles Ryrie . A Survey of Bible Doctrine. Chicago, III: Mood, 1972
- Chafer, Lewis Sperry. Revised by John F. Wal Voord. Major Bible Themes. Grand Rapids Zondervan, 1974.
- Donald C. stamps. The full life study Bible. Grand Rapids, Michigan, 1984.
- Louis Berkhof. Systematic Theology. Grand Rapids Michigan,1949.
- Thomas Hale. The Applied NT. Commentary. King way publications east bourne.
- W/Vision – East Africa Sub Regional office, Introduction to Christian Doctrine (Amharic Version) Kenya, 2001
- የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ፡- የ1962 ዓ.ም ትርጉም እና የ1993 ዓ.ም አዲሱ መደበኛ ትርጉም ተጠቅሚያለሁ።